አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3585 ቅዳሜ ነሐሴ 2 ቀን 2018 ዓ.ም ዋጋው 10.00 ብር

## ኢትዮጵያ እየመከረች ነው

# የመዲናዋ ቱሪዝም ጌጥ



6

ግራፊክስ - በእዮብ ተፈራ

አረንጓዴ አሻራ ለከተማዋ ቱሪዝም ጉልህ አስተዋፅኦ እያበረከተ ነው

## የሉዓላዊነት ልብ

8




ፎቶ- ከፋይል

የባህር በር ጥያቄው መልስ እንዲያገኝ ሁሉም የአርበኝነት ሚናውን እንዲወጣ ይጠበቃል

## የሀገር በቀል እሴቶች አሻራ በዘመናዊው ኪነ ጥበብ

11



ፎቶ- ከገፀ ድር

የሀገር በቀል ሙዚቃዎችና መሳሪያዎች ለኪነ ጥበቡ መጎልበት አስተዋጽኦ እያደረጉ ነው

## የአዳጊዎቹ ተሳትፎ በዓለም ሻምፒዮናው

20



ፎቶ- ከገፀ ድር

በ 21ኛው የዓለም ከ20 ዓመት በታች ሻምፒዮና እየተካፈሉ ካሉ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች መካከል ከፊሎቹ

# ወሳኙ የታሪክ ምዕራፍ

- በምክክሩ ሂደት መግባባት ላይ ለመድረስ "ለጋራ ጥቅም ሲባል የእኔን ጥቅም መስዋዕት ማድረግ አለብኝ" የሚል አመለካከት ሊኖር እንደሚገባ ተጠቁሟል

**በስንታየሁ ምትኩ**

ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ የምትታወቅባቸው በርካታ መገለጫና ማንነት አላት፡፡ ዳር ድንበሯን ከወራሪዎች ለማስጠበቅ ባደረገችው የተጋድሎ ታሪኳ ትታወቃለች፡፡ አፍሪካውያን በቅኝ ግዛት ቀንበር በሚማቅቁበት ወቅት፣ ያስመዘገበችው ድል ለመላው ጥቁርና ጭቁን ህዝብ የነጻነት ተምሳሌት በመሆን ስሟን በታሪክ መዝገብ ላይ በደማቅ መዝገብ ላይ ማስፈር ችላለች፡፡ በጥንታዊ የስልጣኔ ባለቤትነቷ፣ በሰው ዘር መገኛነቷ፣ በድልብ የባህል ሀብቷ፣ በለም መሬቷ፣ በበርካታ ወንዞቿ፣ በሰማይ ጠቀስ ተራሮቿ...

ወደ ገጽ 7 ዞሯል



ፎቶ- ከገፀ ድር

ሀገራዊ ምክክሩ ለዛሬው ብቻም ሳይሆን ለቀጣይ ትውልድም ዘርፈ ብዙ ትሩፋት ይዞ የመጣ ወርቃማ ዕድል ነው




# አዲስ አበባን በከተሜነት ልኬት

- የኮሪደርና ወንዝ ዳርቻ ልማቶች፣ በቴክኖሎጂ የታገዙ አገልግሎቶች የከተማዋን ዝማኔ ከፍ እያደረጉት ስለመሆኑ ተመላክቷል

**በቶለሳ መብራቴ**

ከተሞች የሰው ልጅ ሥልጣኔ፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የፈጠራ ማዕከላት ናቸው። የአንድ ከተማ እውነተኛ ስኬት የሚለካው በረጃጅም ፎቆች ከፍታ ወይም በኮንክሪት ሕንፃዎች ብዛት ሳይሆን፣ የመሬት አጠቃቀሙ በሳይንስ መመራቱን፣ የመጓጓዣ ሥርዓቱ ውጤታማ መሆኑን፣ የአረንጓዴ ስፍራዎቹ መጠበቃቸውን፣ የአደጋ መከላከል ብቃቱን እና የነዋሪዎችን የሕይወት ጥራት ማሻሻሉን በማረጋገጥ ጭምር ነው።

የዓለም ሕዝብ ቁጥር በከተሞች ውስጥ በፍጥነት እየጨመረ በመጣበት በዚህ የ21ኛው ክፍለ ዘመን፣ የከተማ ፕላንና ምህንድስና የዜጎችን ዕለታዊ ሕይወት የሚቀርጹ ወሳኝ መሣሪያዎች ሆነዋል። በአፍሪካ አህጉር በፍጥነት ከሚያድጉ ከተሞች አንዷ የሆነችው አዲስ አበባም፣ ባለፉት 140 ዓመታት ውስጥ ከተፈጥሯዊ አመሠራረት ወደ ዘመናዊ የከተማ ምህንድስና የምትሸጋገርበትን ረጅም

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

አድራሻ +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

## ርዕሰ አንቀፅ



# የአረንጓዴ አሻራ ተሳትፎ ተጠናክሮ ይቀጥል!

የአየር ንብረት ለውጥ፣ የደን መመናመን፣ የአፈር መሸርሸርና የከባቢ አየር ብክለት የዘመናችን ትልልቅ ፈተናዎች ሆነዋል። የተፈጥሮ ሀብትን መመለስ የአካባቢ ጥበቃ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የምግብ ዋስትና፣ የጤና፣ የኢኮኖሚና የትውልድ ደህንነት መሠረት ነው። ኢትዮጵያ ይህን እውነታ በመገንዘብ በ2011 ዓ.ም የጀመረችው የዐረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በዓለም ደረጃ ትኩረት ካገኙ የተፈጥሮ ማገገሚያ ስልቶች አንዱ ሆኗል። ይህ የሚያሳየው ተፈጥሮን መልሶ የማልማት ስራ በተግባር ሲጀመር ውጤቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሻገር መሆኑን ነው።

ኢትዮጵያ በረጅም ዓመታት ውስጥ በደን ጭፍጨፋ፣ በመሬት መራቆትና በውሃ ምንጮች መቀነስ ምክንያት የተፈጠሩ ችግሮችን ለመቀልበስ ትልቅ ጥረት እያደረገች ትገኛለች። የግብርና ሚኒስቴር መረጃ እንደሚያሳየው፣ በ1990ዎቹ መጨረሻ ወደ 3 በመቶ የወረደው የደን ሽፋን በዐረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር እና በተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥረቶች ዳግም እያገገመ ነው። ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ከ48 ቢሊዮን በላይ ችግኞች መተከላቸውና የሀገሪቱ የደን ሽፋን ወደ 24 በመቶ መጠጋቱ የፕሮግራሙን ውጤታማነት ያሳያል። በዘንድሮው መርሃ ግብር ደግሞ ከ8 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል ዕቅድ ተይዟል።

የዐረንጓዴ አሻራ ለአዲስ አበባ ትልቅ ትርጉም አለው። በፍጥነት እያደገች ያለችው ዋና ከተማ በበርካታ ተሽከርካሪዎች፣ በኢንዱስትሪዎችና በሌሎችም ምክንያት የአየር ብክለትና የሙቀት መጨመር ተግዳሮትን ተጋፍጣለች። ስለዚህ በከተማዋ እየተካሄዱ ያሉ የኮሪደር እና የወንዝ ዳር ልማት፣ የመናፈሻ ፓርኮች ግንባታና የዐረንጓዴ ሽፋን ማስፋፊያ ሥራዎች ከተማዋን ንፁህ አየር እንዲኖራት እና የነዋሪዎች ጤና ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ናቸው። ዛፎች ካርቦንን ይወስዳሉ፣ የአየር ብክለትንና የከተማውን ሙቀት ይቀንሳሉ፣ ለመዝናኛና ለጤናማ ኑሮ ምቹ አካባቢ ይፈጥራሉ። ይህም የአዲስ አበባን ስም የሚመጥን ዘላቂ የከተማ ልማት መሠረት ነው።

የዐረንጓዴ አሻራ ስኬት የመንግሥት ቁርጠኛ አቋምና የሕዝብ ቀጣይነት ያለው ተሳትፎ ውጤት ነው። በየዓመቱ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ዝናብና ብርድ ሳይበግራቸው በችግኝ ተከላ ይሳተፋሉ። ይህ የትብብር መንፈስ ኢትዮጵያ ታላላቅ ሀገራዊ ግቦችን በሕዝብ ኃይል ማሳካት እንደምትችል አረጋግጧል። አንድ ሰው የሚተክለው ጥቂት ችግኝ ትንሽ ቢመስልም፣ ሚሊዮኖች ሲደግሙት የሀገርን ገጽታ የሚቀይር ታሪካዊ እንቅስቃሴ ይሆናል። ይህ የአንድነት መንፈስ በአዲስ አበባም ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።

ስለዚህ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች፣ የመንግሥት ተቋማት፣ የግል ድርጅቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የሃይማኖት ተቋማትና የማህበረሰብ ድርጅቶች በዘንድሮው የዐረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር የበለጠ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ይገባቸዋል። የምንተክለውን ችግኝ ከመትከል በላይ መንከባከብ፣ የአካባቢያችንን አረንጓዴ ገፅታ ማስጠበቅና የተፈጥሮ ጥበቃን የዕለት ተዕለት ባህላችን ማድረግ የዘላቂ ለውጥ መሠረት ነው። ዛሬ የምንፈጥረው አረንጓዴ አሻራ ነገ ንጹህ አየር፣ ጤናማ ከተማ፣ ጠንካራ ኢኮኖሚና ተስፋ የሞላባት ኢትዮጵያን ለትውልድ ያሻግራል። ይህ የትውልድ አደራ ነው፤ ሁላችንም በተግባር ልንወጣው ይገባል።

## የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

# ክረምትና አልባሳት

**ቻቺ ከለሚኩራ**

በየትኛውም ዓለም ቢሆን ክረምትና በጋ መፈራረቃቸው አይቀሬ ነው፡፡ በተለይ የክረምት ወራት ቅዝቃዜና ዝናብ የሚበዛበት ወቅት መሆኑ ከማንም የተሰወረ አይደለም፡፡ በአውሮፓና አሜሪካ ያለው ክረምት ከፍተኛ ቅዝቃዜና በረዶ የሚበዛበት ስለሚሆን ዜጎች ለአለባበሳቸውና አኗኗራቸው ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣሉ። በአገራችን ያለው የአየር ሁኔታ ተመጣጣኝ ነው ቢባልም የክረምቱ ወቅት በዝናብ የተሞላ ነው። በገጠር አርሶ አደሩ እንደየኑሮ ዘይቤው የከሰል ፍምና እሳት ዳር ከቦ ማምሸትና ሙቀት የሚሰጡ አልባሳትን ለመከናነብ ይሞክራል።

በከተሞችም ሰዎች እንደ አቅማቸው የክረምቱን ቅዝቃዜ ለመከላከል የተለያዩ መንገዶችን ይጠቀማሉ። በተለይ እንደ አዲስ አበባ ባሉ አካባቢዎች ከሚለብሱት አልባሳት፣ ከሚመገቡት ምግብና ከሚጫሙት ጫማ በተጨማሪ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰሩ ዘመናዊ የቅዝቃዜ መከላከያ ወይም ሙቀት ማመንጫ ቴክኖሎጂዎችን የሚጠቀሙም አሉ፡፡

ይሁን እንጂ በመካከለኛና ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያለው ማህበረሰብም ቢሆን ክረምቱ ሳይበረታ ቀደም ብሎ ለክረምት የሚያስፈልጉ አልባሳትን ማዘጋጀት ብሎም ከክረምቱ ጋር ተያይዞ የሚመጣን ጉዳት ለመከላከል አስቀድሞ ማሰብ ይኖርበታል። ከቤታችን ከመውጣታችን በፊት የሰውነት ሙቀትን ለመጠበቅ እና ከዝናብ ለመከላከል እንደ ጃኬትና ሹራብ ያሉ የክረምት ልብሶችን መደረብ፣ ትኩስ ነገር መጠጣት እና ሙቀት የሚሰጡ ምግቦችን መመገብ ይጠቅማል።

በከተማችን እንደምንታዘበው በክረምት ወቅት አለባበስን በማስተካከል ጤናን የመጠበቅ ጥረታችን በቂ አይደለም። ለአብነት ያህል በክረምት የማይመከሩ ስስ ልብሶችን ለብሰው የሚሄዱ፣ ፀጉራቸውን ወይም አናታቸውን የማይሸፍኑና ክፍት ጫማዎችን የተጫሙ ሰዎችን እናያለን። ይህ አቅም ያለመኖር ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ ማድረግ ለምንችለው ግን ለራስ ካለማሰብ ወይም በቸልተኝነት የሚደረግ ተግባር ሊሆን ይችላል፡፡ በዚያው ልክ የውሃ መከላከያ ጃኬቶች በወንዶችም ሆነ በሴቶች ዘንድ እየተለመዱ መጥተዋል። ውሃ የማያሳልፉ ወይም ጃንጥላ የሚተኩ ጃኬቶች ከባድ ዝናብ ሲኖር በጣም የሚጠቅሙ ስለሆነ ሊዘወተሩ ይገባል፡፡

በተለይ ከቤት ሲወጣ ሰውነትን ለማሞቅ ከጥጥ ወይም ከሱፍ የተሰሩ ወፍራም ሹራቦችን መልበስ፤ ቤት ውስጥ የምንቀመጥ ደግሞ ጋቢ፣ ወፍራም ሹራብና አነስተኛ ብርድ ልብስ መጠቀም ሊዘወተር ይገባል። አቅማችን የሚፈቅድ ከሆነ የዝናብ ጫማዎች፣ ፕላስቲክ ወይንም ውሃ የማያሳልፉ ጫማዎችን መጠቀም እግርን ከውሃ እና ጭቃ ለመከላከል ጤናማ ተግባር ነው። ሻርፖችን አንገት ላይ ማድረግም ከቀዝቃዛው የክረምት ንፋስ ለመሸፈን ይረዳል።

የክረምት አልባሳት የሰውነት ሙቀትን ከመጠበቅ ባለፈ እንደ ፋሽን ተወስደው ውበትን የሚያጎናፅፉ አምረንና ሸክ ብለን እንድንታይ የሚያደርጉም ናቸው። በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ሴቶች ከጉልበት በላይ ወይም እስከ ጉልበታቸው የሚደርስ ጫማ በአጭር ጉርድ ቀሚስ ተጫምተው ሻርፕ፣ ጥላና ውሃ የማያሳልፉ ጃኬቶችን ደርበው በክረምት ወቅት በፋሽን ልብሶች አምረው መታየታቸው የተለመደ ነው፡፡

ነገሩን በወጉ የተረዱት ደግሞ ክረምቱን ጤናማና ጠንካራ ሆነን ለማሳለፍ አለባበስ ብቻ ሳይሆን አመጋገባችንም መስተካከል እንዳለበት ይመክራሉ። በተለይ ቅባትነት ያላቸው ምግቦች፣ ማርና መሠል ሙቀት ሰጭ ምግቦች ከሰውነት መቀዝቀዝ ሊጠብቁን ይችላሉ፡፡

ADDIS MEDIA NETWORK
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ**

**እየተዘጋጀች ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ ግንቦት 1985 ዓ.ም ተመሰረተች**

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ግራፊክስ ዲዛይን**
እዮብ ተፈራ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ይግለጡ ጓዴ
ለይላ መሀመድ
አብርሃም ገብሬ
ፋንታነሽ ተፈራ

**ዋና አዘጋጅ**
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ
ቶሎሳ መብራቴ

# አዲስ ... ከገጽ 1 የዞረ

ታሪካዊ ጉዞ አድርጋለች። ከተሞች የሰው ልጅ ሥልጣኔ፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የፈጠራ ማዕከላት ናቸው። የአንድ ከተማ እውነተኛ ስኬት የሚለካው በረጃጅም ፎቆች ከፍታ ወይም በኮንክሪት ሕንፃዎች ብዛት ሳይሆን፤ የመሬት አጠቃቀሙ በሳይንስ መመራቱን፣ የመጓጓዣ ሥርዓቱ ውጤታማ መሆኑን፣ የአረንጓዴ ስፍራዎቹ መጠበቃቸውን፣ የአደጋ መከላከል ብቃቱን እና የነዋሪዎችን የሕይወት ጥራት ማሻሻሉን በማረጋገጥ ጭምር ነው።

የዓለም ሕዝብ ቁጥር በከተሞች ውስጥ በፍጥነት እየጨመረ በመጣበት በዚህ የ21ኛው ክፍለ ዘመን፣ የከተማ ፕላንና ምህንድስና የዜጎችን ዕለታዊ ሕይወት የሚቀርጹ ወሳኝ መሣሪያዎች ሆነዋል። በአፍሪካ አህጉር በፍጥነት ከሚያድጉ ከተሞች አንዷ የሆነችው አዲስ አበባም፣ ባለፉት 140 ዓመታት ውስጥ ከተፈጥሯዊ አመሠራረት ወደ ዘመናዊ የከተማ ምህንድስና የምትሸጋገርበትን ረጅም ታሪካዊ ጉዞ አድርጋለች።

አዲስ አበባ በ1879 ዓ.ም በዳግማዊ ምኒልክና በእቴጌ ጣይቱ በእንጦጦ ተራራ ሥር ስትመሠረት፣ ለቦታው መመረጥ ዋና ምክንያቶች የፍልውሃው መኖር፣ መልካም የአየር ጠባይ፣ የእንጨት ሀብትና ስትራቴጂካዊ አቀማመጥ ነበሩ። ይህ ውሳኔ በዘመኑ ብልህ አካሄድ ቢሆንም፣ አመሠራረቷ ግን በወቅቱ የነበሩትን የከተማ ፕላን መርሆዎች ተከትሎ አልነበረም። ከተማዋ በዘመናዊ ማስተር ፕላን ሳይሆን በመኳንንት ሰፈር፣ በገበያዎች፣ በቤተ መንግሥትና በቤተ እምነቶች ዙሪያ በተፈጥሯዊ ሁኔታ እየተስፋፋች ሄደች።

አዲስ አበባ ከተቆረቆረች ጀምሮ በፍጥነት እያደገች የመጣች የአፍሪካ ዋና ከተማ ናት። ይሁን እንጂ ዕድገቷ ሁልጊዜ በአንድ ዓይነት ዕቅድ አልተመራም፤ በየዘመኑ ከፖለቲካ፣ ከኢኮኖሚ፣ ከሕዝብ ብዛት እና ከቴክኖሎጂ ለውጦች ጋር ተያይዞ የከተማዋ ፕላን ሲከለስና ሲሻሻል ቆይቷል። በታሪኳ ውስጥም ከ1929 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በርካታ የማስተር ፕላንና የመዋቅራዊ ፕላን ሙከራዎች እንደነበሩ የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቢልት ኤንድ ኢንቫይሮንመንት (Built and Environment) ኮሌጅ መምህርና ተመራማሪ ብርሃኑ ግርማ (ዶ/ር) እንደሚገልጹት፣ የከተማዋ የመጀመሪያ ዕድገት በሳይንስና በምህንድስና ሕግጋት ላይ ባለመመሥረቱ፣ መዲናዋ አሁን ላይ እንደ አዲስ ፈርሳና ታስባ እንድትገነባ የሚያስገድድ ታሪካዊ ጫና ውስጥ እንድትወድቅ አድርጓታል።

በቂ የመንገድ መረብ አለመኖር፣ የእግረኛና የሳይክል መንገዶች እጥረት፣ እንዲሁም የሰው ልጅን ክብር የማይመጥኑ ቤቶችና መጋፋቶች የነበሩበት የቆየው የከተማዋ አደረጃጀት፣ የአንድን ከተማ መሠረታዊ መስፈርቶች የማያሟላ እንደነበር ምሁሩ ያመላክታሉ።

በ20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ የሕዝብ ቁጥር መጨመር፣ የገጠር ወደ ከተማ ፍልሰት፣ የንግድና የኢንዱስትሪ መስፋፋት ከተማዋን በከፍተኛ ፍጥነት አሳደጓት። ሆኖም ይህ ዕድገት ከበቂ መሠረተ ልማት ጋር አልተመጣጠነም። ብዙ ጊዜ የአዲስ አበባን የመዋቅር ችግሮች ከቅርብ ዓመታት ፖለቲካዊ ለውጦች ጋር ብቻ ለማያያዝ ሙከራ ቢደረግም፣ እውነታው ግን ችግሮቹ ለበርካታ ዓመታት የተጠራቀሙ መሆናቸውን ያሳያል።


ፎቶ- ከገፀ ድር
የፒያሳ የትናንትና የዛሬ ገፅታ በከፊል

የከተማዋ ሕዝብ ሲጨምር መንገዶች፣ የፍሳሽ መስመሮችና የሕዝብ መጓጓዣዎች አብረው ባለማደጋቸው፣ የከተማ ፕላን ባለሙያዎች "የመሠረተ ልማት ክፍተት" የሚሉት ክስተት ተፈጠረ። የትራፊክ መጨናነቅ፣ የጎርፍ አደጋ፣ የመኖሪያ ቤት እጥረት፣ የአየር ብክለትና የአገልግሎት መጓደል የዚሁ የተከማቸ መዋቅራዊ ችግር ውጤቶች ናቸው።

የከተማ ፕላን ባለሙያዎች "ከተሞች በአጋጣሚ አይገነቡም፤ በውሳኔ ይገነባሉ" ይላሉ። አዲስ አበባ በታሪኳ በርካታ የማስተር ፕላን ሙከራዎችን አስተናግዳለች። የመጀመሪያው ዘመናዊ የከተማ ፕላን በ1930ዎቹ በጣሊያን ወረራ ወቅት የተዘጋጀ ሲሆን፣ ዋና ዓላማው የቅኝ ግዛት አስተዳደርን ማገልገልና ነዋሪዎችን በቦታ መለየት ነበር።

በመቀጠል በ1950ዎቹና 1960ዎቹ የፈረንሳይና የብሪታንያ ባለሙያዎች የተለያዩ ማስተር ፕላኖችን ቢያዘጋጁም፣ በተለያዩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ተቋማዊ ምክንያቶች ሙሉ በሙሉ ሊተገበሩ እንዳልቻሉ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህም ከተማዋን ከሳይንሳዊ ዕቅድ ይልቅ በሁኔታዎችና በክስተቶች የምትመራ አድርጓት ቆይቷል።

ዘመናዊ የከተማ ሳይንስ ከተማን እንደ ሕያው ሥርዓት ይመለከታል። አሜሪካዊቷ የከተማ አስተሳሰብ ባለሙያ ጄን ጃኮብስ ከተማ ለሰዎች እንጂ ለመኪናዎች እንደማይገነባ እና የከተማ ቦታዎች የማህበራዊ ሕይወት ማጠናከሪያ መሆን እንዳለባቸው ታስረዳለች። የዴንማርኩ የከተማ አዋቂ ጃን ጌል ደግሞ ከተሞችን "በሰው መጠን" በመቅረጽ፣ ለእግረኞች፣ ለመራመጃና ለመገናኛ ምቹ ማድረግ የልማት ዋና መለኪያ እንደሆነ ይመክራል። በተመሳሳይ የፈረንሳይ ምሁር ሄንሪ ሌፈቭር "Right to the City" በተባለው ጽንሰ-ሐሳቡ ከተማ የሁሉም ዜጎች የጋራ ቦታ መሆን እንዳለባትና ልማት ሰውን ያማከለ፣ ፍትሐዊና አካታች መሆን እንደሚገባው ያሳስባል።

ከ2010 ዓመተ ምህረት ወዲህ በአዲስ አበባ የተጀመሩት በርካታ የከተማ ልማት ሥራዎች፣ ከተማዋን ከችግር ተከተልነት ወደ ቅድመ-ዕቅድ መሪነት ለማሸጋገር የተደረጉ ጥረቶች ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ። የኮሪደር ልማት፣ የወንዝ ዳርቻ ማልማት፣ የአረንጓዴ መሠረተ ልማት፣ የአደባባይ እድሳትና የዲጂታል አገልግሎት ማስፋፋት የዚሁ ምዕራፍ አካላት ናቸው።

በከተማ ሳይንስ እይታ "ኮሪደር" ማለት የመጓጓዣ፣ የንግድ፣ የሕዝብ ክፍት ቦታና የመሠረተ ልማት የተቀናጀ አውታር ነው። በአዲስ አበባ የታየው የኮሪደር ልማት የእግረኛና የብስክሌት መንገዶችን፣ የመብራትና የውሃ ማስወገጃ አውታሮችን አቀናጅቶ የያዘ በመሆኑ ከዓለም አቀፍ የከተማ ፕላን መርሆዎች ጋር ይጣጣማል ሲሉ ብርሃኑ(ዶ/ር) ገልጸዋል።

ብርሃኑ (ዶ/ር) በቅርብ ዓመታት በመዲናዋ እየተካሄደ ያለው የኮሪደር ልማትና አጠቃላይ የከተማ ማሻሻያ ሥራዎች ከተማዋን ከነበረችበት ታሪካዊ የፕላን ስህተት በማውጣት ወደ ዓለም አቀፍ ደረጃ እያሸጋገሯት እንደሚገኙ ያብራራሉ።

እንደ ምሁሩ ገለፃ፣ ይህ እርምጃ የከተማዋን ገጽታ ከመቀየር በላይ ሳይንሳዊ የከተማ ምህንድስናን ማዕከል ያደረገ ነው። አዳዲስ የሚገነቡ ሕንፃዎች የመሬት ውስጥ የመኪና ማቆሚያ እንዲኖራቸው መገደዳቸው የትራፊክ ጥግግትን ለመቀነስ ትልቅ አስተዋፅኦ እያደረገ ሲሆን፣ የወንዞች ዳርቻ ልማትና ሰፋፊ የእግረኛ መንገዶች መገንባታቸው ደግሞ የነዋሪዎችን የመኖሪያና የጉዞ ምቾት በከፍተኛ ደረጃ አሻሽሎታል።

በሌላ በኩል፣ ለብዙ ዓመታት የቆሻሻ መጣያ ሆነው የቆዩት የከተማዋ ወንዞች በወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክት መታደሳቸው አዲስ ተስፋ ፈጥሯል። ወንዞች የከተማ ተፈጥሯዊ መሠረተ ልማት በመሆናቸው የጎርፍ አደጋን ይቀንሳሉ፣ የሙቀት መጠንን ያመጣጥናሉ፣ ለነዋሪዎችም የመዝናኛ ቦታ ይፈጥራሉ። እንዲሁም በአረንጓዴ ልማት የታዩት ጥረቶች የከተማዋን "ሳንባ" በመገንባት የአየር ጥራትን ለማሻሻልና የሙቀት ደሴት (Heat Island) ተጽዕኖን ለመቀነስ የሚረዱ ናቸው። ዲጂታል አገልግሎቶችና የኦንላይን አሠራሮች ደግሞ ከተማዋ በመረጃ የተመራ አስተዳደር ወዳለው "ስማርት ሲቲ" ለማደግ የምታደርገውን ጥረት ያመለክታሉ።

ብርሃኑ (ዶ/ር) በአጭር ጊዜ ውስጥ የተመዘገበው ይህ የከተማ ማሻሻል ውጤት ለአገሪቱ ዜጎች ብቻ ሳይሆን ለውጭ ሀገር ጎብኚዎችና ለዲፕሎማቶችም ቢሆን ከፍተኛ እርካታን የፈጠረና የኢትዮጵያን አገራዊ ገጽታ ያሳደገ ተግባር መሆኑን ያመላክታሉ።

ይሁን እንጂ የከተማ ሳይንስ እንደሚያስረዳው፣ የከተማ ፕሮጀክት በተመረቀበት ቀን አይጠናቀቅም። የጀመሩትን የልማት አቅጣጫዎች ዘላቂ ማድረግ የመጨረሻውና ዋናው ፈተና ነው። በዓለም ላይ እንደ ሲንጋፖር፣ ኮፐንሃገን፣ ኩሪቲባ እና ሴኡል ያሉ ከተሞች ስኬት የተመዘገበው በአጭር ጊዜ ፕሮጀክቶች ሳይሆን፣ በአስርተ ዓመታት በተተገበረ ተከታታይ ፖሊሲ፣ በቀጣይ ጥገና፣ በተቋማዊ ብቃትና በመረጃ በተደገፈ ውሳኔ ነው።

አዲስ አበባም የጀመረቻቸውን መልካም አጋጣሚዎች ወደ ዘላቂ ስኬት ለመቀየርና ይዛ የተነሳችውን ራዕይ ለማሳካት የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋም አካባቢ መገንባት እና ሁሉንም ያካተተ ፍትሐዊ ዕድገትን ለማረጋገጥ እያደረገች ያለው ጥረትና የተመዘገቡት ውጤቶች ይህንን የሚያመላክቱ ናቸው።

እነዚህ የተጀመሩ አዎንታዊ እርምጃዎች ዘላቂ ፍሬ እንዲያፈሩ ብርሃኑ (ዶ/ር) ሁለት ወሳኝ የወደፊት አቅጣጫዎችን ያሰምሩበታል፡- አካታችነትና ጥራት። የተጀመሩት ጥራታቸውን የጠበቁ የኮሪደር ልማቶች በአንድ አካባቢ ወይም በጥቂት ማዕከላት ብቻ ሳይወሰኑ፣ ሁሉንም የአዲስ አበባ ክፍለ ከተሞችና ሰፈሮች በጥራትና በፍጥነት ማዳረስ አለባቸው። አዲስ አበባ ይህንን ተግባር በጽናትና በከፍተኛ ሞራል በመተግበር ሁሉንም የመዲናዋን ጥጋጥጎች ለማዳረስ ጥረት እያደረገች ትገኛለች።

አዲስ አበባ በአጋጣሚ የተፈጠረች ታሪካዊ ከተማ ብትሆንም፣ የወደፊቷ ዕጣ ፈንታ ግን በአጋጣሚ ሊወሰን አይገባም። ከተሞች የሰው ልጅ ሥልጣኔ መስተዋቶች እንደመሆናቸው መጠን፣ የከተማ ልማት የሕንፃ ግንባታ ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅ የወደፊት ሕይወት የሚቀረጽበት ሳይንሳዊ፣ ማህበራዊና ሥነ-ምግባራዊ ሂደት ነውና።

አዲስ አበባ የታሪኳን ክብር ጠብቃ ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ ጤናማና ዘላቂ ከተማ መሆን የምትችለው ዘመናዊ የከተማ ምህንድስና፣ ሳይንሳዊ ፕላን፣ አረንጓዴ ኢኮኖሚና የስማርት ቴክኖሎጂ አጠቃቀም በተቀናጀና ተቋማዊ በሆነ መንገድ ሲተገበሩ ነው።

በዚህ አዋጭ መንገድም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ መዲናዋ በመጀመሯ አስደማሚ ለውጦችን እያስመዘገበች በመሆኑ በርካታ አህጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ ሽልማቶችን አግኝታለች። አሁን ከተማዋ እየተጓዘች ያለችበት መስመርም በሳይንሳዊ ዕቅድ የተመራ፣ በውጤትም የተገለጠና ተጠናክሮም የቀጠለ በመሆኑ በርግጥም አዲስ አበባ የአፍሪካ ብቻ ሳይሆን የዓለም ተወዳዳሪና ተመራጭ ከተማነቷ ከፍ ብሎ መቀጠሉ ጥርጥር የለውም ብለዋል፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቢልት ኤንድ ኢንቫይሮንመንት (Built and Environment) ኮሌጅ መምህርና ተመራማሪ ብርሃኑ ግርማ (ዶ/ር)።

# ከተሞች የአረንጓዴ ልማት ጉዳይ ስለምን ግድ አላቸው?

**በሳህሉ ብርሃኑ**

የሰው ልጆች እስካሁን ምድር ላይ በቆዩባቸው ጊዜያት ቢያንስ 70 በመቶ የሚሆነውን የምድር ክፍል ለራሳቸው ምቾት ሲሉ ቀይረውታል ይላል አንድ ጥናት። እንግሊዝ በሚገኘው 'Natural History Museum' የአካባቢ ጉዳዮች ተመራማሪው ፕሮፌሰር አንዲ ፑርቪስ እንደሚገልጹት፣ በተለይ የዓለም ሕዝብ ቁጥር በእጥፍ ከጨመረበት ከ1970ዎቹ ወዲህ ሰዎች በነፍስ ወከፍ የሚጠቀሙት ፍጆታ በ45 በመቶ በመድረሱ የሰው ልጅ በተፈጥሮ ላይ እያሳረፈው ያለው ጫና በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል።

ይሁንና ይላሉ ፕሮፌሰር አንዲ፤ ሰዎች እንደዚህ አሟጠው እየተጠቀሟት ያለችውን ምድር ለመጠበቅ እያደረጉት ያለው ጥረት የሚያስተዛዝብ ነው። በተለይም ከተሞችን በማሳያነት በመጥቀስ ከተሞች የዕድገትና የኢኮኖሚ ማዕከላት ብቻ ሳይሆኑ፣ የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖዎችና የከባቢ ብክለትን የሚጋፈጡ 'አውደ-ውጊያዎች' ስለመሆናቸው ያስረዳሉ። ለዚያም ይመስላል የዘርፉ ባለሙያዎች በከተሞች የኮንክሪት ጫካዎች ይልቅ ለአረንጓዴ መሠረተ-ልማት ቅድሚያ መስጠት የቅንጦት ሳይሆን የህልውና ጉዳይ ስለመሆኑ አበክረው የሚመክሩት።

የተባበሩት መንግሥታት የሰፈራ መርሃ ግብር (UN-Habitat) ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት ከተሞች በኮንክሪት፣ በአስፋልት እና በተሽከርካሪዎች ብዛት የተነሳ ከገጠር አካባቢዎች በበለጠ መልኩ ሙቀት ይስባሉ። በዚህም ሳቢያ የአረንጓዴ ልማት ሥራን እንደ ስትራቴጂካዊ የልማት ምሰሶ ያደረጉ ዓለም አቀፍ ከተሞች የነዋሪዎቻቸውን ጤና፣ ሥነ-ምህዳራዊ ጽናት እና ኢኮኖሚያዊ ተወዳዳሪነት ሲያጎለብቱ፣ ይህንን ቸል ያሉ ከተሞች ግን በከፍተኛ የሙቀት ተጽዕኖ፣ በጤና ቀውሶችና በሥነ-ምህዳር መራቆት እየተፈተኑ ይገኛሉ።

ጉዳዩን በንጽጽር ለማየት ይረዳን ዘንድ አዲስ አበባን ጨምሮ የተወሰኑ የዓለማችን ከተሞችን በአስረጅነት እንጥቀስ።

እንደ ሕንዳዊቷ መዲና ዴሊ እና የፓኪስታኗ የንግድ ማዕከል ካራቺ ያሉ ግዙፍ ከተሞች ለአረንጓዴ እና ሰማያዊ መሠረተ-ልማቶች ተገቢውን ትኩረት ባለመስጠታቸው ዛሬ ላይ ከፍተኛ ዋጋ እየከፈሉ ይገኛሉ። የዓለም ጤና ድርጅት (WHO) ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት፣ እነዚህ ከተሞች የተፈጥሮ ዛፎችን በመቁረጥ እና ክፍት ቦታዎችን በኮንክሪት በማጨናነቃቸው ሳቢያ ለከፋ የአየር ንብረት ተጽዕኖ ተጋልጠዋል። የተፈጥሮ ማጣሪያ የሆኑት አረንጓዴ ቦታዎች በበቂ ሁኔታ ባለመኖራቸው፣ ከተሞቹ



ፎቶ ከገፀ ድር
አዲስ አበባን ከአረንጓዴ ልማት ጋር ለማስማማት ከተሰሩ ልማቶች አንዱ

የከባድ ዝናብ አደጋዎችን መቋቋም አቅቷቸው በመሠረተ-ልማት ውድመትና በንጹሕ መጠጥ ውሃ እጦት እየተሰቃዩ ይገኛሉ። ዴሊ ከተማ በየዓመቱ በከባድ የጭስና የአየር ብክለት ትታመሳለች። የነዋሪዎቿ ጤና በተለይም የመተንፈሻ አካል ሕመም ለከፍተኛ አደጋ በመጋለጡ በከተማዋ ሕይወት ከብዷል። ካራቺ እንደዚሁ ባለፉት ዓመታት ባጋጠማት የሙቀት ማዕበል ብቻ በወባና በድርቀት (ዲሃይድሬሽን) በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ሕይወት አጥታለች።

በተቃራኒው ደግሞ እንደ ደቡብ ኮሪያዋ ዋና ከተማ ሴኡል ያሉ የዓለማችን ከተሞች በአረንጓዴ ልማት ሥራ የከተማን ትራንስፖርት ስፍራዎችና ሕንፃዎችን ወደ ውብ የተፈጥሮ ማረፊያዎች በመቀየር ታላቅ ስኬትን ያስመዘገቡ ናቸው። ሴኡል በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ በጽዳቷ ቀዳሚ ከሆኑ ከተሞች ተርታ ትመደባለች። የሴኡል ከተማ አስተዳደር ከተማዋን የበለጠ ጽዱ፣ ጤናማ እና ለአየር ንብረት ለውጥ የማትበገር ለማድረግ ባለፉት ዓመታት ሰፊ የአረንጓዴ ልማት ሥራዎችን አከናውኗል። ይህም የተፈጥሮ ወንዝን እና የሕዝብ መዝናኛ ፓርክን በመፍጠር የከተማዋን የሙቀት መጠን እንዲቀንስ እና የብዝሃ-ሕይወት መነቃቃት እንዲኖር ስለማድረጉ ዩኔስኮ ከጥቂት ዓመታት በፊት ስለከተማዋ ያወጣው መረጃ ያሳያል።

እነዚህ ዓለም አቀፋዊ ተሞክሮዎች እንደሚያሳዩት ዘላቂ የሆነ የአረንጓዴ ልማት ሥራ ለነዋሪዎች ሕልውና ወሳኝ መሆኑን ነው። አዲስ አበባም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ይህንን እውነታ በመገንዘብ በኮሪደር ልማት፣ በወንዝ ዳርቻ ልማት እና በሰፋፊ ፓርኮች ግንባታ የከተማዋን ገጽታ በመቀየር እና ነዋሪዎቿን ከንጹሕ አየር ጋር በማቀራረብ ረገድ አበረታች እና ተስፋ ሰጪ ስኬቶችን እያስመዘገበች ትገኛለች።

የአዲስ አበባ አረንጓዴ ልማት እና የኮሪደር ልማት ስኬቶች ከተማዋን ውብ፣ ጽዱ እና ለኑሮ ምቹ በማድረግ ረገድ ትልቅ ለውጥ አሳይተዋል። እነዚህ ሥራዎች ንጹሕ አየር እንዲኖር፣ የቱሪዝም እንቅስቃሴ እንዲሻሻል እና የከተማው ገጽታ እንዲቀየር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ከተማዋን ውብና ለኑሮ ተስማሚ ከማድረግ ባሻገር፣ ለነዋሪዎች ምቹ የሆኑ በርካታ አረንጓዴ የመዝናኛ ቦታዎችን ለመፍጠርም አስችሏል። በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የአዲስ አበባ ከተማ ዋና ሥራ አስኪያጅ ወንድሙ ሴታ (ኢ/ር) ከዓመታት በፊት የከተማዋ የአረንጓዴ ሽፋን ከ3 በመቶ በታች እንደነበርና ባለፉት ተከታታይ ስምንት ዓመታት በተከናወነው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ከ23 በመቶ በላይ ማደግ መቻሉን ይገልጻሉ።

የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማትም ኢትዮጵያ በተለይም አዲስ አበባ እያከናወነች ያለውን የአረንጓዴ አሻራ ሥራ አስመልክቶ በተለያየ ወቅት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። ከእነዚህም መካከል የዓለም አቀፍ አረንጓዴ ልማት ኢንስቲትዩት አንዱ ነው። ተቋሙ «Living in Harmony with Nature: Lessons from Ethiopia's Experience on Nature Based Solutions and the Green Legacy Initiative» በሚል በድህረ ገጹ ላይ ባሰፈረው ሀተታ ሌሎች ሀገራት ከኢትዮጵያ ተምረው እያበላሹት ያለውን ዓለም በፍጥነት ወደ ማከም እንዲገቡ የኢትዮጵያን ተሞክሮ በመጥቀስ አሳስቧል። የአረንጓዴ አሻራ ሥራው በተጨማሪም ኢኮ-ቱሪዝምን ለማስተዋወቅ እና ዘላቂ ልማትን ለማምጣት ያለው አበርክቶ ከፍተኛ ስለመሆኑ አስቀምጧል።

አረንጓዴ ልማት ለአንድ ከተማ ዘላቂ እድገት፣ ውበት እና ለነዋሪዎች ጤናማ ሕይወት ወሳኝ ተግባር ነው። መሬትን በአረንጓዴ ተክሎች እና በዛፎች መሸፈን ተፈጥሯዊ ሚዛንን ለመጠበቅ የሚያስችል መተኪያ የሌለው ወሳኝ እርምጃ ነው። ዛፎችን እና ተክሎችን በከተማ መሬቶች ላይ በእቅድ ማልማት አየርን ከማፅዳት ባሻገር ዘርፈ-ብዙ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የአካባቢ ጥበቃ ጥቅሞችን ያስገኛል። በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮ ሀብት አጠባበቅ ትምህርት ክፍል መምህሩ አቶ የማነ ወልደየሱስም ከዚህ ቀደም ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት እንደገለፁት አረንጓዴ ልማት ለከተሞች ዋስትና መሆኑን ነው።

አረንጓዴ አካባቢዎች ለከተማ ነዋሪዎች የአእምሮ እና አካላዊ ጤንነት መሻሻል የማይተካ አስተዋፅኦ እንዳላቸውም መምህሩ አቶ የማነ ይገልጻሉ። በዛፎች የተከበቡ ክፍት ቦታዎች፣ የመዝናኛ ፓርኮች እና የመንገድ ዳር አረንጓዴ ቦታዎች ነዋሪዎች የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ፣ እርስ በእርስ እንዲገናኙ እንዲሁም ከአእምሮ ውጥረት እንዲያገግሙ እንደሚያግዙም አስረድተዋል። አያይዘውም የአረንጓዴ ልማት ሥራ አሁን ላለው ትውልድ የኑሮ ዋስትና የሚሰጥና ለመጭው ትውልድ ደግሞ አረንጓዴ ሀገር የማስረከብ የሕልውና ጉዳይ ነው ሲሉ ገልጸውታል።

የዓለም ባንክ የከተማ ልማት እና የአካባቢ ጥበቃ ተቋም ሪፖርቶች እንደሚገልጹት አረንጓዴ ቦታዎች (ፓርኮች፣ ዛፎች እና የተፈጥሮ ወንዞች) የከተሞችን የሙቀት መጠን በእጅጉ በማቀዝቀዝ ከተማዋ ለኑሮ ምቹ እንድትሆን ያደርጋሉ። የኮንክሪት ንጣፎች የዝናብ ውሃ ወደ መሬት እንዳይሰርግ በማድረጋቸው ከተሞች በቀላሉ ለጎርፍ አደጋ የተጋለጡ ናቸው። የአረንጓዴ ልማቶች እና ተፈጥሯዊ የውሃ ማስተላለፊያዎች (እንደ ወንዝ ዳርቻዎች ልማት) ውሃው በመሬት ውስጥ እንዲጣራ እና የጎርፍ አደጋን ለመቀነስ ወሳኝ ሚና አላቸው።

ከተሞች በሚፈጥሩት ከፍተኛ ድምፅ፣ ግርግር እና ጭንቀት ውስጥ የሚኖሩ ማህበረሰቦች ከተፈጥሮ ጋር የሚገናኙበት ክፍት ቦታዎችን ይፈልጋሉ። ፓርኮች እና አረንጓዴ መንገዶች ሰዎች በእግር እንዲዘዋወሩ፣ ስፖርት እንዲሠሩ እና የአእምሮ እረፍት እንዲያገኙ በማድረግ የሕብረተሰቡን ጤና ይጠብቃሉ። የአረንጓዴ ልማት ሥራ ለከተሞች አንገብጋቢ የሆነውም ለዚሁ ነው።

# በዘመናት የፀና ድል

**በመለሰ ተሰጋ**

የአንድ ሀገር ታሪክ የሚለካው በድል ብቻ አይደለም፤ በፈተናዎች ውስጥ ማንነቷን በጠበቀችበት ጀግንነት፣ በጥበቧ እና በአንድነቷ ብርቱ ክንድ ጭምር ነው። ሀገር የምትለካው በእነዚህ ነው። አዎ! ኢትዮጵያ በታሪኳ ውስጥ የውጭ ወረራዎችን፣ የፖለቲካ ጫናዎችን እና የክልላዊ ፉክክሮችን ተጋፍጣ መቆም የቻለችውም ከላይ ያስቀመጥናቸውን መለኪያዎች በማሟላት ስለመሆኑ የታሪክ ምሁራን ይመሰክራሉ፡፡

የኢትዮ-አረብ ግንኙነት እና የታሪክ ተመራማሪው ፕሮፌሰር አደም ካሚል በዚህ ሀሳብ ይስማማሉ፡፡ እንደ ፕሮፌሰሩ ገለፃ፣ የኢትዮጵያ ጽናት የተገነባው በአንድ ዘመን ሳይሆን በብዙ ትውልዶች ተሞክሮ እና ቅብብሎሽ ነው። ይህ ጽናት በጦር ሜዳ ብቻ የሚለካ አይደለም፤ ይልቅ በዲፕሎማሲ፣ በባህልና በማንነት ጥበቃ ውስጥም ከፍ ብሎ ታይቷል፡፡

ኢትዮጵያ በቀይ ባህር እና በዙሪያዎቿ በነበሯት ወደቦች በኩራት በሚንቀሳቀሱት መርከቦቿ በጥንት ዘመን ከዓለም አስፈላጊ የንግድና የሥልጣኔ ማዕከላት አንዷ ነበረች። ወዲህ ደግሞ ከቀይ ባህርና ዓባይ ወንዝ ጋር በተያያዘ ወዝና ለዛ ያላቸው ወዳጆቿ፤ ጥቃቅን ስንጥቆችን እየፈለጉ ሰላሟን ለማደፍረስ፤ ልማቷንም ለማጨለም እንቅልፍ የማይተኙ ጠላቶችንም በተባበረ ብርቱ ክንዷ እየመከተችና እያሳፈረች፣ ወዳጆቿንም እያበዛች በታሪክ ምዕራፍ ላይ በከፍታ ቀጥላለች፡፡

በታሪክ መንገድ ላይ ወደ ጥንቱ ስንጓዝ ታላቁን የዓድዋ ድል እናገኛለን፡፡ 1888 ዓመተ ምህረት የኢትዮጵያን ገናናነት በዓለም አደባባይ ከፍ አድርጎ የፃፈ ታላቅ ድል ነው፤ ዓድዋ፡፡ የዓድዋ ጦርነት በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ታሪክ ውስጥም ታላቅ ሥፍራን ይዟል። በዚህ ጦርነት የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነትና የነፃነት ስሜት የድሉ ዋና መሠረቶች ነበሩ፤ ዛሬም ናቸው፡፡

ፕሮፌሰር አደም ካሚል እንደሚሉት የኢትዮጵያ ታሪክ የሚያሳየው የታሪካዊ ጠላቶቿ ሴራ ምን ያህል ውስብስብና በየዘመናቱ የነበረ ከመሆኑ በላይ የኢትዮጵያውያንን ብርቱ ክንድ ነው።

ለአብነትም በኢትዮጵያ ታሪክ እስካሁን ከጥንት እስከ ዛሬ ባለው ሁኔታ ግብፅ ኢትዮጵያን በጠላትነት የመፈረጅ እንቅስቃሴ ታደርጋለች፤ ከዛም አልፎ ጦር እስከማዝመት ድረስ የደረሰችበት ሁኔታም ምክንያት አለው። በኢትዮጵያውያን ጀግኖች ብርቱ ክንድ እየተለበለበች ተመልሳለች እንጂ፡፡

ግብፅ፣ የኢትዮጵያን ጠላቶች የውስጥም የውጭንም በማደራጀት ደግሞ ብዙ ነገር ስትሰራ፣ ስታተራምስ፣ ጥረት ስታደርግ ደግሞ ስትሞክር እናውቃለን፤ ሲሳካላት ግን አናይም። “ለመሆኑ ግብፅና መሰል የኢትዮጵያ ጠላቶች ፍላጎታቸው ያልተሳካበት ምስጢር ምንድን ነው?” ለሚለው ጥያቄ ፕሮፌሰር አደም መልስ አላቸው፡፡



ግራፊክስ - በእዮብ ተፈራ

ኢትዮጵያውያን ከጥንት እስከ ዛሬ አንድነታቸውን ጠብቀው የጠላትን ሴራ እያከሸፉ ታላላቅ ድሎችን አስመዝግበዋል

“የኛ ጉዳይ ከጥንት ጀምሮ በተለይ ግብፆች በሚዲያው ዓለም በጣም የታወቁ ናቸው። ከዚህ አንፃር አልጀዚራን በምሳሌነት ብንጠቅስ በማኔጅመንት ደረጃ እነሱ አሉበት፤ ኤምቢሲ፣ ቢቢሲ፣ ሞንቴ ካርሎ፣ ሁራም ብትሄድ ከሚዲያዎቹ ጀርባ እነሱ አሉ፡፡ ቢያንስ ቢያንስ ግብፅ በውጭ ሀገር ወደ 800 ሺህ የሚሆኑ ትውልደ ግብፃውያን ስደተኞች አሏት፣ 10 ሚሊዮን ሰራተኞች በውጭ ይኖራሉ፣ ትውልደ ግብፃውያን የሆኑ 150 ሺህ ሀኪሞች በአውሮፓ ይገኛሉ፡፡

ይህንን ተከትሎም እነዚህ በርካታ እና በተለያዩ መስኮች ያሉ ግብፃውያን ለሀገራቸው መንግሥትና የህልውና ጥያቄ በፅናት የሚቆሙ ናቸው፡፡ ሁልጊዜም መሪዎቻቸውን በመከተል ኢትዮጵያን በጠላትነት ይፈርጇታል፡፡ በሀገራቸው ጉዳይ ላይ ምንም ሁን ምንም አንድ አቋም አላቸው፡፡ ለምሳሌ ዓባይን በተመለከተ ግብፆች በእነሱ አመለካከት እና ግምት ወይም አረዳድ ወንዙ ከሰማይ የመጣና ለግብፅ የተፈጠረ ብለው ነው የሚያምኑት። የኢትዮጵያ እራት መሆኑን፣ ከኢትዮጵያ የሚመጣ መሆኑን በምንም አይነት ግንዛቤ እንዲያዝ አይፈልጉም፣ እውነቱ እንዲታወቅም አይፈልጉም።”

እንደ ፕሮፌሰር አደም ካሚል ማብራሪያ የግብፅ እመቤት አንድ ህፃን ልጅ ወልዳ ስታጠባ ለህፃኑ ልጅ የምትመግበው “ወተቱን፣ ጡቷን ይሄ የዓባይ ውሃ ውጤት ነው” የምትለው። የግብፃውያን የውትድርና ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ቃለ መሃላ ሲፈፅሙ “ለግብፅ እሞታለሁ” አይደለም፣ “ለዓባይ እሞታለሁ” በማለት ቃለ መሃላ እስከመፈፀም የደረሱበት ዘመንም እንደነበር ያወሳሉ፡፡ ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ፣ በዓድዋ የዓለምን የእኩልነት ሚዛን ያስተካከለ ድልን የተጎናፀፈች፣ የጥቁሮች መብትን ያስከበረች፣ ውብና ውድ የተፈጥሮ ፀጋን የታደለች ድንቅ ታሪክና ባህል ያላቸው ከ130 ሚሊዮን በላይ ህዝብ ያላት ሀገር ናት።

ከተማዋ አዲስ አበባ የአፍሪካ ዋና ከተማ ነች። ከኒውዮርክ ቀጥሎ የኮንፈረንስ ስብሰባዎች የሚካሄዱባት በዓለም ሁለተኛዋ ከተማ አዲስ አበባ ናት። በጥቁሮች ዘንድ እኛ ልዩ ክብር አለን፤ በሙስሊሙ ዓለም ደግሞ ነብዩ መሐመድ በዛች ከባድ ሰዓት ላይ ተከታዮቻቸው ለችግር ሲጋለጡ “ፍትህ፣ ሀቅ፣ እውነት ያለባት ሀገር ሂዱ ተጠለሉ” ብለው ነው የላኳቸው፤ እናም ግብፆች ይህንን ያውቃሉ፡፡

ኢትዮጵያ ማለት በ1945 እ.ኤ.አ የተባበሩት መንግስታት ሲመሰረት ሳንፍራንሲስኮ ላይ መሰረት የጣለች፣ የአፍሪካ ህብረት በ1963 እ.ኤ.አ ሲመሰረት አሻራዋን ያስቀመጠች ናት፡፡ “ግን ኢትዮጵያውያን ይሄን ታላቅነቷን፣ ይህን ሀቅ ሁሉ ያውቁላታል ወይ? ግብፅንና መሰል ጠላቶቻቸውን ሴራ ተረድተውታል ወይ?” የሚለው ትልቅ ጉዳይ ነው ይላሉ ፕሮፌሰር አደም ካሚል፡፡

“ለምሳሌ በመሐመድ አሊ ፓሻ ዘመን የመጣን እንደሆነ ቴዎድሮስን ያስገደለው ማን ነው? ያን ጊዜ ግብፅ በኛ ውሃ የተመረተ ጥጥ ታመርት ነበር፡፡ እናም በቴዎድሮስ ዘመን ከእንግሊዝ ጋር በመነጋገር 'ኢትዮጵያን እናዳክም' ሲሉ ምፅዋ ላይ ወርደው ከዛ መቅደላ መጥተው ቴዎድሮስን ለህልፈት ዳረጉት፤ የግብፆች ሴራ አለ በስተጀርባ። ከዛ ቀጥሎ ወደ ፋውዚ ዘግሉል ዘመን እንምጣ፣ እ.ኤ.አ በ1875 እና 1876 ዘመቻ አካሂደዋል፤ ይሁን እንጂ በኢትዮጵያውያን አንድነትና ብርቱ ክንድ ወደ 20 ሺህ ሰራዊት ከስሮ ተመለሰ፡፡”

ከአልናስር እስከ አንዋር ሳዳት፤ ከሁስኒ ሙባረክ እስከ ሞርሲ ዘመን የታሪክ ድርሳናትን ብናገላብጥ የግብፅ ሴራ ከፍ ብሎ ይታያል፡፡

በፕሬዝደንት ሞርሲ ዘመን በተካሄደ አስቸኳይ ስብሰባ በዚህ ስብሰባም በኢትዮጵያ ላይ እንደለመዱት የተንኮል ዕቅድ መንደፋቸውን የገለፁት ፕሮፌሰር አደም ካሚል፣ ለአብነት ኤርትራን ከኢትዮጵያ በመለየት በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት እንድትከፍት ማድረግ፣ አላሙዲ የሚባል መሰረቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ የሳዑዲ ዜግነት ያለው ከሳዑዲዎች ጋር ተነጋግረን ከኢትዮጵያ እንዲወጣ ማድረግ፣ ጅቡቲ የወደብ አገልግሎት እየሰጠች ስለሆነ በአረብ ሊግ አባልነቷ በኩል በመግባት ለኢትዮጵያ የምትሰጠውን አገልግሎት እንዲቋረጥ ማድረግ እና ለኦጋዴን ነፃ አውጪዎች ትጥቅ ሰጥተን ጦር በኢትዮጵያ ላይ ይክፈቱ እስከማለት የደረሰ በተግባርም የተገለፀ ሴራ መደረጉን እና ሙርሲም ዕቅዳቸው እንደ ጉም በኖ፤ ተኖ ሁለት ወር ሳይቆዩ ወደ እስር ቤት ተወረወሩ፤ በዛውም ህይወታቸው አለፈ ይላሉ የኢትዮ-አረብ ግንኙነት እና የታሪክ ተመራማሪው ፕሮፌሰር አደም ካሚል፡፡

የኢትዮጵያን ጉዳይ በተለያየ ጊዜ የግብፅ ባለስልጣኖች የስልጣን ማራዘሚያ አጀንዳቸው አድርገውታል የሚሉት ፕሮፌሰሩ ዋናው ግን የዓባይ ውሃ ነው፤ የዓለም አቀፍ ህግጋትን፣ የታሪክ እውነታን እና ፍትሐዊ የተጠቃሚነት መርህን የያዘችው ኢትዮጵያ የታሪካዊ ጠላቶቿን ሴራ እየበጣጠሰች ግድቡን በተከታታይ ሞልታ ጨረሰች፡፡

ስለዚህ አሁን ተስፋ ቆርጠዋል፤ ግን በተለያየ ጊዜ አሁንም ኢትዮጵያን የማዳከም ሴራቸውን ቀጥለዋል፡፡ ለአብነትም በተለይ ምርጫ እና ክረምቱ በቀረበ ቁጥር የግብፅ ጩኸት ይበዛል። እያንዳንዷ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚፈጠር ኩርፊያ እና ጠላት በስተጀርባ ከኤርትራ መገንጠልም ሆነ ጦርነት በስተጀርባ የግብፅ እጆች አሉ፡፡ የሰሜኑም ጦርነት ከዚህ የራቀ አይደለም ይላሉ ፕሮፌሰሩ፡፡

ግብፆች የባህር በር ፍላጎታችን አሁን ሲነሳ ደግሞ ሴራቸውን ቀጥለዋል፡፡ ለአብነትም ኢትዮጵያ ፍትሐዊ፣ ታሪካዊና ትክክለኛ ጥያቄ እንዲደናቀፍ ከሱዳን እስከ ደቡብ ሱዳን፣ ከኡጋንዳ እስከ ጅቡቲ ተንቀሳቅሰው በኢትዮጵያ ላይ ክልከላ ለማድረግ ጥረት አድርገዋል። ግን አልተሳካላቸውም፡፡በቀጣይም አይሳካላቸውም ይላሉ ፕሮፌሰር አደም ካሚል፤ ግን ዛሬም እንደ ትላንቱ የሀገርን ሰላም እና አንድነት ማስጠበቅ አለብን፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ የጥቁሮችን መብት ያስከበረ የዓድዋ ታሪክ ባለቤት፣ አሁንም የአህጉሪቱን ግዙፍ ግድብ በራሱ ገንዘብ፣ ጉልበትና እውቀት በዓባይ ወንዝ ላይ እውን ያደረገ ህዝብ ነው፡፡ አሁንም ይህንን የሀገርን አንድነት፣ ልማትና ከፍታ አጠናክረን ልንቀጥል ይገባል ብለዋል።

ኢኮኖሚ

# የመዲናዋ ቱሪዝም ጌጥ

## • አረንጓዴ አሻራ ከቱሪዝም ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት እንዳለው ተጠቁሟል

**በስንታየሁ ምትኩ**

ዳውድ አኩንድዛዳ በዓለም ዙሪያ በመዘዋወር የሀገራትን ባህል፣ ታሪክ፣ ምግብና የሰዎችን የዕለት ተዕለት ኑሮ በካሜራው እየቀረፀ የሚያሰራጭ ታዋቂ ይዘት ፈጣሪ ነው። ፌስቡክ፣ ቲክቶክ እና ዩትዩብን ጨምሮ በተለያዩ የማህበራዊ ትስስር ገፆቹ ከ3 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ተከታዮች አሉት፡፡ ይህ ሰው በቅርቡ አዲስ አበባን የጎበኘ ሲሆን ያስደነቁትን ነገሮች በሚዲያው አጋርቷል፡፡

ዳውድ አዲስ አበባን "እስቲ ይህቺ ከተማ እንዴት ያለች ውብ እንደሆነች ተመልከቷት፤ ዱባይ ውስጥ እንዳለሁ ይሰማኛል፤ ግን ከእሷ የተሻለ የአየር ሁኔታ አላት" በማለት ሲያደንቅ ታይቷል። በቅርቡ የተመረቀውን የቀበና የወንዝ ዳርቻ ፕሮጀክት ሲጎበኝም፤ አዲስ አበባ በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በዓለም ከሚገኙ አረንጓዴ ከተሞች አንዷ እንደሆነች በአድናቆት መስክሯል። በርግጥ ዳውድ ብቻ አይደለም፤ በመዲናዋ ውበት፣ ፅዳትና ሁለንተናዊ ለውጥ በመደነቅ የሚናገሩና የሚፅፉ በርካቶች ናቸው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ የተፋሰስና አረንጓዴ ልማት ዳይሬክተር ወይዘሮ ስንታየሁ መንግስቱ እንደገለጹት፣ አዲስ አበባ ከሀገራዊ ለውጡ (2010 ዓ.ም) በፊት የነበራት ገጽታ ስሟንና ግብሯን የሚመጥን አልነበረም፤ በሁለንተናዊ መልኩም የተጎሳቀለ ገፅታ ነበራት። የተፈጥሮ ሀብቷ፣ በተለይም የደን ሽፋኗ ተመናምኖ ከ2 ነጥብ 8 በመቶ አይበልጥም ነበር።

ይህ የደን ሽፋንና አረንጓዴ ልማት እንዲጨምርና እንዲያንሰራራ ካደረጉ ትላልቅ ስራዎች መካከል የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ዋነኛው ነው። ከተማዋ ባለፉት ስምንት ተከታታይ ዓመታት በርካታ ተግባራትን ስታከናውን ቆይታለች። ከ90 ሚሊዮን በላይ የጥላ፣ የውበትና የፍራፍሬ ችግኞችን ተክላለች። የከተማ አስተዳደሩ የ2018 በጀት ዓመት እቅድ አፈጻጸም በቀረበበት ወቅት የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ በ2010 ዓ.ም 2 ነጥብ 8 በመቶ ብቻ የነበረው የመዲናዋ አረንጓዴ ሽፋን አሁን ላይ 24 በመቶ መድረሱን ተናግረዋል፡፡

ዘንድሮም በመዲናዋ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር 6 ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ድረስ 7 ሚሊዮን 117 ሺህ 99 ችግኞች ተተክለዋል። ከዚህም ውስጥ በሐምሌ 27 ቀን 2018 ዓ.ም በተካሄደው የአንድ ጀምበር የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ብቻ 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ችግኞችን መትከል ተችሏል።



ግራፊክስ፡- በእዮብ ተፈራ
አረንጓዴ አሻራ ለከተማዋ ቱሪዝም ጉልህ አስተዋፅኦ እያበረከተ ነው

### አረንጓዴ አሻራ እና ቱሪዝም

የአረንጓዴ አሻራ ወይም ችግኝ መትከል ከቱሪዝም ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት እንዳለው የቱሪዝም መምህርና ተመራማሪው አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር) ለዝግጅት ክፍላችን ይገልጻሉ፡፡ ቱሪስቶችን ከአንድ አካባቢ ወይም ሀገር ወደ ሌላ የሚንቀሳቀሱት የተለያዩ ዓላማዎችን በመሰነቅ ነው። ከእነዚህ ውስጥ አንደኛው የተፈጥሮ መስህቦችን፣ አዕዋፋትንና የዱር እንስሳትን ለማየት ሊመጡ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፡- በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ከ6 ሺህ በላይ የሚሆኑ የዕፅዋት ዝርያዎች ይገኛሉ፡፡ ዕፅዋትን፣ አዕዋፋትንና የዱር እንስሳትን ለመመልከት የሚመጡት፤ አረንጓዴ አካባቢዎች በተበራከቱ ቁጥር ብዙም ሳይርቁ በቀላሉ በአዲስ አበባና ዙሪያ እነዚህን የሚያዩበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

አዲስ አበባ እንደ ስሟ ውብ እና አበባ መሆኗን ቱሪስቶች እንዲረዱ ገና ከአየር ማረፊያ ሲወርዱ አበባ በመስጠት ብንቀበላቸው፣ የከተማዋን መልካም ገፅታ የበለጠ መገንባት ይቻላል የሚል እምነት እንዳላቸው አያሌው (ዶ/ር) ተናግረዋል፡፡ እንደ ባለሙያው ገለጻ፣ ቱሪስቶች ከተፈጥሮ ጋር በተወዳጁ መዝናኛ ስፍራዎች መንፈሳቸውን እያደሱ የእረፍት ጊዜያቸውን የሚያሳልፉባቸው እንደ አንድነትና እንጦጦ ፓርክ፣ ወዳጅነት አደባባይ... ለምተዋል፡፡ የውጭ ሀገር ዜጎች ለስብሰባና ለተለያየ ዓላማ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ፣ በሚኖራቸው ትርፍ ጊዜ በአረንጓዴ ዕፅዋት የተሸፈኑና ፅዱ የሆኑ የመስህብ ስፍራዎችንና መናፈሻዎችን እንዲጎበኙ አስቀድሞ ማሳወቅና ተንቀሳቅሰው እንዲጎበኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህን አድርገው ሲመለሱ 'አዲስ አበባ የዲፕሎማሲ ብቻ ሳይሆን የአረንጓዴ ማዕከል ሆናለች' ብለው መስክረው ለሌሎች እንዲነግሩ ጉብኝታቸው አስደሳች ማድረግ ይገባል፡፡

በአዲስ አበባ የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ የተፋሰስና አረንጓዴ ልማት ዳይሬክተሯ ወይዘሮ ስንታየሁ እንደገለፁት፣ አዲስ አበባን እንደ ስሟ አዲስ፣ ውብ እና አበባ እንድትሆንና በአረንጓዴ ዕፅዋት የተሸፈነች ከተማ ለማድረግ የተከናወኑ የተቀናጁ ሥራዎች ውጤት አስገኝተዋል። የከተማዋን አረንጓዴ ሽፋን በማሳደግ ረገድ የተገኘው ውጤት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተቀመጠው መስፈርት (የአንድ ከተማ የአረንጓዴ ሽፋን ከጠቅላላ ከከተማው ስፋት 30 በመቶ መሆን እንዳለበት ከተቀመጠው) ጋር እንድትቀራረብ አስችሏታል፡፡ የተራቆቱ አካባቢዎች አረንጓዴ ለብሰዋል፤ የነጠፉ ወንዞች ማንሰራራት ጀምረዋል።

የአዲስ አበባ የአረንጓዴ ሽፋን መጨመር፣ ንፁህና ውብ አካባቢዎች መፈጠር ከተማዋ በሀገር ውስጥና በውጭ ቱሪስቶች መዳረሻ እንድትሆን እያደረጋት ይገኛል፡፡ ወይዘሮ ስንታየሁ እንደገለፁት፣ ከኮሪደር እና ከወንዝ ዳርቻ ማልማት ጋር ተያይዞ የተፈጠሩ አረንጓዴ መናፈሻዎች የከተማዋን ገጽታ በእጅጉ ለውጠውታል። ቀድሞ በቆሻሻ የተሞሉ፣ የተረሱ የወንዝ ዳርቻዎች በአረንጓዴ መናፈሻዎችና በመዝናኛ ስፍራዎች ተተክተዋል። የእግረኛ መንገዶች፣ የብስክሌት መስመሮች፣ የተለያዩ አገልግሎቶችን አሟልተው እንዲገነቡ መደረጋቸው ለነዋሪዎች ብቻ ሳይሆን ለጎብኚዎችም የሚስብ መዳረሻ ሆነዋል፡፡ እነዚህ አካባቢዎች ንፁህ፣ አረንጓዴና ውብ ገፅታን ተላብሰው ሰዎች የሚዝናኑባቸውና መንፈሳቸውን የሚያድሱባቸው አካባቢዎች ሆነዋል፡፡

ተራራማ አካባቢዎች፣ መሀል ከተማ፣ መዝናኛ ስፍራዎች፣ የመንገድ አካፋዮችና ክፍት ቦታዎች አረንጓዴ መልባሳቸው ሙቀትን በመቀነስ ሚዛኑን የጠበቀ የአየር ንብረት እንዲኖር አዎንታዊ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

በአፍሪካ ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ዘገባዎችን በማቅረብ የሚታወቀው "ዘ አፍሪካ ሪፖርት" የተሰኘው መገናኛ ብዙሃን ባደረገው ጥናት በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2025 በአፍሪካ በንፁህና ቀዳሚ ከሆኑ አስር የአፍሪካ ከተሞች አዲስ አበባ አንዷ እንደሆነች መግለጹ ይታወሳል፡፡ ከተማዋ ይህንን አጠናክራ መቀጠሏ ከዚህም በበለጠ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላትን ተወዳዳሪነት እንደሚያሳድገው ወይዘሮ ስንታየሁ አስረድተዋል፡፡

በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አነሳሽነት በአዲስ አበባ በተከናወነው የ"ገበታ ለሸገር" ፕሮጀክት እንደ አንድነትና እንጦጦ ፓርኮች፣ ወዳጅነት አደባባይ ያሉ መስህቦች እንዲኖራት እንዲሁም በኮሪደር ልማትና በወንዝ ዳርቻ ልማት አረንጓዴ፣ ውብና ፅዱ በመሆን በቱሪስቶች ዘንድ መዳረሻ እንድትሆን አድርጓታል፡፡ የአረንጓዴ ልማትን በማቀናጀት በተሰሩት በእነዚህ ፕሮጀክቶች የአዲስ አበባ የቆሸሸ ገፅታ ተቀይሯል፡፡ የኮንፈረንስ እና የስብሰባ ቱሪዝም ማዕከል (MICE) እየሆነች መጥታለች፡፡

የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ የ2018 በጀት ዓመት የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት እንደገለጹት፣ በከተማዋ በበጀት ዓመቱ 221 አህጉር እና ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ተካሂደዋል፡፡ በ2017 በጀት ዓመት 150 ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ስብሰባዎች ተካሂደው እንደነበርም ይታወሳል፡፡

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የ2017 ዓ.ም የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ባስጀመሩበት ወቅት የተናገሩት ንግግርም ይህንን ሀሳብ ያጠናክራል፡፡ የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ለኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ትሩፋቶችን እያመጣ እንደሆነ ጠቁመው፤ ለአብነት ቱሪዝምን ብናነሳ ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡት አንድም ውብ የሆነውን መልክዓ ምድሯን ለማየት እና ንጹህ፣ ምቹና ተስማሚ በሆነው የአየር ንብረቷ በመማረክ ነው፡፡ አረንጓዴ አሻራ ኢትዮጵያ በኮንፈረንስ ቱሪዝም ማዕከልነት ተመራጭ እንድትሆን የማይተካ ሚና መጫወቱን ገልጸዋል፡፡

የቱሪዝም መምህርና ተመራማሪው አያሌው (ዶ/ር) እንደሚሉት፣ የአዲስ አበባ አረንጓዴና ፅዱ መሆን የኮንፈረንስ ቱሪዝም መዳረሻነቷን ለማሳደግ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ለኮንፈረንስ ቱሪዝም ወደ ከተማዋ የሚመጡ እንግዶች ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ ሲንቀሳቀሱ፣ የአዲስ አበባን አረንጓዴነትና ፅዱነት ሊመለከቱ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን አሁን የተሰሩት መናፈሻዎች በእግርና በብስክሌት እየተንቀሳቀሱ መንፈሳቸውን የሚያድሱበት እድል ስለፈጠሩ፣ እንግዶች ወደ ከተማዋ ሲመጡ ጉብኝት እንዲኖራቸው አስቀድሞ ፕሮግራም እንዲይዙ ማድረግ ይገባል፡፡

በአረንጓዴ አሻራ አዲስ አበባን አረንጓዴ የማልበስ ስራ ከስነ ምህዳር ቱሪዝም፣ ከአረንጓዴ ቱሪዝም፣ ቀጣይነት ያለው ቱሪዝም (sustainable tourism) ጋር የሚዛመድና የተቀናጀ እንደሆነ አያሌው (ዶር) ያነሳሉ፡፡ በቅርብ ጊዜ ብቅ ያሉት እነዚህ የቱሪዝም ዓይነቶች የካርቦን ልቀትን፣ የውሃ እና የኃይል አጠቃቀምን በመቀነስ እንዲሁም ቆሻሻን በአግባቡ በማስወገድ ላይ ያተኩራሉ። እፅዋትን፣ የዱር እንስሳትንና ተፈጥሯዊ መልክዓ ምድሮችን እየጠበቁ ለአካባቢው ማህበረሰብ ከብክለት የፀዱ የሥራ ዕድሎችን ይፈጥራሉ። ዋና ግባቸውም ተፈጥሮ ሳይጎዳ በኃላፊነት ስሜት ለቀጣዩ ትውልድ በአደራ ማስተላለፍ ነው።

በአዲስ አበባ ባለፉት ዓመታት ከተከናወኑት ሰፋፊ ሥራዎች አረንጓዴ አሻራ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶታል። በዚህም የከተማዋን የደን ሽፋን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ፤ ንጹህ፣ ውብ እና ለአየር ንብረት ለውጥ የማትበገር የቱሪስት መዳረሻ ማድረግ ተችሏል።

አዲስ አበባ አሁን እያደረገች ባለው ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ በዓለም አቀፍ ደረጃ ጭምር እውቅናን እንድታገኝ አስችሏታል። በቀጣይም ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ያለውን የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር አጠናክሮ በማስቀጠል ለነዋሪዎችና ለጎብኚዎች ምቹ ማድረግ ይገባል እንላለን።

## ወሳኙ . . . ከገጽ 1 የዞረ

በአፍሪካና በዓለም እውቅናን አትርፋለች። ያላት ፀጋዎች ከሰፊው የሰው ሀይሏ ጋር ተዳምሮ ከራሷ አልፎ ለሌሎችም መትረፍ የሚያስችል እምቅ አቅም ያላት መሆኑን ያሳያል፡፡

ሆኖም ዘላቂ ሰላም፣ ቀጣይነት ያለው ልማትንና ዴሞክራሲን በማረጋገጥ ረገድ መሄድ በሚገባት ልክ ወደፊት አልተራመደችም፡፡ በተለያዩ ጊዜያት ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለማሸጋገርና ዘላቂ ሰላም ለማምጣት የሚያስችሉ እድሎች ቢያጋጥሟትም፤ በአግባቡ መጠቀም ስላልተቻለ ባክነው ቀርተዋል፡፡

ፕሮፌሰር ዶናልድ ሌቪን፤ "የኢትዮጵያ የባከኑ እድሎች" (Ethiopia's Missed Chances) በሚለው መፅሀፋቸው እነዚህን ዕድሎች ዘርዝረዋል። በ1953 ዓ.ም የዘውዳዊ አገዛዝ በህዝብ ላይ ያደርስ የነበረውን በደል በመቃወም በብርጋዴር ጀነራል መንግስቱ ንዋይ፣ ግርማሜ ንዋይና ሌተናል ኮሌኔል ወርቅነህ ገበየሁ መሪነት የተደረገው የለውጥ ሙከራ፣ የ1966 ዓ.ም የልጅ እንዳልካቸው መኮንን የሪፎርም ጥረት፣ በ1966 ዓ.ም ንጉሳዊ ስርዓትን ያስወገደው አብዮት፣ በ1983 ዓ.ም ደርግ የተወገደበትና የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) የተተካበት እና በ1997 ዓ.ም ጠንካራ ፉክክር የተደረገበት ሀገር አቀፍ ምርጫ ኢትዮጵያን ወደ ዴሞክራሲ፣ ዘላቂ ሰላምና ልማት ሊወስዱ ይችሉ የነበሩ ያመለጡ ዕድሎች ናቸው፡፡

እነዚህ እድሎች መባከናቸው ኢትዮጵያ በግጭት አዙሪት ውስጥ እንድትዳክር አድርገዋታል፡፡ የፖለቲካ ሳይንስ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ምሁሩ መኮንን አለሸኝ (ዶ/ር) ኢትዮጵያ በግጭት ውስጥ እንድትቆይ ያደረጉ ችግሮች በርካታ መሆናቸውን ለዝግጅት ክፍላችን አብራርተዋል፡፡ የመንግስታት አመሰራረት ታሪክ መቻቻልን መሰረት ያደረገ አለመሆኑ፣ በሀገር ግንባታ ሂደት መሰራት ያለባቸው ስራዎች በወቅቱ አለመሰራታቸው፣ ጠንካራ የዴሞክራሲ ተቋማት አለመኖራቸው (ነጻ የዳኝነት አካል፣ ፓርላማ፣ የምርጫ ተቋማትና የፖለቲካ ፓርቲዎችን ጨምሮ የሚጠበቅባቸውን ሚና መወጣት የሚችሉበት አቅም አለመገንባታቸው) የሚያጋጥሙ ግጭቶች እንዳይፈቱና እየተወሳሰቡ እንዲመጡ አድርጓል፡፡

በአንድ ሀገር ውስጥ ወሳኝ ሚና የሚጫወቱት ሊሂቃን 'የእኔ ሀሳብ ብቻ ነው መሰማት ያለበት' የሚል ግትርነት፣ በህገ መንግስትና የፌዴራል ስርዓት አወቃቀር ላይ ያሉ ውዝግቦች፣ በሀብት አጠቃቀም (መሬት) ላይ ያለው ውድድርና ፉክክር የግጭት ምክንያቶች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ችግሮችን በሀይል ለመፍታት መሞከር፣ ባህላዊ የግጭት



ፎቶ፡- ከገፀ ድር

ሀገራዊ ምክክሩ ለዛሬው ብቻም ሳይሆን ለቀጣይ ትውልድም ዘርፈ ብዙ ትሩፋት ይዞ የመጣ ወርቃማ ዕድል ነው

አፈታት ስርዓቶች መዳከምና ጠንካራ የግጭት አፈታት ስርዓት አለመኖር፣ በፖለቲካ ሀይሎች መካከል መተማመን አለመኖር፣ በታሪክ የሚታይ ብሶት፣ የሚዲያ ዋልታ ረገጥነት፣ የውጭ ሀይሎች ተፅዕኖ ኢትዮጵያ ከግጭት አዙሪት እንዳትወጣ ያደረጉ ተጠቃሽ ምክንያቶች እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡

ከአራት ዓመት በፊትም መንግስት ለዘመናት ሲያጨቃጭቁና ሲያጋድሉ የነበሩ እና የአለመግባባት ምክንያት የሆኑ መሰረታዊ ችግሮችን በምክክር ለመፍታት ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን እንዲቋቋም ተነሳሽነቱን ወስዷል፡፡ በአሁኑ ወቅትም በኮሚሽኑ አስተባባሪነት የአለመግባባትና ቅራኔ ምክንያት በሆኑ ጉዳዮች ላይ ከመላው ሀገሪቱ የተሰባሰቡ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን የወከሉ 4 ሺህ ሰዎች እየተመካከሩ ይገኛሉ፡፡

በአዲስ አበባ ፈረንሳይ ሌጋሲዮን አካባቢ ነዋሪ የሆነው ወጣት እዝራ ዘቱሱኤል፣ ይህ የምክክር ሂደት ውጤታማ እንዲሆን ሁሉም ዜጋ ሊደግፈው እንደሚገባ ይናገራል። በሀገራችን አለመግባባቶችን በሽምግልናና እርቅ የመፍታት የቆየ ባህል ቢኖርም እንደ ሀገር ያጋጠሙትን ችግሮች ለመፍታት ገለልተኛ ተቋም ተቋቁሞ ችግሮችን በምክክር ለመፍታት የተወሰደው እርምጃ የሚደነቅ ነው። መሳሪያ ታጥቀው ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ሀይሎች ጭምር ሰላማዊውን መንገድ መርጠው የመጡበት ሁኔታ ተስፋ ሰጪ መሆኑን ይገልጻል።

የሀገርን ዳር ድንበር በማስጠበቅ፣ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን በአንድነትና በላቀ ተሳትፎ በመገንባት የታየውን

> **የሀገር ፍቅር ስሜት ከግል ጥቅም ይልቅ ለብዙሃንና ለሀገር ጥቅም ቅድሚያ መስጠት ነው። በምክክሩ ሂደት ይህንን ማድረግ ከተቻለ ወደ መግባባት መምጣት ይቻላል። ዘመኑ የሚጠይቀው መስዋዕትነትም ይህንን ማድረግ ነው**

አርበኝነት፣ በምክክሩ በመድገም ሀገርን ወደፊት የሚያራምድ መግባባት መፍጠር ይገባል። ሰላም እንዲኖርና ታሪካችን ተጠብቆ እንዲቆይ እንደ ወጣት የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ገልጿል።

በአዲስ አበባ በተለምዶ ደንበል አካባቢ የሚኖሩት አቶ አበራ አቦዬ በበኩላቸው፣ የኢትዮጵያን ነጻነትና ረጅም ታሪክ ሲታሰብ፣ ለአለመግባባት ምክንያት የሆኑ ችግሮችን አስቀድመን መፍታት ይገባ እንደነበር ያነሳሉ።

"ጦርነትም ሞክረናል፤ የሰውንና የአምራቹን ዜጋ ሕይወት ከመብላት፣ ከንብረት ውድመት በስተቀር ምንም አላተርፍንም። አሁን ከእንቅልፋችን በመባነን ከሀይል ውጪ በሆነው የመፍትሔ አማራጭ (በምክክር) ችግሮቻችንን ለመፍታት እየሰራን ነው" የሚሉት አቶ አበራ፣ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ በአንድ ወቅት ባቀኑበት ያዩትን የቴምር ተክል በማስታወስ፣ ቴምር ለፍሬ ለመብቃት ቢያንስ ሰባት ዓመታት ይወስዳል፡፡ ቴምር ለትውልድ የሚተከል ነው፤ ምክክሩም በአንድ ጀምበር ተጀምሮ የሚያልቅ ሳይሆን ለቀጣዩ ትውልድ በማሰብ መሰረት የሚጣልበት መሆኑን መረዳት እንደሚገባ ይናገራሉ፡፡

ከንጉሱ ዘመን ጀምሮ ሶስት መንግስታትን የማየት አጋጣሚ እንዳገኙ የሚናገሩት አቶ አበራ፣ ቀደም ሲል ስልጣን ላይ የነበሩ አካላት ከላይ ወደ ታች ብቻ እያዩ ህዝብን ሳይሰሙ መቅረታቸውን ያስታውሳሉ። በአሁኑ ወቅት ግን ህብረተሰቡን ከታች ጀምሮ በማሳተፍ ሀገራዊ መግባባት ለማምጣት የሚደረገው ጥረት የሚደነቅ ነው፤ ተመካካሪዎች ዝቅ ብለው ሀገርን ከፍ ለማድረግ እየሰሩ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ መኮንን (ዶ/ር) ሀገራዊ ምክክሩ ለኢትዮጵያ በርካታ ጥቅም እንደሚያስገኝ ያብራራሉ፡፡ የጋራ የሆነ ብሔራዊ ርዕይ በኢትዮጵያውያን መካከል እንዲኖር ያደርጋል፡፡ በአንድ ዓይነት ዓላማ፣ አቋም፣ በጋራ በመቆም ለመስራትና ለመንቀሳቀስ ያስችላል፡፡

ሌላው የፖለቲካ ዋልታ ረገጥነትን በተለይ 'እኛ' እና 'እነሱ' የሚለውን ጫፍና ጫፍ የወጣ አመለካከት ለመግራት ያግዛል፡፡ አንዱ ብሔር በሌላው ላይ አለኝ የሚለው ታሪካዊ ቅራኔ ለመቀነስ ብሎም ለማክሰም ያስችላል፡፡ ተቋማት እንዲቀየሩ፣ እንዲጠናከሩ፣ ግጭትን የሚያስቀሩ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ መንግስትን እና የፖለቲካ ፓርቲዎችን ጨምሮ የተለያየ የፖለቲካ ተዋናዮች በህዝብ ዘንድ ያላቸው ቅቡልነት ይጨምራል፡፡ ምክንያቱም እርቅና መግባባት ከተፈጠረ የሚያጋጭ ነገር አይኖርም፤ በዚህም ምክክሩ ከግጭት መውጣት የሚያስችል እንደሆነ የፖለቲካ ሳይንስ መምህሩ መኮንን (ዶ/ር) አብራርተዋል፡፡

ጀግንነት በኢኮኖሚ፣ በትምህርት፣ የሀገርን ዳር ድንበር ከጠላት በመጠበቅ ሊታይ ይችላል፡፡ በአሁኑ ወቅት ወሳኝ የሆነ የፖለቲካ ጀግንነት (Political Patriotism) የሚያስፈልግበት ወቅት ላይ እንደምንገኝ መኮንን (ዶ/ር) ያነሳሉ። ይህም ለመቻቻል፣ ለመደማመጥ፣ ለመግባባት እድል መስጠት ነው፡፡ ከግል ይልቅ ለሀገር፣ ከቡድን ይልቅ ለብዙሃን፣ ከጠባብ ይልቅ ለሰፊ ቅድሚያ መስጠትን ያመለክታል፡፡ በምክክሩ ሂደት መግባባት ላይ መድረስ የሚቻለው 'ከእኔ የእሱ ሀሳብ ይሻላል'፤ 'እሱ ወይም እሷ በዚህ በኩል ተጎጂ ትሆናለች፤ ስለዚህ ለጋራ ጥቅም ሲባል የእኔን ጥቅም መስዋዕት ማድረግ አለብኝ' የሚል አመለካከት ሊኖር ይገባል፡፡ ከዚህ ውጪ 'የእኔ ሀሳብ ነው የሚበልጠው፤ ይኼ ካልሆነ ሞቼ እገኛለሁ' ማለት የሀገር ፍቅር ስሜት መገለጫ አይደለም፡፡ የሀገር ፍቅር ስሜት ከግል ጥቅም ይልቅ ለብዙሃንና ለሀገር ጥቅም ቅድሚያ መስጠት ነው፡፡ በምክክሩ ሂደት ይህንን ማድረግ ከተቻለ ወደ መግባባት መምጣት ይቻላል። ዘመኑ የሚጠይቀው መስዋዕትነትም ይህንን ማድረግ መቻል ነው፡፡

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በታሪካዊው የሀገራዊ ምክክር ጉባኤ ዋዜማ ላይ በይፋዊ የማህበራዊ ትስስር ገጻቸው (ፌስቡክ) ባስተላለፉት መልእክትም፤ ሀገራዊ ምክክሩ "ፍቱን የፖለቲካ መድረክ ብቻም ሳይሆን የእኛን እና የመጪውን ትውልድ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# የሉዓላዊነት ልብ

- **የዲፕሎማሲ አማራጮችን በመጠቀም የባህር በር ለማግኘት በትጋት መስራት እንደሚገባ ተጠቁሟል**

**በስንታየሁ ምትኩ**

በዓለም ላይ 44 ሀገራት ወደ ባህር መውጫ በር የላቸውም፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በአፍሪካ፣ አውሮፓ፣ እስያ እና ደቡብ አሜሪካ የሚገኙ 32 የባህር በር የሌላቸው አዳጊ ሀገራት ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ትልቋ ከ130 ሚሊዮን በላይ የህዝብ ቁጥር ያላት ኢትዮጵያ ስትሆን፤ ትንሿ ደግሞ አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብ ያላት ቡታን ናት፡፡ የባህር በር በሌላቸው አዳጊ ሀገራት በአጠቃላይ ከ600 ሚሊዮን ህዝብ በላይ እንደሚኖር የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስለወደብ አልባ ሀገራት የሚያትተውና በገፀ-ድሩ ላይ ያጋራው ጽሁፍ ያመለክታል፡፡

የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ባለፈው ዓመት በየዓመቱ ሐምሌ 30 ቀን (በፈረንጆቹ አቆጣጠር ኦገስት 6ን) የባህር በር የሌላቸው ታዳጊ ሀገራት ልዩ የልማት ፍላጎቶች እና ፈተናዎችን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዓለም አቀፍ ቀን ሆኖ ታስቦ እንዲውል ወስኗል፡፡



ፎቶ፦ ከፋይል
የባህር በር ጥያቄው መልስ እንዲያገኝ ሁሉም የአርበኝነት ሚናውን እንዲወጣ ይጠበቃል

## ኢትዮጵያ እና የባህር በር

በኢትዮጵያ ታሪክ በአክሱም ዘመነ መንግስትና ከዚያ በኋላ የነበሩ ስልጣኔዎች መሰረታቸው ከባህር ጋር የተቆራኘ ነው። ባህር ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ምንጭ፣ የህልውና መጠበቂያ አቅም፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የፖለቲካ ሚዛን ማስጠበቂያ እንዲሁም ከውጭ ዓለም ጋር ለሚደረግ የንግድ ልውውጥ ማሳለጫ በመሆን ትልቅ ሚና ተጫውቷል፡፡ ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር እየራቀች በመጣች ቁጥር የኢኮኖሚ፣ የዲፕሎማሲና ራስን የመጠበቅ አቅሟ እየተዳከመ መምጣቱን የታሪክ ባለሙያዎች ፅፈዋል፡፡ ኢትዮጵያ ስትጠቀምባቸው ከነበሩ የባህር በርና ወደቦች መካከል አዶሊስ፣ ዘይላ፣ በርበራ፣ ምጽዋ እና አሰብ ይጠቀሳሉ፡፡

በ1983 ዓ.ም የመንግስት ለውጥ ሲመጣና ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ራሷን የቻለች ሀገር ስትሆን ኢትዮጵያ የባህር በሯን አጥታለች፡፡ ኤርትራ ነጻ በወጣችበት ወቅት የአሰብ ወደብ ለኢትዮጵያ በነጻ እንዲያገለግል ስምምነት ነበር፡፡ የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትን ተከትሎ ግን ይህ ሁኔታ መቋረጡን "የሁለት ውኃዎች ዐቢይ ስትራቴጂ" በሚል ርዕስ በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የተዘጋጀው ሰነድ ያሳያል፡፡

## የባህር በር ባለመኖሩ ምን አጣን?

በአዲስ አበባ ከተማ በተለምዶ "ፈረንሳይ ሌጋሲዮን" እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ የሆኑት አቶ ሰለሞን መላኩ፤ ኢትዮጵያ ላለፉት ከ30 በላይ ዓመታት የባህር በር አጥታ መኖሯን በታላቅ ቁጭት በማስታወስ ይህ ጉዳቱ ዘርፈ ብዙ መሆኑን ይገልጻሉ።

"የባህር በር ባለመኖሩ እያስከተለብን ያለው የኢኮኖሚ ጫና ቀላል አይደለም" የሚሉት አቶ ሰለሞን፣ "ከምንበላውና ከምንጠጣው እየቀነስን በሀገር ውስጥ ከፍተኛ ልማት ማምጣት የሚያስችል ብር ለወደብ ኪራይ እየከፈልን እንገኛለን። ከዚህ በተጨማሪ የባህር በር የሌላቸው ሀገራት እንደ ተመፅዋች ነው የሚታዩት። ለዚህ ምክንያቱ በሌላ ሀገር ግዛት አልፈው ወደ ዓለም አቀፍ ገበያ ስለሚገቡ ነው።" ሲሉ ያስረዳሉ።

በታሪክ የባህር በር የነበራት ሀገር ይህንን ሀብት ማጣቷ ታሪካዊ ስህተት ብቻ ሳይሆን፣ የህዝብን ሞራልና በራስ መተማመን የሚቀንስ፣ የሀገርን ደህንነት በአስተማማኝ መልኩ ለመጠበቅ የሚያስቸግርና ለውጭ ወራሪዎች ሊያጋልጥ የሚችል መሆኑን ያነሳሉ።

ኢትዮጵያ የባህር በር አልባ የሆነችው በዙሪያዋ በነበሩ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀይሎች አሻጥር መሆኑን የሚናገሩት አቶ ሰለሞን፣ ይህንን ታሪካዊ እውነታ ለመቀልበስ እና ኢትዮጵያን ወደ ባህር ለመመለስ መንግስት እያደረገ ያለው ቁርጠኝነት የሚበረታታ መሆኑን ይገልጻሉ።

"ያለ መስዋዕትነት የሚገኝ ድል የለም፤ የሚከፈለው መስዋዕትነት ግን የሰው ህይወት የማይጠይቅ ሆኖ ያጣነውን የባህር በር ማግኘት ከተቻለ እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ደስተኛ ነኝ" የሚሉት አቶ ሰለሞን፣ እንደ ነጋዴ የማህበረሰብ ክፍል ሀገራቸው የባህር በር ባለቤት እንድትሆን መንግስትና ህዝብ በሚያደርጉት ጥረት የበኩላቸውን ለመወጣት ዝግጁ ናቸው፡፡ ህዝቡም ኢትዮጵያ በሰላማዊ መንገድ በዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ህግ በሚፈቅደው መሰረት ማግኘት የሚያስችላትን ጥረት ሊደግፍ እንደሚገባ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።

ሰኔ 10 ቀን 2018 ዓ.ም ቻተም ሃውስ የተሰኘው ዓለም አቀፍ ተቋም በለንደን ባዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጌዲዮን ጢሞቴዎስ (ዶ/ር)፤ "ኢትዮጵያ ውዝግብ በሞላበት ቀጣና ውስጥ በውጭ ጉዳይ ፖሊሲዎቿ ቅድሚያ የምትሰጣቸው ጉዳዮች" በሚል ርዕስ ባደረጉት ንግግር፣ የኢትዮጵያ የዛሬ አንዱና እጅግ ወሳኝ ስትራቴጂካዊ ጥያቄ የባህር በር ማግኘት እንደሆነ ተናግረዋል። ይህ ጉዳይ አዲስ የመነጨ ፍላጎት ሳይሆን ንግድን፣ ሎጂስቲክስን፣ የኢነርጂ ደህንነትን እና የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚ ዕቅድን እየጎዳ ያለ መዋቅራዊ ጉዳይ በመሆኑ ነው፡፡ በዚህ ላይ የኢትዮጵያ አቋም የባህር በር ማግኘት የሀገራዊ ልማትና የቀጣናዊ ውህደት ጉዳይ ነው የሚል መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ሚኒስትሩ እንደገለፁት፤ ኢትዮጵያ የባህር በር ለማግኘት ውይይትን፣ የጋራ ጥቅምን እና ቀጣናዊ መረጋጋትን በማስቀደም ትንቀሳቀሳለች፡፡ በአፍሪካ ቀንድ የኢኮኖሚ ትስስር ለመፍጠር የሚደረገው ጥረት፣ ሀገራቱ የሚገናኙባቸውን የትስስር ችግሮች በትብብር ማዕቀፍ መፍታት ካልተቻለ እውን ማድረግ አይቻልም።

> **የኢትዮጵያ የወደብ ባለቤት መሆን ጥቅሙ ለራሷ ብቻ ሳይሆን ለአካባቢው እና ለዓለም ዓቀፉ ማህበረሰብ ጭምር ነው**

በቅርቡ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነትና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ ፈትሂ ማህዲ በኢትዮጵያ የኪርጊዝ ሪፐብሊክ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደርን ተቀብለው ባነጋገሩበት ወቅት እንደገለፁት፣ ኢትዮጵያ የባሕር በር ባለቤት ባለመሆኗ ምክንያት በየዓመቱ ለወደብ ኪራይና ተያያዥ የሎጂስቲክስ አገልግሎቶች እስከ 2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚደርስ ወጪ ታወጣለች፡፡

በውጭ ጉዳይ ኢንስትቲዩት የተዘጋጀው ከላይ የተጠቀሰው ሰነድ እንዳመላከተው፣ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ከሆነች በኋላ በዋነኛ የወጪ ንግድ መተላለፊያነት እየተጠቀመች ያለው የጅቡቲን ወደብ ነው፡፡ ወደቡ ከመሀል ሀገር ያለው ርቀት ከፍተኛ፣ የመንገድ መሰረተ ልማቱም የተጓደለ በመሆኑ ለከፍተኛ የትራንስፖርት አገልግሎት ወጪ ተዳርጋለች፡፡ አብዛኛው የወጪ ንግድ ግንኙነቷ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ሳይሆን ባህር ማዶ ካሉት ጋር ነው፡፡ በተጨማሪ ሀገሪቱ የወጪ ንግድ ግንኙነቷ በጅቡቲ በኩል ስለሚያልፍ የጅቡቲ መንግስት በየጊዜው በሚያደርገው የክፍያ ጫና መጨመር ሀገር ውስጥ ላለው የዋጋ ጭማሪ የራሱ የሆነ አሉታዊ አስተዋፅኦ አሳድሯል፡፡

በተጨማሪም ኢትዮጵያ እንደ ሌሎቹ ያላደጉ ወደብ አልባ ሀገራት ሁለት እጥፍ የሆነ የኢንሹራንስና የመጓጓዣ ክፍያ ትከፍላለች፡፡ ከሌሎች የበለፀጉ ሀገራት ጋር ሲነጻጸር ደግሞ ሶስት እጥፍ የሆነ ክፍያ ትከፍላለች፡፡ ለወደብ አገልግሎት በየዓመቱ የሚከፈለው ከፍተኛ ወጪ ኢኮኖሚውን እየጎዳው ይገኛል፡፡ እየወጣ ያለው ገንዘብ ምናልባት ለውስጥ የመሰረተ ልማትና ማህበራዊ ልማት ግንባታ ቢውል የተሻለ ልማት ለማረጋገጥ አስቻይ ሁኔታ ይፈጥር እንደነበር በሰነዱ ተጠቅሷል። ታዋቂው እንግሊዛዊ የምጣኔ ሀብት ተመራማሪ ፖል ኮሊየርም ወደብ አልባ መሆን የአዳጊ ሀገራት ዋነኛ ጋሬጣ እንደሆነ "The Bottom Billion" በተሰኘው መጽሀፋቸው ላይ አብራርተዋል፡፡

በቦንጋ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ረዳት ፕሮፌሰር ያሬድ አያሌው (ዶ/ር) እንደገለፁት፤ የኢትዮጵያ የባህር በር አልባ ሀገር መሆን ከኢኮኖሚ ባሻገር ከደህንነት አኳያ ከፍተኛ ተፅዕኖ አለው፡፡ ኢትዮጵያ የወጪ ንግዷን የምታካሂደው የጅቡቲ ወደብን በመጠቀም ሲሆን ይህ ግንኙነት ሊቀጥል የሚችለው በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለው መልካም ግንኙነት እስከቀጠለ ድረስ ነው።

የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ኢንስትቲዩት ያዘጋጀው ሰነድ እንደሚያሳየው፣ የኢትዮጵያ እና ጅቡቲ ደህንነት አንዱ በሌላው ላይ የተንጠለጠለ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የወጪ ገቢ ንግድ በጅቡቲ ወደብ ላይ የተንጠለጠለ እንደመሆኑ፣ የጅቡቲ ገቢም በኢትዮጵያ መረጋጋትና አስተማማኝ እድገት ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ በተጨማሪም የወደብ አገልግሎት እየሰጡ ባሉ ሀገራት ያለው የፖለቲካ ሁኔታ ወደብ አልባ ለሆኑ ሀገራት የንግድ እንቅስቃሴ ወሳኝነት አለው። ለምሳሌ፡- በጅቡቲ ውስጥ የፖለቲካ አለመረጋጋት

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# ከእለት ጉርስ ባሻገር

- ባለፉት አምስት ዓመታት ከ5 ሺህ 500 በላይ የተስፋ ብርሀን ምገባ ማዕከል ተጠቃሚዎች የስራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል

**በለይላ መሀመድ**



ፎቶ - ከፋይል

መስራት ለሚችሉ የምገባ መርሃ ግብሩ ተጠቃሚዎች የግብዓት ድጋፍ ሲደረግ

ወይዘሪት ገነት እዮብ ቆሎ በመሸጥ ነበር ራሷን የምታስተዳድረው። የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ባስከተለው ተፅዕኖ ምክንያት ራሷንም ሆነ የሚች እህቶቿን ልጆች በቀን አንድ ጊዜ መመገብ ተቸግራ ነበር። ከዚህ ችግር ወጥታ እፎይታ እንድታገኝ ያደረጋት የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከል መግባቷ እንደነበር ነው ያጫወተችን።

በመጀመሪያ ከማዕከሉ ያገኘችው የዕለት ምግብ ድጋፍ ነበር፡፡ በመቀጠል በራሷ አቅም ሰርታ የምትለወጥበት የስራ ዕድል ተፈጥሮላታል። “የአዲስ አበባ ምገባ ማዕከል በሻይ ቡና ስራ ተሰማርቼ ራሴን በራሴ የማስተዳድርበት ገቢ እንዳገኝ አድርጎኛል” የምትለው ወይዘሪት ገነት፣ ለስራዋ የሚያስፈልግ የተለያየ ቁሳቁስ ድጋፍ ተደርጎላት በየታክሲ ተራው እያዞረች ሽጣ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነቷን በማሳደግ ራሷንና ቤተሰቧን እያስተዳደረች ትገኛለች፡፡

በአሁኑ ወቅት ከሰዎች እጅ ሳትጠብቅ በስራዋ የምታገኘው ገቢ የሚች እህቷን ልጆች በሰላም ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ እድል እንደፈጠረላትና በዚህም ኩራት እንደሚሰማት ገልጻለች። የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከል ይህንን ዕድል ለሌሎችም ተቸግረው ለሚኖሩ ወገኖች ቢያደርስ መልካም ነው ስትልም አስተያየቷን ሰጥታለች፡፡

ወይዘሮ ሳባ ከበደም በተመሳሳይ በሰው ቤት ልብስ አጠባ ስራ ተሰማርተው ነበር ሶስት ልጆቻቸውን ያስተዳድሩ የነበረው። ባለቤታቸው ተባራሪ ስራ ስለሚሰሩና ገቢው ከሞላ ጎደል በመሆኑ ቤታቸውን ማሸነፍ አቅቷቸው ነበር፡፡ በዚህ ችግራቸው የምገባ ማዕከሉ ተጠቃሚ መሆን መጀመራቸውን ይናገራሉ። ሆኖም ማዕከሉ በየቀኑ ከመመገብ ባለፈ የስራ ዕድል ፈጥሮላቸዋል፡፡ የዳቦ መጋገሪያ ማሽን ተሰጥቷቸው ወደ ስራ መግባታቸውንና ይህም ራሳቸውን እንዲችሉ እንዳገዛቸው ለዝግጅት ክፍላችን ተናግረዋል።

ወይዘሪት ገነትን እና ወይዘሮ ሳባን ማሳያ አደረግን እንጂ ከዕለት ምገባ ባለፈ በሁለት እግራቸው ቆመው ራሳቸውን ማስተዳደር ይችሉ ዘንድ የስራ እድል የተፈጠረላቸው ሰዎች ስለመኖራቸው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምገባ ኤጀንሲ መረጃ ያመላክታል፡፡ የዝግጅት ክፍላችም የኤጀንሲው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ስንታየሁ ማሞን ከምገባ አገልግሎቱ ባለፈ የስራ እድል በመፍጠር ረገድ እየተሰራ ስላለው ስራ አስተያየታቸውን ጠይቋል፡፡

እንደ ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ ገለጻ፣ የምገባ ማዕከሉ የተቋቋመበት ዋና ዓላማ የእለት ጉርስ ለሌላቸው ዜጎች የምገባ አገልግሎት መስጠት ነው፡፡ ማዕከሉ የማህበራዊ ፍትህ ማንገሻ ነው፡፡ በተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከላት ተጠቃሚዎች መካከል የመስራትና የመንቀሳቀስ ሙሉ አካላዊ አቅም ያላቸው ሰዎች ወደ ስራና በራሳቸው ገቢ ህይወታቸውን ወደ መምራት እንዲሸጋገሩ የሚያደርጉ የተለያዩ የድጋፍና የማቋቋም ስራዎች ይከናወናሉ።

በአሁኑ ወቅት በ30 የምገባ ማዕከላት ለ41 ሺህ ዜጎች አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ማዕከሉ የምገባ አገልግሎቱን የሚሰጠው “ከመመገብ ባሻገር” የሚል መሪ ሀሳብ ይዞ ነው፡፡ ይህም ማለት ዜጎች እለታዊ ማህበራዊ ችግራቸውን ለመሻገር የእለት ጉርስ የሌላቸው ምገባ እንዲያገኙ ከማድረግ ባሻገር ካሉበት ችግር በዘላቂነት እንዲላቀቁ የስራ እድል መፍጠር ነው፡፡ የተስፋ ብርሀን ስራ እድል ፈጠራ ሲነሳ ወደ ምገባ ማዕከሉ የሚመጡ ሁሉም ዜጎች መስራት ስለማይፈልጉ ብቻ ሳይሆን ከነበሩበት ማህበራዊ ችግር ተላቅቀው ወደ ሌላ አምራችነት ለመሻገር ለተወሰነ ጊዜ የስነ-ልቦና እና የኢኮኖሚ ድጋፍ ስለሚፈልጉ ነው፡፡ ዘመናቸውን ሙሉ በዘላቂነት ድጋፍ የሚፈልጉ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ ለዚህም ነው የማዕከሉ ዋና ስራ የምገባ አገልግሎት መስጠት ቢሆንም የስራ እድል መፍጠር እንደ ሁለተኛ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ ያለው፡፡

> **በተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከላት ተጠቃሚዎች መካከል የመስራት አቅም ያላቸው ሰዎች ወደ ስራና በራሳቸው ገቢ ህይወታቸውን ወደ መምራት እንዲሸጋገሩ የሚያደርጉ የተለያዩ የድጋፍና የማቋቋም ስራዎች በመከናወን ላይ ናቸው**

የስራ እድል ፈጠራ ላይ ትኩረት ተደርጎ መሰራቱ የሚያስገኛቸው በርካታ ጠቀሜታዎች አሉ፡፡ አንደኛ መስራት የሚችሉ የህብረተሰብ ክፍሎች የተረጂነት ስሜት እንዳያዳብሩ በማድረግ ‘እኔ መስራት እችላለሁ’ በሚል አስተሳሰብ ራሳቸውን ቃኝተው ከተረጅነት ስሜት እንዲላቀቁ ማድረግ ነው፡፡ በዚህም ምገባ ማዕከሉ መስራት የሚችሉትን ለይቶ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅትና በትብብር የስራ እድል እንዲፈጠርላቸው በማድረግ ኢኮኖሚያዊ አቅማቸውን እንዲያሳድጉ ይደረጋል፡፡ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራውን ስራ በዋናነት ምገባ ኤጀንሲ የማመቻቸት ስራ ይሰራል፡፡

እንደ ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ ገለጻ፤ መስራት የሚችሉት ዜጎች ከተለዩ በኋላ ‘ከተረጂነት እወጣለሁ፤ በራሴ አቅም ቆሜ ሌሎችን እረዳለሁ’ የሚል ስሜት እንዲያዳብሩ የስነ ልቦና እንዲሁም የክህሎት ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል። በመቀጠል የመነሻ ካፒታል እና የመስሪያ ቦታ እንዲሰጣቸው በማድረግ በተፈጠረው የስራ መስክ እንዲሰማሩ የማመቻቸት ስራ ይሰራል፡፡ በእነዚህ የስራ እድል በተፈጠረላቸው ዜጎች ምትክ ሌሎች ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ዜጎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

የስራ እድል የሚፈጠርላቸው ዜጎች የሚመረጡበትን መስፈርት በተመለከተ ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ ሲያብራሩ፤ የመጀመሪያው መስፈርት ‘መስራት እችላለሁ’ የሚል የስራ ፍላጎት መኖር ነው። ለመለወጥ ያላቸው ፍላጎትና ቁርጠኝነት ይታያል፡፡ ሁለተኛው እድሜ ሲሆን ከ60 ዓመት በታች መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ጤነኛ መሆን እንዲሁም የአዲስ አበባ ነዋሪ የሆኑና የነዋሪነት መታወቂያ ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል።

ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ እንደገለፁት፤ የምገባ ኤጀንሲው ወደ ስራ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ባለፉት አምስት ዓመታት ከ5 ሺህ 500 በላይ ዜጎች የዚህ ተጠቃሚ ሆነዋል። በ2018 በጀት ዓመት ብቻ 1 ሺህ 63 የሚሆኑ ዜጎችን ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን ለስራ መነሻ የሚሆን ገንዘብና የመስሪያ ቦታ እንዲሁም ቁሳቁስ እንዲሰጣቸው በማድረግ በእንጀራና ዳቦ መጋገርና ማከፋፈል፣ በሻይ ቡና፣ በፓርኪንግ፣ በሱቅ ስራዎች እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡ ከውጤታማነት አንጻር በርካታ ዜጎች ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን በራሳቸው አቅም መርዳት ችለዋል፡፡

በአነስተኛ የሰው ቤት ስራ እና በልመና እንዲሁም ጎዳና ላይ ሲያድሩ የነበሩ በርካታ ሰዎች ዛሬ ላይ በራሳቸው አቅም ቤታቸውን መምራትና ማስተዳደር መቻላቸው ደስተኞች እንዲሆኑ አስችሏቸዋል፡፡ ይህንን ተግባር በቀጣይም ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

እነዚህን በማህበራዊ ችግሮች ምክንያት ወደ ተስፋ ብርሀን የምገባ ማዕከል የገቡና መስራት የሚችሉ ዜጎችን በተለያየ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች፣ የመንግስት ተቋማት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የስራ እድል በመፍጠር ማገዝ አለባቸው፡፡ በማዕከሉ የስነ ልቦና እና የክህሎት ስልጠና የወሰዱ ዜጎችን በመቅጠር አጋርነታቸውን ማሳየት ይኖርባቸዋል ሲሉም ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# የኪነ ጥበብ ድግሶች

**በጊዜው አማረ**

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል። ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል መሰናዶዎች ይቀርባሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የመጽሐፍት ምረቃ፣ የኪነ ጥበብ አውደ ርእይ እና የቴአትር መርሃ ግብር ይገኙበታል፡፡ ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

## የቴሌቪዥን ተከታታይ ሾው

192 ሚሊዮን ዓለም አቀፍ ተመልካቾች ባሉት አማዞን ፕራይም አማካኝነት የሚተላለፈው እና የኢትዮጵያን በጎ ገጽታ፣ የባህልና የቅርስ ሀብቶች እንዲሁም የአዲስ አበባን አዲስ ገጽታ የሚያስቃኝ “Why Are You Not Here?” የተሰኘ የቴሌቪዥን ተከታታይ ሲሪየስ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በዛሬው ዕለት በዓድዋ ድል መታሰቢያ ለዕይታ ይበቃል።

ይህ በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሠረተው ሲሪየስ ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ አቅንቶ በሃገሪቷ ፍቅር፣ በባህሏ፣ በቅርሶቿና በህዝቡ እንግዳ ተቀባይነት ስለተማረከ አፍሪካዊ-አሜሪካዊ ገጣሚ የሚተርክ ልዩ ሥራ መሆኑን የኤቨንት አዲስ ዘገባ ያሳያል፡፡

በመርሃ ግብሩ በነፃ የመታደም፣ የዓድዋ ድል መታሰቢያን የመጎብኘት እና ከዓለም አቀፍ እንግዶች ጋር የመገናኘትና የመተዋወቅ አጋጣሚ መመቻቸቱ የተገለጸ ሲሆን በተጠቀሰው ቀንና ቦታ በ9:00 ሰዓት ይካሄዳል፡፡

## መጽሐፍት

“በመሃል” የተሰኘው መጽሐፍ ዛሬ ይመረቃል፡፡ የእመቤት አብዲሳ የአጫጭር ታሪኮችና የግጥም ስብስብ ስራ የሆነው ይህ መጽሐፍ ከቀኑ 8:00 ሰዓት ጀምሮ መስቀል አደባባይ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ፊትለ ፊት በሚገኘው




ፎቶ- ከገፀ ድር
በመዲናዋ ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

ከተማ ማዕከል ይመረቃል፡፡ በምረቃ ስነ ስርዓቱ ላይ አንጋፋና ወጣት ደራሲያንና ገጣሚያን እንደሚታደሙ ተገልጿል፡፡

በሌላ መረጃ “ትወና እና ወጋየሁ ንጋቱ” የተሰኘው መጽሐፍ በቅደመ ህትመት ሽያጭ ለገበያ ቀርቧል፡፡ በፋሲካ ለገሠ የተጻፈው ይኸው መጽሐፍ የከያኒ ወጋየሁ ንጋቱ ህይወት ታሪክ እና ስራዎቹን ይዟል።

በተመሳሳይ ልጆች በተደጋጋሚ ለሚያጠቁ የጤና ችግሮች መፍትሔዎችን የሚያስገነዝብና በደራሲ አብርሐም ካሳዬ የተጻፈ “ልጆችን በተደጋጋሚ የሚያጠቁ በሽታዎችና የቤት ውስጥ ቀላል ሕክምናዎች” የተሰኘ ኢ-ቡክ ለአንባቢዎች ቀርቧል።

መጽሐፉ 49 የሕፃናት ጤና ርዕሶችን በመዳሰስ ትኩሳት፣ ተቅማጥና ማስታወክ፣ የመተንፈሻ አካላት ሕመሞች፣ አስም፣ ድንገተኛ አደጋዎች፣ የቆዳ፣ የዓይን፣ የጆሮና የጥርስ ጤና እንክብካቤ እንዲሁም በአስቸኳይ ወደ ሕክምና ተቋም መሄድ የሚገባቸውን አደገኛ ምልክቶች (Red Flags) የሚያስገነዝብ ነው፡፡

በተጨማሪ “ፋቡላ” የተሰኘ 45 አጫጭር የዓለም ተረቶችን የያዘው እና ከ4 እስከ 12 ዓመት ዕድሜ ላሉ ልጆች የሚሆን መጽሐፍ በኢ-ቡክ አማካኝነት ለንባብ በቅቷል፡፡

## የውይይት መርሃ ግብር

90ኛው ዙር የዐውደ ፋጎስ የሃሳብና የንባብ ውይይት መድረክ በነገው እለት ይካሄዳል፡፡ የውይይቱ ርእሰ “ተሰጥኦን ፍለጋ” ሲሆን ደራሲ ዘነበ ወላ የውይይቱ አቅራቢ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ውይይቱ ከቀኑ 8:00 ሰዓት ላይ በኢትዮጵያ ቤተ መዛግብት እና ቤተ መጻሕፍት (ወመዘክር) ይደረጋል፡፡

## የቴአትር መርሃ-ግብር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ። በብሄራዊ ቴአትር ቤት ቅዳሜ 8:00 ሰዓት “12ቱ እንግዶች” እንዲሁም በ12:00 ሰዓት “በር የሌለው ቤት” ቴአትሮች ይታያሉ። እሁድ ደግሞ በ8:00 ሰዓት “ንጉስ አርማሕ” እንዲሁም በ12:00 ሰዓት “እምዩ ብረቷ” ይታያሉ፡፡ ተመልካቾችም ጊዜያቸውን ለመቆጠብ የ“ሁሉ በጄ” መተግበሪያን በመጠቀም ትኬቶችን አስቀድመው መግዛት እንደሚችሉ ተገልጿል።

በአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ “እሳት ወይ አበባ” ዘወትር ቅዳሜ በ11:00 ሰዓት እንዲሁም “ባልቻ አባነፍሶ” እሁድ በ8:00 ሰዓት የሚታዩ ሲሆን ትኬቱን በኦንላይን የክፍያ ስርዓት መቁረጥ እንደሚቻል ተጠቁሟል፡፡

ቦሌ ፍላሚንጎ በህፃናትና ወጣቶች ቴአትርና ሲኒማ ኮምፕሌክስ ቅዳሜ ጠዋት 4:00 ሰዓት “አዮ ቦራ” የተሰኘው የአፋን ኦሮሞ ቴአትር ይታያል፡፡ እሁድ ጠዋት 4:00 ሰዓት ደግሞ “የንባብ ከተማ” የተሰኘው አዲስ ቴአትር ለእይታ ይበቃል፡፡ እሁድ በ8:00 ሰዓት በቅርቡ ወደ መድረክ የመጣው “ወህኒ አምባ”፣ 11:30 ሰዓት ደግሞ “አትጥሪኝ” የተሰኙ ቴአትሮች ለተመልካች ይደርሳሉ፡፡

እንዲሁም በሀገር ፍቅር ቴአትር ረቡእ በ11:00 “አሉ” የተሰኘው አዲስ ቴአትር፣ ሐሙስ 11:30 ሰዓት “ነገሩ አይቆምም”፣ እሑድ በ8:00 ሰዓት ሰዴታ (በአፋን ኦሮሞ) እና በ12:00 ሰዓት “የመጨረሻው ፍርድ” ለቴአትር አፍቃሪያን ይቀርባሉ።

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ጥያቄ መልስ

በእያንዳንዱ ሳጥኖች ላይ የተጻፉ ቁጥሮች ድምር ከሳጥኑ በታች የተጻፈውን ቁጥር ይሰጠናል፡፡ ማለትም የመጀመሪያው 8 + 4 + 7 = 19 ነው፡፡ ሁለተኛው 8 + 2 + 1 = 11 ይሆናል፡፡ በዚህ አመክንዮ መሰረት የጥያቄ ምልክት ያለበት ስሌት 4 + 3 + 2 = 9 ይሆናል፡፡ ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ የሚገባው ትክክለኛ ቁጥር 9 ነው፡፡




## የዛሬው የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# የሀገር በቀል እሴቶች አሻራ በዘመናዊው ኪነ ጥበብ

**በአብርሃም ገብሬ**

በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ከተፈጠሩ እጅግ አስደናቂ ጉዳዮች መካከል በባህል ውስጥ የሚገኙ መልከ-ብዙ እሴቶች ዋነኛ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ምክንያቱም ባህል ውስጥ ማህበረሰብ አለ፡፡ ባህል ውስጥ ስልጣኔ አለ፡፡ ባህል ውስጥ ፍልስፍና አለ፡፡ ባህል ውስጥ ፈጠራ አለ፡፡ እንደ ኪነ ጥበብ ያሉ የፈጠራ ስራዎችም መገኛቸው ይኸው ባህል ነው፡፡


ፎቶ- ከገፀ ድር
የሀገር በቀል ሙዚቃዎችና መሳሪያዎች ለኪነ ጥበቡ መጎልበት አስተዋጽኦ እያደረጉ ነው

ኢትዮጵያ የጥንታዊ ስልጣኔ ባለቤት እንደመሆኗ፣ ከዚህ ሥልጣኔና ረጅም ታሪክ ሲወራረሱ የመጡ በርካታ ቅርሶችና ጥበባዊ እሴቶች አሏት፡፡ እነዚህ እሴቶች ባለ-ብዙ ባህል፣ ሀይማኖት፣ ቋንቋ፣ ዜማ፣ ኪነ ህንጻ፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች... ባለቤት እንድትሆን አስችሏታል፡፡ በዚህ አምድም በየዓመቱ ነሃሴ ሶስት (እ.አ.አ ነሃሴ 9) የሚከበረው ዓለም አቀፍ የሀገር በቀል ማህበረሰቦችና ባህሎች ቀን (International Day of the World's Indigenous People) መነሻ በማድረግ፣ የኢትዮጵያ ሀገር በቀል ባህሎች ለኢትዮጵያ ዘመናዊ ኪነ ጥበብና ለአሰባሳቢ ትርክት ግንባታ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ በጨረፍታ ልናስቃኛችሁ ወድደናል፡፡

የዓለም አቀፍ የሀገር በቀል ማህበረሰቦችና ባህሎች ቀን በየዓመቱ በዩኔስኮ ደረጃ ይከበራል፡፡ እለቱ የሰው ልጅ የታሪክ፣ የእውቀትና የባህል ብዝሃነት ጥበቃ ለእድገትና ሰላም ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ የሚያሳስብ ትልቅ መድረክ ነው። እንዲሁም የሀገር በቀል ማህበረሰቦች ባህል፣ እውቀት፣ ጥበባዊ አሻራዎች፣ ማንነት... ሊጠበቁና ሊከበሩ የሚገባቸው የሰው ልጅ የጋራ ሃብቶች መሆናቸውን አጽንኦት ለመስጠትም ጭምር ነው። ኢትዮጵያ ደግሞ በብዝሃ ባህልና እሴት የደመቀች ነች፡፡ በርካታ ሀገር በቀል እሴቶችን፣ የዜማ ስልቶችንና ኪነ ጥበባዊ ሥራዎችን ከእነዚህ ሀገር በቀል ዕሴቶች አግኝታለች፡፡ እነዚህ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ የቆዩ መልከ ብዙ ጥበባዊ እሴቶች የሀገሪቱን የማህበራዊ ህይወት መስተጋብር ከማጠናከራቸውም በላይ ለዘመናዊው የኪነ ጥበብ ዘርፍ ታላቅ የፈጠራ መሰረት በመሆንም አገልግለዋል።

የሙዚቃ ተመራማሪዎች እንደሚገልፁት፣ ኢትዮጵያ በሙዚቃና በሙዚቃ መሳሪያዎች ብዝሃነት ከሚታይባቸው ሀገራት መካከል አንዷ ነች፡፡ እነዚህን የሙዚቃ መሳሪያዎች ማህበረሰቡ ለፈርጀ-ብዙ አገልግሎቶች እንደሚጠቀምባቸው የባህል ጉዳዮች ተመራማሪ ሰሎሞን ተሾመ (ዶ/ር)፣ 'ፎክሎር' በተሰኘው መጽሃፋቸው አስፍረዋል፤ "የተለያዩ ፌስቲቫሎች፣ ስነ ስርዓቶች፣ ድራማዎች፣ ሙዚቃዎች፣ ሀይማኖታዊ የሆኑና ያልሆኑ ክዋኔዎች በሚቀርቡበት ወቅት ክዋኔዎችን ለማጀብ እንደማህበረሰቡ ባህል የተለያዩ ሀገረሰባዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች (Folk Musical Instrument) ይቀርባሉ፡፡ እነዚህ መሳሪያዎች በተለያዩ ሥርዓቶች በርካታ ጠቀሜታ ቢኖራቸውም ዋና ዓላማቸው ስሜትን ለመግለጽና ለደስታ..." የሚውሉ መሆናቸውን በመጽሃፋቸው አስፍረዋል።

## ከሀገር በቀል እሴት እስከ ዓለም አቀፍ ዜማ

የባህልና ኪነ ጥበባዊ ጉዳዮች ተመራማሪ ወሰን ባዩ (ዶ/ር) ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት፣ የኢትዮጵያ ሀገር በቀል ማህበረሰቦች ዛሬ ላይ የምንኮራባቸው በርካታ እሴቶች ጠብቀው ያቆዩ ባለውለታዎች ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ የብዝሃ ባህልና እሴት ባለቤት እንድትሆን ያስቻላትም የማህበረሰቡ አርቆ አስተዋይነት ነው፡፡ በተለይ ሀገር በቀል ባህሎች ለኢትዮጵያ ዘመናዊ ኪነ ጥበብ ማደግ መነሻ የሆኑ በርካታ እሴቶች ማበርከታቸውን ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሀገር በቀል ባህሎች በሙዚቃና በሌሎች የኪነ-ጥበብ ዘርፎች ውስጥ ለተሰሩ ጥበባዊ የፈጠራ ስራዎች ማዕከል እንደሆኑ ያብራሩት ወሰን (ዶ/ር)፣ እነዚህ ጥበባዊ አሻራዎች ዘመናዊው የኪነ-ጥበብ ዘርፍ ኢትዮጵያዊ መገለጫ እንዲይዝ አስችለውታል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ የሙዚቃ መሳያዎች፣ ስነ-ቃሎች፣ ፍልስፍናዎች፣ የምስል እይታዎችና ጥበባት ከኢትዮጵያም አልፈው ለዓለም ማህበረሰብ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ ለዚህ ጥሩ ማሳያ የኢትዮ-ጃዝ ሙዚቃ ስልት መሆኑን ምሁሩ አብራርተዋል፡፡

በእርግጥም ኢትዮ ጃዝ ከሀገር በቀል የኢትዮጵያ ባህሎች ውስጥ ተገኝቶ፣ ዛሬ የዓለም ማህበረሰብ የጋራ ቋንቋ ወደመሆን ደረጃ ከፍ ብሏል፡፡ ይህ የሙዚቃ ስልት ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ በተለያዩ የዓለም ክፍል ያሉ የሰው ልጆች የጋራ ተወዳጅ የጥበብ እሴት ሆኗል፡፡ የኢትዮ ጃዝ የሙዚቃ በኢትዮጵያ ሀገር በቀል የሙዚቃ ቅኝቶችና መሳሪያዎች ላይ ይመሰረታል፡፡ ይህ ሀገር በቀል የሙዚቃ መሰረት ያለው የሙዚቃ ስልት፣ የኢትዮጵያን ባህላዊ ቅኝቶችና ሀገር በቀል ዜማዎች ከምዕራባውያኑ የሙዚቃ ስልቶችና መሳሪያዎች ጋር በማዋሃድ የተፈጠረ ነው፡፡

እውቁ የኢትዮ-ጃዝ ፈጣሪና የሙዚቃ ሳይንቲስቱ አርቲስት ሙላቱ አስታጥቄ፣ እ.አ.አ የካቲት 1 ቀን 2018 ለቢቢሲ በሰጠው ቃለ መጠይቅ እንደ ደራሼ ማህበረሰብ ያሉ የደቡብ ኢትዮጵያ ማህበረሰቦች ለኢትዮ ጃዝ ሙዚቃ መፈጠር መሰረት እንደሆኑ ተናግረዋል። አርቲስት ሙላቱ በደራሼ ብሄረሰብ የሙዚቃ መሳሪያዎች ጥናት ማድረጉን በማውሳት፣ እነዚህ ሕዝቦች ለበርካታ የአውሮፓውያን የሙዚቃ መሳሪያዎች መሰረቶች ናቸው። ትራምፔትንና ትሮምቦንን የሚመስሉ የሙዚቃ መሳሪያዎች አሏቸው። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የቤኒንሻንጉል የሙዚቃ መሳሪያ የሆነው ዙምባራ ነው ሲል፤ የደራሼና ሌሎች ማህበረሰቦች የዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ፈር-ቀዳጅነታቸውን አስታውሷል፡፡

አርቲስት ሙላቱ በኢትዮጵያ ማህበረሰቦች ውስጥ የሚገኙ የሙዚቃ መሳሪያዎች በዓለም የሙዚቃ እድገት ውስጥ ቁልፍ ሚና እንዳላቸው በማስገንዘብ፣ በሙዚቃ ስልቶቹና መሳያዎቹ ላይ የተደራጁ ሳይንሳዊ ጥናቶች ማድረግ ብሎም ተጠብቀው እንዲቆዩ ማስቻል ያስፈልጋል ብሏል፡፡

የኢትዮጵያ ሀገር በቀል ባህሎችና እሴቶች ሚና ትልቅ ነው፡፡ ለስነ ጽሁፍ፣ ለቴአትር፣ ለኪነ ህንጻ ጭምር መነሻዎች ናቸው፡፡ በሃመር ማህበረሰብ ባህልና ዕሴቶች ላይ ትኩረት ያደረጉት የፍቅረ ማርቆስ ደስታ ድርሰቶች፣ በ1860ዎቹ የሴቶች የመብት ጥያቄዎችን ይዛ በመነሳት የጉራጌን ማህበረሰብና ባህል የሞገተችው የቃቄ ወርድወት ህይወትና አስተሳሰብ የሚያንጸባርቀው ቴአትርና ድርሰት፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ የነባሩን ሕብረተሰብ ማህበራዊ መስተጋብርና ኢኮኖሚያዊ መሰረት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየው የታላቁ ደራሲ ሀዲስ አለማየሁ ፍቅር እስከ መቃብር ስራዎች ለዚህ ጥሩ ማሳያዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የኪነ ጥበብ ስራዎች፣ ከጥበባዊ ፋይዳቸው ባሻገር አንዱ ማህበረሰብ የሌላውን ማህበረሰብ ዕሴት እንዲያውቅና እንዲማር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳደረጉ ወሰን (ዶ/ር) አክለዋል፡፡

የባህል ብዝሃነት በተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ወጎች፣ እምነቶች እና ልማዶች በማክበር የሰውን የህይወት ልምድ ይበልጥ የሚያሳድግና ውበትን የሚጨምር የህብረተሰብ መሰረታዊ ገጽታ ነው። ኪነ ጥበባት ደግሞ የተለያዩ ማህበረሰቦችን ልዩ ማንነት የሚያንፀባርቁ የጥበብ ዕሴቶችና አገላለጾች መድረክን በማመቻቸት የባህል ብዝሃነትን በማስተዋወቅ እና በመጠበቅ በኩል ጉልህ ሚና ይጫወታሉ፡፡ እንደ ሙዚቃ፣ ውዝዋዜ፣ የእይታ ጥበባት፣ ስነ-ጽሁፍ እና ቴአትር ባሉ የተለያዩ የፈጠራ ስራዎች አማካኝነት ጥበባዊ ስራዎች የጋራ መግባባትን ይበልጥ ለማስተዋወቅ፣ በተለያዩ ባህሎች መካከል ውይይትን ለማዳበር እና የጋራ አቀራራቢ ትርክት በመቅረጽ ረገድ ኹነኛ መሳሪያ ሆነው እንደሚያገለግሉ ወሰን (ዶ/ር) ተናግረዋል፡፡

ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ የባህል ብዝሃነትን በማስተዋወቅና ውበትን በማጉላት ረገድ ኪነ ጥበባዊ ስራዎች ከሚጫወቱት ቁልፍ ሚና አንዱ የተለያዩ ባህላዊ አመለካከቶችን እና ልምዶችን በፈጠራ ስራዎች አማካኝነት እንዲወከሉ ማስቻል ነው። አርቲስቶች አንድን ማህበረሰብ የሚገልጹ እሴቶችን፣ እምነቶችን እና ወጎችን በፈጠራ አጎልብቶ በማንፀባረቅ የባህላቸውን ምንነት በስራዎቻቸው የመከሰት ችሎታ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

ኢኮኖሚ

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# ተቋማቱን በከተማ ግብርና ሚዛን

- **በ2012 በጀት ዓመት የከተማ ግብርና ተሳታፊዎች 157 ሺህ 502 የነበሩ ሲሆን በ2018 ወደ 1 ሚሊዮን 283 ሺህ 537 ከፍ ብለዋል**

**በይግለጡ ጓዴ**

የጋዜጣዋ ዝግጅት ክፍል የሽመልስ ሃብቴ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን በጎበኘበት ወቅት ትኩረቱን የሳበው የተማሪዎች የዕረፍት ሰዓት እንቅስቃሴ ወይም የግቢው የትምህርት ድባብ ብቻ አልነበረም። ከክፍል መማሪያዎች ጎን ለጎን በሥርዓት የተዘጋጁ የአትክልት ማሳዎች፣ በአረንጓዴ ቀለም የተሞሉ የሰላጣና የጎመን እርሻዎች፣ የዶሮዎች ድምፅና የእንስሳት እንቅስቃሴ ትምህርት ቤቱ ከተለመደው የመማሪያ ተቋም ከፍ ብሎ ወደ ምርት ማዕከል የተቀየረ መሆኑን በግልጽ ያሳያሉ።

ለዓመታት ጥቅም ሳይሰጥ የቆየው የትምህርት ቤቱ ክፍት ቦታ ዛሬ የሕይወት ምንጭ ሆኗል። በዚያ ቦታ የተተከሉ ሰላጣዎች እንደ አረንጓዴ ምንጣፍ ተዘርግተው ይታያሉ፤ ጎመንና ቆስጣ በተሟላ ሁኔታ አድገው የተመለከታቸውን ሁሉ ያስደምማሉ። ቃሪያ፣ ድንች፣ ስኳር ድንችና ሌሎች የጓሮ አትክልቶች ደግሞ ይህ ቦታ ከመማሪያ ክፍል ባለፈ የምርት ማዕከል መሆኑን ይመሰክራሉ።



ፎቶ- ከፋይል

በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ተቋማት እየተከናወኑ ካሉ የከተማ ግብርና ስራዎች መካከል ጥቂቶቹ

የግቢው አረንጓዴ ገጽታ ውበትን ብቻ አይገልጽም፤ በከተማ ውስጥ ያሉ ትንንሽ ክፍት ቦታዎች በአግባቡ ከተጠቀሙባቸው ለምግብ ዋስትና፣ ለቤተሰብ ገቢና ለአካባቢ አረንጓዴነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከት እንደሚችሉ በተግባር ያስረዳል። ተማሪዎችም በዚህ ግቢ ውስጥ ከመጽሐፍ እውቀት ባሻገር መሬትን በአግባቡ መጠቀም፣ ምርትን ማምረት፣ ምግብ እንዴት እንደሚመረት መረዳትና የሥራ ባህልን ማዳበር ይማራሉ።

ይህ ምስል በአንድ ትምህርት ቤት ብቻ የተገደበ አይደለም። በአዲስ አበባ በርካታ ትምህርት ቤቶች፣ ጤና ተቋማት፣ የመንግሥትና የግል ተቋማት ባላቸው ክፍት ቦታዎች የከተማ ግብርናን በማስፋፋት የራሳቸውን የምግብ ፍላጎት ከማሟላት ባለፈ ለገበያም ምርት እያቀረቡ ይገኛሉ። ይህም በከተማ ውስጥ ያለውን የምግብ አቅርቦት በማጠናከር እና የኑሮ ውድነትን ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ ነው።

የግብርና ኢኮኖሚ ባለሙያው አለሙ አባቡ (ዶ/ር) እንደሚገልጹት፣ በፍጥነት እየጨመረ ያለው የከተማ ሕዝብ ቁጥርና የኑሮ ውድነት የምግብ ዋስትናን ዋነኛ የፖሊሲ ጉዳይ አድርጎታል። በመሆኑም የከተማ ግብርና በተቋማት ደረጃ በስፋት መተግበሩ ከጊዜያዊ መፍትሔነት ባለፈ ዘላቂ የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ መሆን ይገባዋል። በተለይ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን በተግባር የሚያስተምሩ ማዕከላት በመሆናቸው ለዘርፉ ልዩ ትኩረት መስጠት እንዳለባቸውም ይጠቁማሉ።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተቋማትን የከተማ ግብርና ምርት ማዕከል አድርጎ ከማስቀጠል አንፃር በርካታ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። ትምህርት ቤቶች፣ ጤና ተቋማት፣ የመንግሥትና የግል መሥሪያ ቤቶች ያላቸውን ክፍት ቦታ ወደ ምርት መስክ በመቀየር ለምግብ ዋስትና፣ ለገቢ ፈጠራና ለአረንጓዴ ከተማ ግንባታ እያበረከቱ ነው። የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን መረጃም ትምህርት ቤቶች በዚህ ረገድ ግንባር ቀደም ሚና እየተጫወቱ መሆናቸውን ያሳያል።

በሽመልስ ሃብቴ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የጽዳት ሰራተኛ የሆኑት ወይዘሮ ሰብለ ተስፉ የዚህ ለውጥ ቀጥተኛ ተጠቃሚ ናቸው። ከዕለታዊ የሥራ ኃላፊነታቸው ጎን ለጎን በጓሮ አትክልት ልማትና በዶሮ እርባታ በመሳተፍ የተቋሙ የምርት ሂደት አካል ሆነዋል። በግቢው ውስጥ ሰላጣ፣ ጎመን፣ ቆስጣ፣ ቃሪያ፣ ድንች፣ ስኳር ድንችና ሌሎች አትክልቶች በተከታታይ እየተመረቱ ሲሆን፣ የተቋሙ ሠራተኞችም በቀጥታ ተጠቃሚ ሆነዋል።

"ማንኛውም ሰው ያለውን ትንሽ ክፍት ቦታ በአግባቡ ከተጠቀመበት የቤተሰቡን የአትክልት ፍላጎት በራሱ ማሟላት ይችላል" የሚሉት ወይዘሮ ሰብለ፣ ሰላጣና ቆስጣ የመሳሰሉ ምርቶች በትንሽ ቦታ ላይም በቀላሉ ማምረት እንደሚቻል ያስረዳሉ። ይህም ከገበያ ግዢ ወጪን ከመቀነስ ባለፈ የራስን ምግብ በራስ የማምረት ባህልን ያጎለብታል።

በትምህርት ቤቱ የትምህርት ቤት መሻሻል ምክትል ርዕሰ መምህር ኤፍሬም አስፋው እንደሚገልጹት፣ በ2016 ዓመተ ምህረት የተጀመረው የከተማ ግብርና ሥራ በትምህርት ቤት መሻሻል፣ መዋቅርና በግብርና ክበብ በኩል ተጠናክሮ ቀጥሏል። በሌማት ትሩፋት መርሃ ግብር የወተት ከብት፣ የዶሮና የእንቁላል ምርት እንዲሁም የጓሮ አትክልት ልማት በስፋት እየተከናወነ ነው፡፡

የሚመረቱት ቆስጣ፣ ጎመን፣ ቃሪያ፣ ድንችና ሌሎች ምርቶች በአካባቢው ለሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ምገባ ማዕከላት እየቀረቡ ነው። ይህም ተቋሙ ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ተቋማትም ድጋፍ የሚያደርግ የምርት ማዕከል መሆኑን ያረጋግጣልም ብለዋል።

እንደ ኤፍሬም አስፋው ገለጻ፣ ትምህርት ቤቱ ከ300 በላይ ዶሮዎች፣ ዘጠኝ የወተት ላሞችና 4 ፍየሎች አሉት። በቀጣይም የከብት ማድለብን በማስፋፋት የከተማ ግብርናውን የበለጠ ለማጠናከር ዝግጅት እያደረገ ይገኛል። ይህ ሥራ ተማሪዎችን ከመጽሐፍ እውቀት ባሻገር በተግባር የሚያስተምር እና የወደፊት የሥራ ባህልን የሚያዳብር መሆኑንም ጠቅሰዋል።

ልክ እንደ ሽመልስ ሃብቴ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በደጅ አዝማች ወንድይራድ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትም የከተማ ግብርና በተቀናጀ መንገድ እየተተገበረ ይገኛል። የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ካሱ ቱምሳ እንደሚገልጹት፣ ትምህርት ቤቱ የእውቀት መስጫ ብቻ ሳይሆን ምርት የሚፈጠርበት ተቋም እንዲሆን በትጋት እየተሠራ ነው። በግቢው ውስጥ የሚታዩት የአትክልት ማሳዎች፣ የእንስሳት እርባታ እና የንብ ማነብ ሥራዎች ይህንን እውነታ በተግባር ያረጋግጣሉ።

ግቢውን የሚጎበኝ ሰው በትምህርት ቤት ውስጥ እንዳለ ሳይሆን በሰፊ የእርሻ ማሳ ውስጥ እንዳለ ስሜት ይሰማዋል። ይህም ትምህርት ከመማሪያ ክፍል ወጥቶ በተግባር ሲተገበር ምን ያህል ውጤታማ እንደሚሆን የሚያሳይ ተጨባጭ ምሳሌ ነው። በጓሮ አትክልት፣ በእንስሳት ማድለብ፣ በወተት ከብት እርባታና በንብ ማነብ ዘርፎች የተገኘው ውጤት የተቋማዊ የከተማ ግብርና ስኬት ማሳያ ሆኗል።

በዚህ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ሥራ ፈላጊዎችም ተጠቃሚ ሆነዋል። በእንስሳት ማድለብ፣ በወተት ላሞች እርባታና በዶሮ እርባታ የሚከናወነው ሥራ ለ17 ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ፈጥሯል። በተቋሙ 48 የሚደልቡ በጎች፣ 5 በሬዎች፣ 600 የእንቁላል ጣይ ዶሮዎች፣ 1 ሺህ የስጋ ዶሮዎች፣ 7 የወተት ላሞች፣ 6 የንብ ቀፎዎች እና በ13 ሺህ ካሬ ሜትር ላይ የተለያዩ የጓሮ አትክልቶች ይገኛሉ። ይህም ተቋማዊ የከተማ ግብርና ከምግብ ዋስትና ባለፈ ለሥራ ፈጠራና ለገቢ ማሳደግ ያለውን አስተዋፅኦ ያሳያል።

የግብርና ኢኮኖሚ ባለሙያው አለሙ አባቡ (ዶ/ር) እንደሚገልጹት፣ የከተማ ግብርና በአንድ ተቋም ወይም በጥቂት ግለሰቦች የሚወሰን ሥራ ሳይሆን የመላው ከተማ የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ መሆን አለበት። በየተቋሙ ያሉ ክፍት ቦታዎች ወደ ምርት ሲቀየሩ የምግብ አቅርቦት ይጨምራል፣ የዋጋ ግሽበትን ለመቋቋም ይረዳል፤ በተጨማሪም ከተማውን አረንጓዴ እና ጤናማ ያደርገዋል።

በየካ ክፍለ ከተማ የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ጽሕፈት ቤት የእጽዋት ቡድን መሪ አቶ ተሾመ ካቡ እንደሚገልጹት፣ በ12 ወረዳዎች ውስጥ በ241 የመንግሥትና የግል ተቋማት የከተማ ግብርና ሥራ በተቀናጀ ሁኔታ እየተከናወነ ነው። በወረዳ 11 ሁለት የዶሮና የወተት ክላስተሮች እየተሰሩ ሲሆን፣ በወረዳ 9 ደግሞ ስምንት ሼዶች በመገንባት የእንስሳት እርባታን የማስፋፋት ሥራ እየተከናወነ ነው።

በትምህርት ቤቶች፣ በጤና ጣቢያዎች፣ በቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች፣ በግል ድርጅቶችና በሌሎች ተቋማት የከተማ ግብርና በፍጥነት እየተስፋፋ መሆኑንም አቶ ተሾመ ይገልጻሉ። በወረዳ 3 በሚገኝ የመንግሥት ጤና ጣቢያ በተለይ የእንስሳት እርባታና ንብ ማነብ ሥራዎች በስፋት እየተከናወኑ እንደሆነ ይጠቅሳሉ። የሙያ ድጋፍ፣ የግብዓት አቅርቦትና ተከታታይ ክትትል ለተቋማቱ እየተሰጠ መሆኑም የሥራውን ዘላቂነት እያጠናከረው ነው።

በአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ወንደወሰን አካሌ እንደሚገልጹት፣ በከተማ ግብርና ዘርፍ የተከናወኑ ሥራዎች በምርትና በምርታማነት ከፍተኛ ለውጥ አምጥተዋል። ለአብነትም በ2012 በጀት ዓመት 64 ሺህ 600 ቶን የነበረው ዓመታዊ ጠቅላላ ምርት በ2018 615 ሺህ 108 ነጥብ 3 ቶን ማድረስ ተችሏል። በተጨማሪም በመኸርና በመስኖ ልማት 7 ሺህ 165 ሄክታር መሬት በቋሚነት እየለማ በመሆኑ ዘርፉ እያደገ መምጣቱን ያሳያል።

ከለውጡ ወዲህ በከተማ ግብርና ዙሪያ በሕብረተሰቡ አመለካከት የተፈጠረው ለውጥም ተጠቃሽ ነው። በ2012 በጀት ዓመት በከተማ ግብርና ተሳትፎ 157 ሺህ 502 የነበረውን ቁጥር አሁን 1 ሚሊዮን 283 ሺህ 537 ተጠቃሚ ማድረስ ተችሏል። ከዚህ በተጨማሪ በመንግሥትና በግል 2 ሺህ 776 ተቋማት የተቀናጀ ዘመናዊ የከተማ ግብርና ሥራ ላይ ተሰፋፍቷል። እነዚህ ተቋማት ለሠራተኞቻቸው ምርት በማቅረብ፣ ማዕድ በማጋራት፣ ለአነስተኛ ደመወዝተኞች ተጨማሪ ገቢ በመፍጠርና የምግብ ወጪን በመቀነስ ጉልህ ሚና እየተጫወቱ ነው።

እንደ ኮሚሽኑ መረጃ፣ የከተማ ግብርናን ዘላቂ ለማድረግ የሌማት ትሩፋት ንቅናቄ ከፍተኛ ድርሻ አበርክቷል። በዚህ መርሃ ግብር 22 ክላስተሮች፣ 6 ግሪንሃውሶች፣ 8 የመኖ ማቀነባበሪያ ማዕከላት እና 107 የግብርና መሸጫ ሱቆች ተገንብተዋል። እነዚህ መሠረተ ልማቶች የምርት ሰንሰለቱን በማጠናከር፣ የግብዓት አቅርቦትን በማሻሻልና ለአምራቾች የገበያ ትስስር በመፍጠር የከተማ ግብርናን ከጊዜያዊ መፍትሔ ወደ ዘላቂ የልማት ስትራቴጂ እንዲሸጋገር አድርገዋል።

# ልጆች! የቴክኖሎጂ አጠቃቀማችሁ እንዴት ያለ ነው?

**በፋንታነሽ ተፈራ**



ፎቶ፡- ኤ አይ ቻትጂፒቲ
ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ በመጠቀም እውቀት መገብየት፣ ጤናንም መጠበቅ ያስፈልጋል

ሰላም ልጆች! እንዴት ናችሁ? ክረምቱን እንዴት እያሳለፋችሁ ነው? ከጓደኞቻችሁ ጋር በመጫወት፣ መጻሕፍትን በማንበብ፣ በስልክ ወይም በቴሌቪዥን የተለያዩ አስተማሪና አዝናኝ ቪዲዮዎችን ማየትን ጨምሮ በተለያየ መንገድ ልትሉ እንደምትችሉ ተስፋ እናደርጋለን፡፡

ልጆች! ስልክ ወይም ቲቪ ማየት በጣም ደስ ቢልም፣ ብዙ ሰዓት ስክሪን ላይ ማሳለፍ ጉዳት አለው። ዓይናችን እና ራሳችንን ሊያመን እንዲሁም ለሌሎች ጠቃሚ ጨዋታዎችና ለቤተሰባችን የምንሰጠውን ጊዜ ሊቀንስብን ይችላል። ታዲያ በምን መንገድ መጠቀም አለብን? ብዙ ሰዓት ማየትስ ምን ችግር ያመጣል?... በሚሉት ላይ የእናንተ ጓደኞች ያላቸውን ልምድና ጠቃሚ ምክር እንደሚከተለው አዘጋጅተንላችኋል።

ክርስቲያን ዘሪሁን እባላለሁ፡፡ ክረምት እንደመሆኑ መጠን ቤት ስሆን የእናቴን ስልክ እጠቀማለሁ፡፡ ሞባይል እና እጄ አይነጣጠሉም። ልጆችን የሚመለከቱ ተንቀሳቃሽ ምስሎችን አያለሁ፡፡ ለትምህርቴ አጋዥ የሆኑ ጽሁፎችን እያወረድኩ አነብበታለሁ። የማላውቃቸውን አዳዲስ ነገሮች እንዳውቅ አድርጎኛል፡፡ ነገር ግን እረፍት ላይ ስለሆንኩ ብዙ ጊዜ ስልክ ላይ አሳልፋለሁ፡፡ በዚህ ምክንያት ዓይኔን ያቃጥለኛል፡፡ ይቆረቁረኛል፡፡ ይህንንም ለእናቴ ነግሬያት ወደ ህክምና ቦታ ልትወስደኝ ቀጠሮ ይዛልኛለች፡፡

ዓይኔን መታመም ከጀመርኩ በኋላ አንዳንድ ጊዜ እንጂ አዘወትሬ አላይም። ስልክም ሆነ ቴሌቪዥን ስናይ የተለያዩ መረጃዎችንና እውቀቶችን እንደምናገኝ ሁሉ አጠቃቀማችንን ካላስተካከልን ጉዳት እንዳለውም ተረድቻለሁ። ስለዚህ ሌሎች ጓደኞቼም እንደ እኔ ዓይናችሁ እንዳይታመም ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጉ።

ራኬብ ታምሩ እባላለሁ፡፡ 13 ዓመቴ ነው። በክረምት ቤት እንደማሳለፌ በቴሌቪዥን ፊልም፣ የተለያዩ ድራማዎችን፤ በስልክ ደግሞ አጫጭር ምስሎችን አያለሁ። ለትምህርት ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችንም አነብባለሁ፡፡

ስልክም ሆነ ቴሌቪዥን የምጠቀመው በቀን ከ1 ሰዓት ላልበለጠ ጊዜ ነው፡፡ ይህን የማደርገው ቤተሰቦቼ በዚህ ላይ ለብዙ ሰዓት መቆየት ለዓይንና ለወገብ ህመም እንደሚያጋልጥ፣ እንዲሁም የስልክ ሱሰኛ እንደሚያደርግ ስለሚመክሩኝ ነው። እኔም በራሴ ያየሁት በቀን ብዙ ሰዓት ካየሁ ሌሊት ላይ እንቅልፍ አይወስደኝም፡፡ ከሌሎች ጓደኞቼ ጋርም ማውራትም ሆነ መጫወት ይደብረኛል፤ በዚህም ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብኝ ተረድቻለሁ፡፡

አማኑኤል ሁሴን እባላለሁ፡፡ 12 ዓመቴ ነው። የእረፍት ጊዜየን ከፋፍዬ እጠቀማለሁ። ቤት ውስጥ ስሆን ቴሌቪዥን ወይም ስልክ አያለሁ። የማየው ግን ቤተሰቦቼ ባስቀመጡልኝ ሰዓት ነው። ለምሳሌ፡-ክረምት ስለሆነ በየቀኑ ለ1፡00 ሰዓት ያህል እንዳይ ይፈቀድልኛል፡፡ የማያቸው ነገሮችም የካርቱን እና የአኒሜሽን ተንቀሳቃሽ ምስሎች፣ የልጆች ፊልም እና ለቀጣይ ትምህርቴ አጋዥ ነገሮችን ነው፡፡ ሌሎች ሰዓታትን የማሳልፈው በመጫወት፣ ታሪካዊ ቦታዎችን በማየት እንዲሁም ከቤተሰቦቼ ጋር ምግብ በመመገብና እንቅልፍ በመተኛት ነው፡፡

ብዙ ጊዜዬን ስልክ ወይም ቴሌቪዥን ላይ ባሳልፍ እስከ ዓይነ ስውርነት የሚደርስ ጉዳት ሊከሰትብኝ ይችላል ብዬ እፈራለሁ። ይህን ያልኩት የማውቀው የትምህርት ቤት ጓደኛዬ በዚህ ምክንያት ዓይኑን በመታመሙ ነው፡፡ ግንኙነቴ ስልክ ላይ ብቻ ከሆነ ከቤተሰቦቼ ወይም ከጓደኞቼ ነጥሎ ብቸኛ እንዳያደርገኝ እጠነቀቃለሁ። አንዳንድ ጊዜም የተለያዩ ቅንብሮች ስለሚለቀቁ የማይጠቅሙኝን ነገሮች ልመለከት ስለምችል በአዕምሮዬ ላይ ጉዳት ሊያስከትልብኝ ይችላል። ይህን እንዳደርግ ቤተሰቦቼ ጥሩ እገዛ ያደርጉልኛል፡፡

## የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም፡- የታሪክ እና የቅርስ ቤት




ልጆች፣ በዚህ የረፍት ጊዜ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየምን ብትጎበኙ በጣም የሚያስደስቱ ብዙ ነገሮችን ታያላችሁ። በዚያ የጥንት ሰዎች ቅሪቶች፣ ታሪካዊ ዕቃዎች፣ ውብ ሥዕሎች እና የተለያዩ ባህላዊ ዕቃዎች ይገኛሉ። እነዚህን በማየት የአገራችንን ታሪክና ባህል በቀላሉ መማር ትችላላችሁ።

ሙዚየሙ ውስጥ ያሉት የታሪክ ሀብቶች በጥንቃቄ ተጠብቀዋል፣ እናንተም በምቾት እንድትጎበኙ ሰፊ የመራመጃ መንገዶች፣ ግልጽ የመረጃ ሰሌዳዎች እና ንጹህ አካባቢ ተዘጋጅተዋል። ስለዚህ በዚህ የረፍት ጊዜ ከቤተሰባችሁ ወይም ከጓደኞቻችሁ ጋር ሙዚየሙን ጎብኙ፤ እየተዝናናችሁም አዲስ እውቀት ታገኛላችሁ።

# 10 ልዩነቶችን ፈልጉ







## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ምግቧ የሚጣፍጥ፤ ጦሯ የሚያብጥ ምንድ ናት?**

**መልስ፡-** ለ. ንብ

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ሲወስዱብኝ የምሰፋ?**

ሀ. ገንዘብ
ለ. ውሃ
ሐ. ጉድጓድ

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ::**

# የክረምቱ የዕውቀት ማዕድ

- **በዘንድሮው የክረምት የበጎ ፈቃድ የማጠናከሪያ ትምህርት መርሃ ግብር በ140 ትምህርት ቤቶች 56 ሺህ 708 ተማሪዎች እየተማሩ እንደሚገኙ ተጠቁሟል**

**በፋንታነሽ ተፈራ**



ፎቶ- በገነት ወንድሙ
በሚያዝያ 23 ቅድመ አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የማጠናከሪያ ትምህርት ሲማሩ

ሮዚና ጋሻው ትባላለች፡፡ ያገኘናት በሚያዝያ 23 ቅድመ አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የክረምት ማጠናከሪያ ትምህርት ስትማር ነው፡፡ አሁን እየተማረች ያለችው በቀጣይ የምትገባበትን የ7ኛ ክፍል ሲሆን የትምህርት አይነቶቹም እንግሊዘኛ፣ ሂሳብ፣ የህብረተሰብ ትምህርት፣ ስነ ዜጋና ስነ ምግባር እና አማርኛ የመሳሰሉት ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ ነግራናለች፡፡

"አሁን መማሬ የቀጣይ መደበኛ ትምህርቱ ቀላል እንዲሆን ያደርግልኛል። ሁሉ ነገር አዲስ እንዳይሆንብኝ ይረዳኛል፣ ጊዜዬንም በጨዋታ ከማሳለፍ ይልቅ እውቀትን ለመቅሰም ያግዘኛል" ስትል ሮዚና ትናገራለች፡፡

በዚሁ ትምህርት ቤት የማጠናከሪያ ትምህርቱን ሲከታተል ያገኘነው ሌላኛው ተማሪ የአብስራ ሳሙኤል ይባላል፡፡ የመደበኛ ትምህርቱን በህዝባዊ ሰራዊት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲከታተል እንደነበር ገልፆ፣ የክረምት የበጎ ፈቃድ ማጠናከሪያ ትምህርቱን ብቻ ለመከታተል በዚህ እንደተገኘ ነግሮናል፡፡

"ይህ የክረምት የበጎ ፈቃድ ማጠናከሪያ ትምህርት በተለይ የቀጣይ የ8ኛ ክፍል የሚኒስትሪ ተፈታኝ እንደመሆኔ መጠን ቀደም በመደበኛው ትምህርት የከበዱኝን ርዕሰ ጉዳዮች ጠይቄ ለመረዳት ይረዳኛል። ከዚህ በተጨማሪ ለትምህርቱ እንግዳ እንዳልሆንና በራስ መተማመኔ እንዲጨምር ያደርገኛል" ሲል መማሩ እንዳስደሰተው ተማሪ የአብስራ ይናገራል።

ማጠናከሪያ ትምህርቱ በበጎ ፈቃደኞች ያለ ክፍያ በነፃ መሰጠቱ ከእውቀት ባለፈ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ እንዳለው የሚገልጸው የአብስራ፣ "ክፍያ ቢኖረው ከቤተሰቦቼ አቅም አንፃር መማር አልችልም ነበር። ቤተሰቦቼንም ምን ከፍዬ ላስተምረው ከሚል ስጋት አሳርፏቸዋል" ሲል አብራርቷል፡፡

ተማሪዎቹ፣ የክረምት ማጠናከሪያ ትምህርት መማራቸው አዕምሯቸው ንቁና ዝግጁ ሆኖ እንዲቆይ፣ ዕውቀት ለመገብየት፣ አልባሌ ቦታ እንዳይውሉ እና በስነ ምግባር እንዲታነፁ እንዲሁም ከአዳዲስ ጓደኞች ጋር እንዲተዋወቁ በማድረግ ዘርፈ ብዙ ጥቅም እንዳስገኘላቸው ነው የነገሩን፡፡

መምህር ስምዖን አማረ በትምህርት ቤቱ በበጎ ፈቃድ የክረምት ማጠናከሪያ ትምህርት የ6ኛ ክፍል እንግሊዘኛና የ8ኛ ክፍል ህብረተሰብ የትምህርት አይነቶችን ሲያስተምሩ ነው ያገኘናቸው። በመደበኛው ስራቸው በግል ትምህርት ቤት ያስተምራሉ፡፡ የበጎ ፈቃድ የማጠናከሪያ ትምህርቱን መስጠት ከጀመሩ ሁለት ዓመት ሆኗቸዋል፡፡ "ይህንን ስራ ስጀምር እንደ አንድ መምህር ማህበራዊ ኃላፊነቴን እንደመወጣት በመቁጠር ነው፡፡ ልጆች መንገድ ላይ አንዳንድ ጊዜም አልባሌ ቦታዎች ሲያሳልፉ እመለከታለሁ፡፡ ለነዚህ ልጆች እውቀት ማስጨበጥና ጊዜያቸውን በትምህርት እንዲያሳልፉ የበኩሌን አስተዋጽኦ ማድረጌን ሳስብ ደስታ ይሰማኛል" ይላሉ፡፡

ተማሪዎች የበጎ ፈቃድ የክረምት ማጠናከሪያ ትምህርት መማራቸው ለቀጣዩ ክፍል የሚረዳቸውን እውቀት አስቀድመው እንዲይዙ ያደርጋቸዋል። አዲስ እንዳይሆንባቸውና የማንበብና የመጻፍ ክህሎታቸውን እንዳይረሱት ይረዳቸዋል፡፡ ይህ ሲሆን በመደበኛ ክፍል ሲገቡ በራስ መተማመናቸው እንዲጨምርና እንዳይቸገሩ በማድረግ ረገድ ትልቅ ሚና እንደሚጫወት ነው መምህር ስምኦን የነገሩን፡፡

የበጎ ፈቃድ ማጠናከሪያ ትምህርት ለተማሪዎቹ ከቀጣይ ትምህርት ዝግጅት የዘለለ ለወላጆችም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አለው የሚሉት መምህሩ፤ ይህም ወላጆች ለማጠናከሪያ ትምህርት ወጭ እንዳያወጡ እንዳደረጋቸው አብራርተዋል፡፡

መምህሩ በማጠቃለያ አስተያየታቸው፣ ገንዘብ ያለው በገንዘቡ፣ እውቀት ያለው በእውቀቱ እገዛ ሲያደርግ ተማሪዎቹ ደግሞ ትኩረት ሰጥተው ትምህርቱን መከታተል እንዳለባቸው መክረዋል፡፡

ሌላኛው አስተያየት ሰጪ መምህር ሁሴን መሀመድ ይባላሉ፡፡ ከ6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ስነ ዜጋና ስነ ምግባር ትምህርት በበጎ ፈቃደኝነት ያስተምራሉ፡፡ ጉዳዩን በማስመልከት በሰጡት አስተያየት፣ "ክረምት ሲመጣ በተለያዩ የበጎ አድራጎት ስራዎች እሳተፋለሁ፡፡ ለማህበረሰቡም አሻራዬን ማኖር እንዳለብኝ አምናለሁም። የማጠናከሪያ ትምህርቱ ተማሪዎች 2019 ዓ.ም ለሚጀምሩት ትምህርት መነሻ በመሆን ይጠቅማቸዋል፡፡ መደበኛው ትምህርት እንደ አዲስ ሳይሆን እንደ ክለሳ ይሆንላቸዋል፡፡

የሚቀጥለው ዓመት ትምህርት ይከብደኝ ይሆን ብለው አያስቡም፤ ግንዛቤው ኖሯቸው መደበኛውን ትምህርት በደስታ እንዲጀምሩና አልባሌ ቦታም እንዳይውሉ ያደርጋቸዋል" ብለዋል፡፡ በበጎ ፈቃደኝነት ማገልገል ከራስ ደስታ አልፎ ሌሎችን የሚጠቅምና ተሞክሮም የሚሆን እንደሆነም አክለዋል።

መምህርት ሉባባ ኢብራሂምን ያገኘናቸው በትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማር ስርዓቱን ሲያስተባብሩ ነው። እንደ እርሳቸው ገለጻ፣ በትምህርት ቤቱ 600 የሚሆኑ ተማሪዎች የዘንድሮውን የክረምት በጎ ፈቃድ የማጠናከሪያ ትምህርት በመውሰድ ላይ ናቸው። አሁን እየተሰጠ ያለው የማጠናከሪያ ትምህርት ተማሪዎች ወደ መደበኛው ክፍል ሲገቡ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያደርግ ነው፡፡ ሂሳብና እንግሊዘኛ ላይ ከሌሎች በበለጠ ትኩረት በማድረግ በሳምንት አራት ክፍለ ጊዜ እየተሰጠ ይገኛል፡፡

> **"እየተሰጠ ያለው የማጠናከሪያ ትምህርት ተማሪዎች ወደ መደበኛው ክፍል ሲገቡ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያደርግ ነው። ሂሳብና እንግሊዘኛ ላይ ከሌሎች በበለጠ ትኩረት በማድረግ በሳምንት አራት ክፍል ጊዜ እየተሰጠ ይገኛል"**

ወይዘሮ ዓለም አለሽኝ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት፣ በትምህርት ቤቱ የበጎ ፈቃድ የክረምት ማጠናከሪያ ትምህርት ሁለት ልጆቻቸውን ያስተምራሉ፡፡ ልጆቻቸው የ4ኛ እና 8ኛ ክፍል ተማሪ ሲሆኑ የማጠናከሪያ ትምህርቱ ለቀጣይ የመደበኛ ትምህርታቸው እንዲዘጋጁና አልባሌ ቦታ እንዳይውሉ እንዳደረጋቸው ገልጸዋል፡፡

"በክፍያ ቢሆን ማስተማር አልችልም ነበር፡፡ በነፃ በመሆኑ እኔን 'ከምን አምጥቼ ልክፈል' ከሚል ጭንቀት ገላግሎኛል። ልጆቼም እውቀታቸውን ማሳደግ የሚችሉበትን እድል ፈጥሮላቸዋል" በማለት አብራርተዋል፡፡

በበጎ ፈቃደኝነት ያለምንም ክፍያ ለልጆቻቸው እውቀታቸውን የሚያካፍሉ፣ የመደበኛው ትምህርታቸው አዲስ እንዳይሆንባቸው የሚያግዙ መምህራንንና በተግባሩ ላይ ተሳታፊ የሆኑ አካላት ሊመሰገኑ እንደሚገባቸውም አክለዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን የበጎ ፈቃድ ግንዛቤ ማስረፅ ቡድን መሪ አቶ ቢኒያም ጊቻ ለጋዜጣው ዝግጅት ክፍል በሰጡት ማብራሪያ፤ በጎ ፈቃደኝነት ዜጎች በራሳቸው ተነሳሽነት ለማህበረሰቡ የሚያደርጉት ተግባር ነው፡፡ ያለምንም ክፍያ መልካም በማሰብ ብቻ የሚፈጸም ነው፡፡ ኮሚሽኑም በዋናነት በከተማዋ የበጎ ፈቃድ ተግባራትን የማስተባበር፣ ነዋሪዎች እንዲሳተፉ፣ እንዲጠቀሙ እንዲሁም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ባህል እንዲሆን እየሰራ ይገኛል ብለዋል፡፡

በክረምት ከሚከናወኑ የበጎ ፈቃድ መርሃ ግብሮች ውስጥ የማጠናከሪያ ትምህርት አንዱ መሆኑን የገለፁት አቶ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

## የቅጥርማስታወቂያ

### የአዲስሚዲያኔትዎርክከዚህበታችበተገለፁትክፍትየስራመደቦችላይአመልካቾችንአወዳድሮለመቅጠርይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የሥራ መደብመጠሪያ | ደረጃ | ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ | አግባብ ያለው የሥራ ልምድ | የሙያ ዓይነት | መደብ መታወቂያ ቁጥር | ብዛት | የቅጥር ሁኔት | ደመወዝ | የሥራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ለቢዝነስና ገበያ ልማት ዘርፍ | | | | | | | |
| 1 | ከፍተኛ የብራንዲንግ ባለሙያ | IX | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 6/4 ዓመት | በማርኬቲንግማኔጅመንት፣ በኢኮኖሚክስ፣ በቢዝነስ ማኔጅመንትና ተመሳሳይ የትምህርት መስክ ወይም በተዛማጅ የትምህርት መስክ | አ/18.1069 | 1 | ቋሚ | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ.አ |

1. አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 /አስር/ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የትምህርት ማስረጃችሁን ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ በመያዝ በተቋሙ የሰው ኃብት ስራ አመራር እና ልማት ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 05 ድረስ በመምጣት እንድትመዘገቡ እናሳስባለን፡፡
2. ከግል ድርጅቶች የሚቀርብ የስራ ልምድ ማስረጃ የስራ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ማስረጃ ማምጣት ይኖርባቸዋል፡፡
3. የስራ ልምድ የሚጠይቀው ከወጣው ክፍት መደብ ጋር ቀጥተኛ መሆን አለበት፡፡
4. የምዝገባው ቀን ነሐሴ 04 ቀን 2018 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 15 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ
5. የፈተና ቀን በውስጥ ማስታወቂያ ይገለፃል፡፡
6. ለበለጠ መረጃ አድራሻ አምስት /5/ ኪሎ ቅድስተ ማርያም ፊት ለፊት ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጐን ስልክ 0111551848

**አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ**

## የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

### የግዢ ጨረታ መለያ ቁጥር 001/2019 ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤት ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት

ሎት.1 የአላቂ የቢሮ እቃዎች ሎት 2. የጽዳት እቃዎች ሎት3. የደንብ ልብስ እቃዎች ሎት 4. የህትመት ዉጤቶች ሎት 5. የመስተንግዶ አገልግሎቶች ሎት 6. የመኪና እቃዎች ሎት 7. የትራንስፖርት አገልግሎት.

ጨረታውን ለመሳተፍ የሚፈልጉ ሕጋዊ ተጫራቾች የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆን አለባቸዉ፡፡

1. ተጫራቾች በዘርፉ የተሰማሩበት ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸውና የዘመኑን ግብር ለመክፈላቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
2. በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በአቅራቢነት የተመዘገበና ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፡፡
3. የታደሰ የንግድ ፍቃድ ያለው፡፡
4. የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል፡፡
5. ተጫራቾች ከዚህ በታች የተጠቀሰውን የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ C.P.O ማቅረብ አለባቸው፡፡

| ሎት ቁጥር | ሎት ዝርዝር | የተጠየቀው የጨረታ ማስከበሪያ በኢትዮጵያ ብር |
|---|---|---|
| ሎት 1. | አላቂ የቢሮ እቃዎች ለሎት 1. አላቂ የቢሮ እቃ | 15,000.00ብር |
| ሎት 2 . | የጽዳት እቃዎች ለሎት 2. ጽዳት እቃዎች | 25,000.00ብር |
| ሎት 3. | የደንብ ልብስ ለሎት 3. ደንብ ልብስ እቃዎች | 25,000.00ብር |
| ሎት 4 . | የህትመት ውጤቶች ለሎት 4. የህትመት ውጤቶች | 10,000.00 ብር |
| ሎት 5 . | መስተንግዶ ለሎት 5. መስተንግዶ እቃዎች | 5,000.00ብር |
| ሎት 6. | የመኪና እቃዎች ለሎት 6. የመኪና እቃዎች | 10,000.00 ብር |
| ሎት 7. | የትራንስፖርት ለሎት 7. የትራንስፖርት | 5,000.00 ብር |

6. የጨረታ ሰነዱን ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በየሎቱ የማይመለስ ብር 200.00/ሁለት መቶ ብር በመክፍል የተዘጋጀውን ሰነድ ከፋይናንስ ጽ/ቤት ከተቋሙ ቢሮ እየቀረቡ መግዛት ይችላሉ፡፡
7. ተጫራቾች ጨረታ ከወጣበት ቀን አንስቶ ባሉት 10/አሥር/ተከታታይ የስራ ቀናት 2ኛ ፎቅ ፋይናንስ ጽ/ቤት የተዘጋጀውን ሰነድ መግዛት ይቻላሉ፡፡ በእያንዳንዱ ሰነድ እና መረጃ ላይ ማህተም በመምታት ዋጋው የተሞላበትን የጨረታ ሰነዱን ኦሪጅናሉንና ኮፒውን በተለያዩ ማሸጊያዎች በማሸግ ፖስታው ላይ ኦሪጅናል ብሎ በመጻፍ ኮፒዉን ኮፒ ብሎ በመጻፍ በተጨማሪ ሁለቱንም ፖስታዎች በአንድ ፖስታ በማሸግ የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡
8. ጨረታው በ10ኛው ቀን ከቀኑ 10፡00 ሰዓት ላይ ተዘግቶ በ11ኛው ቀን ከጧቱ 4፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡ የጨረታው መዝጊያና መክፈቻ የስራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተሰጠው ተመሳሳይ ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
9. ተጫራቾች ያሸነፉበትን ዋጋ የውል ማስከበሪያ 10% ማስያዝ አለባቸው፡፡
10.ተጫራቾች ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ለሚወዳደሩበት ናሙና ለሚቀርብባቸው ዕቃዎች ናሙና ማቅረብ አለባቸው፡፡
11. ተጫራቾች ባሰገቡት ናሙና መሰረት እቃዎች የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡ ይህ ሆኑ ካለተገኘ ከናሙና ውጪ ያመጡ ተጫራቾች ንብረታቸዉ ሙሉ በሙሉ ተወርሶ ለአስተዳደር ገቢ ይደረጋል፡፡
12. የጨረታ አሸናፊ ድርጅት ያሸነፈበትን እቃዎች በ5 ቀናት ውስጥ ለመስረያ ቤቱ በራሱ ትራንስፖርት ማስረከብ ይኖርበታል፡፡
13. መ/ቤቱ ለጨረታ ከቀረበው እቃ እስከ 20% የመቀነስም ሆነ የመጨመር መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
14. መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
15.ለጨረታ ያሰገቡትን ናሙና 6 ወር ከሞላ ወደ ወረዳዉ አስተዳደር ገቢ ይደረጋል፡፡
16.ወቅታዊ /ወርሃዊ/ የቫት (የተጨማሪ እሴት ታክስ) ለገቢዎች ጽ/ቤት ያሳወቁበትን የሚያረጋግጥ የሰነድ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡

አድራሻ፡- ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤት ከአትላስ ሆቴል ወደ ውሰጥ ገባ ብሎ ሻላ መናፈሻ አጠገብ

ለበለጠ መረጃ፡- ስልክ ቁጥር 0116-63-93-38

**ማሳሰቢያ፡- በመጨረሻም የጨረታ ሳጥን የሚገኝበት ቦታ ጨረታው ከተዘጋ በኃላ የሚቀርብ የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት የለውም፡፡**

**የቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤት**

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# መዲናዋ ከ“ፅዱ ኢትዮጵያ” ንቅናቄ ምን አተረፈች?

- **3ኛው የፅዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄ፤ ከሐምሌ ጀምሮ በመከናወን ላይ እንደሚገኝ ተጠቁሟል**

በለይላ መሀመድ



ፎቶ- ከገፀ ድር
ከተማዋን ጽዱ እና ውብ ለማድረግ ከተሰሩ ስራዎች ጥቂቶቹ

## እንደ መግቢያ

የአዲስ አበባ የቀደመ ገጽታ በተፈጥሮ ሀብት የበለጸገችና የተዋበች በሚል የሚገለጽ ነበር። ለአብነትም፡- የንጹህ ወንዞች፣ የጥቅጥቅ ደኖች፣ የተለያዩ አእዋፍት ዝርያዎች መኖሪያ ከተማ ነበረች። 76 የሚደርሱት ወንዞቿ ለመጠጥና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ፣ ዳርቻቸው በጥቅጥቅ ዕፅዋት የተሸፈነ፤ የተለያዩ የዱር እንስሳት እና አእዋፍትም በብዛት የሚታይባቸው ነበሩ። እንደ እንጦጦ፣ የካ ተራራ እና ሌሎች አረንጓዴ ስፍራዎች የከተማዋን የአየር ጥራት ይጠብቁ ነበር፡፡ ከ3 ሺህ ሜትር በላይ ርዝመት ባላቸው ተራሮች የተከበበች ድንቅ ከተማ እንደሆነችም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በተለያየ ጊዜ ያወጣቸው መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

ከጊዜ ወደ ጊዜ የህዝብ ቁጥር መጨመር፣ ያልተቀናጀ ልማት በተለይም ፋብሪካዎች፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በሚለቅቋቸው ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻዎች ሳቢያ አደገኛ ቆሻሻ የተከማቸባት ከተማም ሆና ቆይታለች፡፡ ሳይንሳዊ ያልሆነ የቆሻሻ አያያዝ፣ አወጋገድ እና የወንዞች ዳርቻ ወረራ ተደማምሮ ተፈጥሮ በቸራት ጸጋዎቿ ላይ ጫና ፈጥረውባት ቆይተዋል።

ታዲያ ከዚህ ወጥታ ወቅቱን በሚዋጅ ቁመና ላይ ትገኝ ዘንድ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል። ለዚህ የ“ፅዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄ”ን በማሳያነት ማንሳት ይቻላል። መርሀ ግብሩ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሀሳብ አመንጪነት እና አነሳሽነት በ2016 ዓ.ም በይፋ መጀመሩ ይታወሳል። የንቅናቄው ዓላማ በከተሞች የሚታዩ የፅዳትና የንጽህና ችግሮችን መቅረፍ እና ከባቢያዊ ደህንነትን መጠበቅ ነው።

አዲስ አበባ ያላትን የተፈጥሮ ሀብት ከዘመናዊ የከተማ ልማት ጋር እንዲጣጣም ማድረግ የሁሉም ኃላፊነት ነው። የ“ፅዱ ኢትዮጵያ” ንቅናቄ ዓላማም ይሄው እንደሆነ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ስራ አስኪያጅ እሸቱ ለማ (ዶ/ር) የ3ኛው ዙር “ጽዱ ኢትዮጵያ ለትውልድ” በሚል መሪ ሀሳብ ለሶስት ወራት የሚካሄደውን ዘመቻ ይፋ ለማድረግ በተዘጋጀው መድረክ ላይ ገልጸዋል፡፡

## የንቅናቄው አስፈላጊነት እና ዓላማ

እንደ ዋና ስራ አስኪያጁ እሸቱ (ዶ/ር) ገለጻ፤ የከተሞች ፈጣን እድገት እና የህዝብ ቁጥር መጨመር ከተገቢው የቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት ጋር ካልተጣጣመ በጤና፣ በኢኮኖሚ እና በአካባቢ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳል። ንቅናቄው ይህንን ጉዳይ አጣጥሞ ለማስኬድ ሁነኛ መፍትሄ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የንቅናቄው ዓላማና አስፈላጊነት በቆሻሻ መከማቸት ምክንያት የሚመጡ ተላላፊ በሽታዎችን መቀነስ እና የጽዳት ባህልን በማሳደግ የዜጎችን ጤንነት ማረጋገጥ፣ አካባቢዎችን ፅዱ በማድረግ ለነዋሪዎች ምቹ ከባቢ መፍጠር እንዲሁም የአካባቢ ውበትን እና መስህብነትን በማሳደግ ለቱሪዝም እና ለኢንቨስትመንት ሳቢ እንዲሆን ማድረግ፣ ጽዳትን የዕለት ተዕለት የኑሮ ዘይቤ እና ባህል በማድረግ እያንዳንዱ ዜጋ ለአካባቢው ጽዳት ባለቤት እንዲሆን ማስቻል ነው፡፡ በተጨማሪም የቆሻሻ መልሶ መጠቀም ስርዓትን በማጠናከር ቆሻሻን ዝም ብሎ ከመጣል ይልቅ እንደገና ጥቅም ላይ የሚውልበትን እና ወደ ኢኮኖሚ ሀብት የሚቀየርበትን አሰራር መዘርጋት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

## በባለፉት ፅዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄ ፕሮግራሞች ምን ተሰራ?

ዋና ስራ አስኪያጁ እሸቱ (ዶ/ር)፤ የፅዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በአዲስ አበባ ከተማ በርካታ በተግባር የተደገፉ ስራዎች መከናወናቸውን ያነሳሉ። የብክለት መከላከል ዘመቻዎች ለምሳሌ፡- የፕላስቲክ ወይም ፌስታል ብክለትን መከላከል፣ የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝ፣ የድምፅ ብክለትን ለመቀነስ ሰፋፊ የቁጥጥር ስራዎች ተከናውነዋል።

ባለፉት ሁለትና ሶስት ዓመታት የወንዝና ወንዝ ዳርቻ በማጽዳት እና በማልማት፣ በአረንጓዴ አሻራ ረገድ አበረታች ስራዎች ተሰርተዋል። እንዲሁም በንቅናቄው በመዲናዋ የተለያዩ አካባቢዎች ዘመናዊ፣ ንጹህና የነዋሪዎችን ክብር የሚጠብቁ በርካታ የማህበረሰብ መጸዳጃ ቤቶች ተገንብተው ለአገልግሎት እንዲውሉ ተደርጓል። የአዲስ አበባን የተፈጥሮ ገጽታ ለማሻሻል የመናፈሻ ስፍራዎች ግንባታ እና የዛፍ ተከላ መርሃ ግብሮች ተከናውነዋል፤ እየተከናወኑም ነው።

ባለፉት ሁለትና ሶስት ዓመታት ንቅናቄው ከተጀመረ በኋላ በተሰራው የክትትልና ቁጥጥር ስራ ከድምጽ፣ ከአደገኛ ቆሻሻና ከፕላስቲክ ብክለት ጋር ተያይዞ 17 ሺህ 171 ተቋማት ላይ ቁጥጥር ብቻም ሳይሆን የእርምት እርምጃ በመውሰድ እንዲያስተካክሉ ተደርጓል፡፡ ተቋማት ካርቦንዳይኦክሳይድን ከመቀነስ አንጻር ከግብርና፣ ከኢንዱስትሪ እና ከትራንስፖርት አንጻር ቅነሳ እንዲያደርጉ ተደርጓል፡፡

## የመጡ ተጨባጭ ውጤቶች

የአዲስ አበባ ከተማን ገፅታ የለወጡ ተጨባጭ ለውጦች መጥተዋል። የከተማዋን ገጽታ የለወጡ መናፈሻዎች፣ የህፃናት መጫወቻዎች እና የንፅህና መጠበቂያ ተቋማት ተገንብተዋል። መዲናዋ ጽዱ እንድትሆን አስተዋጽኦ ያደረገው ሌላው ተጨባጭ ውጤት የወንዝና ወንዝ ዳርቻ ልማት ነው፡፡ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞም በአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር በርካታ ችግኞችን መትከል ብቻም ሳይሆን የጽድቀት መጠናቸው እንዲያድግ ጥረት ተደርጓል። በ2018 በጀት ዓመት የጽድቀት መጠን ከ85 በመቶ በላይ ማድረስ መቻሉን ዋና ስራ አስኪያጁ እሸቱ (ዶ/ር) በማሳያነት ገልጸዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከትራንስፖርት፣ ከኢነርጂ፣ ከደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ፣ ወደ አየር የሚለቀቁ ጋዞች እንዲቀንሱ ከማድረግ አንጻርም ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በዚህም ባለፉት ሁለት ዓመታት 1 ሚሊየን 290 ሺህ ቶን ካርቦንዳይ አክሳይድ መቀነስ ተችሏል፡፡ ለውጡ ሊመጣ የቻለው በሁሉም ሴክተሮች የተጠናከረ ስራ በመሰራቱ ነው፡፡ የፕላስቲክ ብክለትን ለመከላከልም 45 የሚሆኑ ፌስታል አምራች ተቋማት ምርታቸውን ወደ ሌላ እንዲቀይሩ የማድረግ ስራም ተሰርቷል።

ንቅናቄው በህብረተሰቡ ግንዛቤ ላይም ተጨባጭ ውጤት አምጥቷል፡፡ ቆሻሻን ያለአግባብ አለመጣል እና አካባቢን በጋራ የማጽዳት ልማድ በህብረተሰቡ፣ በትምህርት ቤቶች እና በተቋማት ዘንድ እያደገ መጥቷል። የአካባቢ ጥበቃ ህጎችን በመጣስ እና አካባቢን በመበከል ጥፋተኛ ሆነው በተገኙ አካላት ላይ ተጠያቂነትን የማስፈን እና ህግን የማስከበር ስራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ተደርጓል። የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት አዲስ አበባ የተሻለ ደረጃ ላይ እንድትቀመጥ አድርጓታል። በአረንጓዴ ልማት እና በአካባቢ ጥበቃ ባሳየቻቸው ተከታታይ ስኬቶች ምክንያት 32ኛውን የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ጉባዔን እንድታስተናግድ ለመመረጥ ትልቅ አስቻይ ሁኔታ ፈጥሯል። እንዲሁም በዓለም ላይ ከሚገኙ 16 ከተሞች መካከል አዲስ አበባ አየሯ ንጹህ ነው በሚል የብሪዝ ሲቲስ አባል ሀገር የመሆን እድል እንድታገኝ አድርጓታል፡፡

## የፅዱ ኢትዮጵያ 3ኛ ዙር ንቅናቄ

የአንድ ሀገር ዕድገት እና የህዝቦቿ የኑሮ ደረጃ የሚለካው በኢኮኖሚ ግንባታ ብቻ ሳይሆን በአካባቢ ጽዳት እና በህዝቧ የጤና ሁኔታ ጭምር ነው። እየተተገበረ የሚገኘው ፅዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄ አዲስ አበባ ከቆሻሻ የጸዳች፣ ለኑሮ የተመቸች እና ለዜጎቿ ጤና ተስማሚ የማድረግ ታላቅ ርዕይ አለው። ለዚህም ነው ፅዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄን ለሶስተኛ ጊዜ ማዘጋጀት ያስፈለገው፡፡

ዋና ስራ አስኪያጁ እሸቱ (ዶ/ር)፣ ባለፉት ዘመቻዎች የተገኘውን ውጤት ለማስቀጠል እና አሁንም በመዲናዋ አዲስ አበባ ያሉ የተለያዩ ብክለቶችን ለማስወገድ “ፅዱ ኢትዮጵያን ለትውልድ” በሚል መሪ ሀሳብ ለሶስት ወር ስለሚቆየው ዘመቻና በመርሀ ግብሩ ትኩረት ተሰጥቷቸው ስለሚሰሩ ስራዎች ገልጸዋል።

የጽዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄ መርሀ ግብር በሀምሌ ወር የፕላስቲክ ብክለትን ማስወገድ ላይ መሰረት ያደረገ የንቅናቄ ስራ ይሰራል። ፌስታል ከ500 ዓመት በላይ ሳይበሰብስ የሚቆይ ለአየር፣ ለአፈርና ለውሃ ብክለት ምንጭ ነው፡፡ ብክለቱም በሰው ልጅ ጤና ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳርፍ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ፕላስቲክ ከረጢት ወይም ፌስታል ሲጠቀም፣ ሲያመርት እና ሲያከፋፍል የተገኘ ላይ አስፈላጊው እርምጃ ይወሰዳል፡፡

ነሀሴ ወር ደግሞ አደገኛ ቆሻሻ ማስወገድ ላይ ያተኮረ ስራ ይሰራል። አደገኛ ቆሻሻ የተለዩትን የማስወገድና ተጨማሪ የመለየት ስራ ይሰራል። ሶስተኛ ወር (መስከረም) ላይ ደግሞ የድምጽ ብክለት ላይ ትኩረት ተደርጎ ይሰራል፡፡ ከፍተኛ የድምጽ ብክለት የሚያስከትሉ 29 ሺህ 760 ተቋማት መሆናቸውን የመለየት ስራ ተሰርቷል። በንቅናቄው በእነዚህ ተቋማት ላይ የእርምት እርምጃ እና ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ይሰራል። ህብረተሰቡ ባለበት አካባቢ ሆኖ ያለውን የብክለት ችግር በፎቶ፣ ቪዲዮ እና ጽሑፍ በቀጥታ ለአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጥቆማ የሚያደርስበት የሞባይል መተግበሪያ ተሰርቷል፡፡ ከጥቆማው በኋላም የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል።

## የዜጎች እና የተለያዩ አካላት ሚና

ለ“ፅዱ ኢትዮጵያ” ንቅናቄ ስኬታማነት የመንግስት ጥረት ብቻ በቂ አይሆንም። የሁሉንም አካላት የተቀናጀ ጥረት ይጠይቃል። የእያንዳንዱ ዜጋ ቆሻሻን ያለአግባብ ከመጣል መቆጠብ፣ የራሱን መኖሪያ እና የስራ ቦታ ማፅዳት እና በየአካባቢው በሚደረጉ የጽዳት ዘመቻዎች ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆን አለበት። የኃይማኖት ተቋማት አስተምህሮቶችን በመስጠት፣ አባላቶቻቸውን በማስተባበር እና የፅዳት ባህልን በትውልድ ዘንድ በመቅረፅ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከት ይኖርባቸዋል። የግል ባለሀብቶች እና ድርጅቶች በጽዳት እና በቆሻሻ አወጋገድ ቴክኖሎጂዎች ላይ መዋዕለ ንዋያቸውን በማፍሰስ እንዲሁም የማህበራዊ ኃላፊነታቸውን በመወጣት ንቅናቄውን በፋይናንስ እና በቁሳቁስ መደገፍ መቻል አለባቸው።

በዚህ 3 ወር ጊዜ ውስጥ እነዚህን አደጋኛ ቆሻሻዎች የማስወገድ ስራ በጋራ የሚሰራ ሲሆን ከብክለት የጸዳች አዲስ አበባ እንድትፈጠር ሁሉም የድርሻውን መወጣት ይኖርበታል፡፡ ፅዱ አካባቢ የጽዱ አዕምሮ እና የጤናማ ህይወት መሰረት ነው።

## ወሳኙ ... ከገጽ 7 የዞረ

እጣፈንታና የወደፊት ተስፋ ሙሉ በሙሉ የሚወስን አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ጭምር ነው። ትናንት አባቶቻችንና እናቶቻችን በዓድዋ ለሀገር ነጻነት፣ ሉዓላዊነትና ክብር ሲሉ በደማቸውና በአጥንታቸው እንደተዋደቁላት ሁሉ፣ ዛሬም ኢትዮጵያ የታሪክ አደራ የሚሸከሙ የቁርጥ ቀን ልጆቿን ትፈልጋለች። ዛሬ ሀገራችን የምትሻው በሀሳብ ብስለት፣ በእውነት፣ በዕውቀትና በጽናት ታጥቀው የተሰናዱ የሰላም ታጋዮችን ነው።" በማለት ምክክሩ ለዘመናት የአለመግባባት ምክንያት የሆኑ ችግሮችን በመፍታት ሀገርን ወደተሻለ ደረጃ ማድረስ እንደሚያስችል ጠቁመዋል፡፡

የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ መኮንን (ዶ/ር) እንደሚያስረዱት፣ ሀገራዊ ምክክሩ ውጤታማ እንዲሆን ከሚያስፈልጉ ነገሮች አንዱ የፖለቲካ ፈቃደኝነት ነው፡፡ ይህም ከመንግስት ጀምሮ የተለያዩ ተዋንያንና ህዝቡ "በሀገራችን ያለው አለመግባባት እርስ በርስ እንድንገዳደል አድርጎናል፤ ሀገራችንን ወደኋላ አስቀርቷታል፤ ይህንን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መቅረፍ አለብን" የሚል የፖለቲካ ቁርጠኝነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህ በመኖሩ አሁን ላይ ሂደቱን የሚያስተባብር ተቋም እንዲቋቋም ተደርጎ ሀገራዊ ምክክር እየተካሄደ ይገኛል፡፡

የምክክሩ ሂደት አካታች መሆን ሌላው ለውጤታማነቱ ወሳኝ ጉዳይ ነው። በምክክሩ የሁሉም ባለድርሻ አካል ፍላጎት መካተት አለበት፡፡ በምክክሩ ሂደት መተማመን፣ ግልጽነት፣ የህዝብ ባለቤትነት መኖር አለበት፡፡ የሚገኙ ምክረ ሀሳቦችን መተግበርም ለምክክሩ ውጤታማነት አስፈላጊ ነው፡፡ ምክክር በአንዴ ተደርጎ የሚጠናቀቅ አይደለም፤ በተከታታይ መቀጠል አለበት። ወደፊትም ችግር ሲከሰት በጦርነት ሳይሆን በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጦ የመወያየት ልምድ መኖር እንዳለበት የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ መኮንን (ዶ/ር) ያስረዳሉ፡፡

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ሰብሳቢ መስፍን አርዓያ (ፕሮፌሰር) የሀገራዊ ምክክር ጉባኤውን ሂደት በተመለከተ ሐምሌ 24 ቀን 2018 ዓ.ም መግለጫ በሰጡት ወቅት እንደተናገሩት፣ ተመካካሪዎች በቅርበት፣ በመከባበር እና በግልጽነት እየተመካከሩ ይገኛሉ። በትናንሽ ቡድኖች ደረጃ በሚካሄዱ ምክክሮች ኩርፊያና ግጭት መከሰቱ የሚጠበቅ ነው። ይህ ምዕራፍ ሁሉም አካል የያዘውን ጥያቄ የሚያቀርብበት እና መደማመጥ የሚጀመርበት በመሆኑ አልፎ አልፎ የሚነሱ እሰጣ ገባዎች መኖራቸው አስፈላጊና ተፈጥሯዊ ነው። በተጨባጭ ግን ያን ያህል የከፋ ችግር አላጋጠመም፤ ምክክሩ በጥሩ ሁኔታ እየሄደ ይገኛል። በሂደት የተሻለ መግባባት እየተፈጠረ እንደሚሄድ እና የዓመቱ መጨረሻ ከማለቁ በፊት በተወሰኑ አጀንዳዎች ላይ መግባባት ተደርሶ ለአዲሱ ዓመት ትልቅ ብስራት ሊሰማ እንደሚችል ጠቁመዋል።

## የሉዓላዊነት ... ከገጽ 8 የዞረ

ቢፈጠር አሊያም በሀገሪቱ የጦር ሰፈር የመሰረቱ ሀያላን ሀገራት መካከል የእርስ በርስ ሽኩቻ ቢፈጠር በኢትዮጵያ የወደብ አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ ማምጣቱ አይቀሬ ነው፡፡

ባለፉት ሶስት አስርት ዓመታት ያለው ሁኔታ እንደሚያመላክተው፣ ቀይ ባህር ከኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ጠቀሜታ አኳያ ተፈላጊነቱ እየጨመረ መጥቷል፡፡ ከዚህ የተነሳ በአካባቢው እና ከአካባቢው ውጪ ባሉ፤ ነገር ግን በአካባቢው ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ በሚጥሩ ሀገሮች መካከል ፉክክር እየተስተዋለ ነው፡፡ ይህ ውድድርና ፉክክር ወደ ግጭት ላለማምራቱ ምንም ዋስትና የለም፡፡

የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ ያሬድ (ዶ/ር) እንደሚያስረዱት፣ ኢትዮጵያ የባህር በር ለማግኘት የሚያስችሏት የተለያዩ አማራጮች ያሏት ሲሆን፤ በዋናነት ሁለቱን መጥቀስ ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው አማራጭ በሰላማዊ ስምምነት ጥያቄውን መመለስ ነው። ሁለተኛው አማራጭ ደግሞ በሰጥቶ መቀበል መርህ ላይ የተመሰረተ ነው። መንግሥት ይህንን አማራጭ ዕውን ለማድረግ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ለምሳሌ፡- ኢትዮጵያ የአሰብን ወደብ ወይም የሌላ ጎረቤት ሀገር ወደብ የመጠቀም ዕድል ብታገኝ፤ በምትኩ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ... የተወሰነ ድርሻ በመስጠት አብሮ ለመጠቀም የሚያስችል አማራጭ ቀርቧል።

የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ ያሬድ (ዶ/ር) እንደሚያብራሩት፤ የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄን ሀያላን ሀገራትና ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ እንዲረዱት በሰፊው ተሰርቷል። የኢትዮጵያ የወደብ ባለቤት መሆን ጥቅሙ ለራሷ ብቻ ሳይሆን ለአካባቢው እና ለዓለም ዓቀፉ ማህበረሰብ ጭምር ነው። በአሁኑ ወቅት በአሜሪካ እና በኢራን ግጭት ሳቢያ የሆርሙዝ የባህር ወሽመጥ እየተዘጋና መስተጓጎል እየገጠመው በመሆኑ የዓለም አቀፍ ኢኮኖሚው ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰበት ነው። የየመኑ ሁቲዎች በባብል ኤል መንደብ እየፈጠሩት ያለው ተፅዕኖም የዓለም ንግድ መስመርን አደጋ ላይ ጥሎታል።

የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ ያሬድ (ዶ/ር) እንደሚያስረዱት፣ በቀይ ባህር እና በሱዌዝ ቦይ በኩል በቀን በሚሊዮኖች የሚቆጠር በርሜል ድፍድፍ ዘይት እና የተጣራ የነዳጅ ምርት ከባህረ ሰላጤው አገራት ወደ አውሮፓ፣ ሰሜን አሜሪካ እንዲሁም እስያ ይጓጓዛል። ከዓለም አቀፍ የባህር ላይ ንግድ ወደ 12 በመቶ የሚሆነው በዚህ መስመር ያልፋል፡፡ የቀይ ባህር አካባቢ ሀገራትን ስንመለከት፤ የመን በተለያዩ ኃይሎች የተከፋፈለችና ሰላም የራቃት ሀገር ናት። ጂቡቲ እና ኤርትራም ቢሆኑ ትናንሽና የአካባቢውን ሰላም በብቃት ማስጠበቅ የሚችሉ አይደሉም።

ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያ የአካባቢውን ሰላምና ደህንነት በጽናት ለማስጠበቅ አቅም ያላት ተመራጭ ሀገር መሆኗን ለአሜሪካ፣ ለአውሮፓ፣ ለሩሲያ፣ ለህንድ እና ለቻይና በዲፕሎማሲ ማስረዳት ይኖርባታል። የቀይ ባህር እና የቀጣናው ሰላማዊ መሆን ለግብፅ ሳይቀር ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም አለው፤ በስዊዝ ካናል የሚያልፉ መርከቦች ቁጥር እንዲጨምር በማድረግ ሀገሪቱ የምታገኘውን ገቢ በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚያሳድገው ምሁሩ ያስረዳሉ።

ዲፕሎማሲያዊ ጫና በመፍጠር እና በሰጥቶ መቀበል አማራጮች የባህር በር ለማግኘት በትጋት መስራት እንደሚገባ አበክረው የሚገልጹት ያሬድ (ዶ/ር)፣ በሀገር ውስጥ የተለያዩ ልዩነቶች ቢኖሩም በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ በአንድነት መቆም ግድ ይላል።

ልዩነቶች ቢኖሩም ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በጋራ እውን አድርገናል። እያንዳንዱ ዜጋ ለቀጣዩ ትውልድ ምን ዓይነት ሀገር ማስረከብ እንደሚፈልግ ሲጠየቅ በልቡ የሚስለው የበለፀገችና ሰላማዊ የሚለውን ነው። እንግዲህ ይህንን የጋራ ርዕይ እውን ለማድረግ እንደ የባህር በር ባሉ ከፍተኛ ሀገራዊ ፋይዳ ባላቸው ጉዳዮች ላይ በአንድነት መቆም ያስፈልጋል። ጠንካራ፣ በኢኮኖሚ የዳበረች፣ አስተማማኝ ሰላም እና ደህንነት ያላት ሀገር ለመገንባት ሁሉም ዜጋ የበኩሉን ድርሻ መወጣት እንደሚኖርበትም ምሁሩ ያክላሉ፡፡

የኢትዮጵያን የባህር በር ጥያቄ በዘላቂነት ለመመለስ መንግስት እያደረጋቸው ያሉትን ዘርፈ-ብዙ ጥረቶች አጠናክሮ መቀጠል አስፈላጊ መሆኑ አያከራክርም። እያደገ የመጣውን የህዝብ ቁጥር በአግባቡ ለመጠቀም እና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዋን አጠናክራ ለማስቀጠል አስተማማኝ የባህር በር ማግኘት የሉዓላዊነት እና የህልውና ጉዳይ ነው።

## የሀገር ... ከገጽ 11 የዞረ

አላቸው። እነዚህን ልዩ ልዩ ውክልናዎች በማሳየት፣ በተለያዩ ባህሎች መካከል አገናኝ ድልድዮችን ያንጻሉ፡፡ በዚህም ከተለያዩ አስተዳደግ በመጡ ግለሰቦች መካከል የመተሳሰብ እና የመረዳት ስሜት እንዲጎለብት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ የጋራ አስተሳሳሪ ትርክቶች ይፈጠራሉ። በዚህ ረገድ ሚና የሚጫወቱት ደግሞ የሀገር በቀል ባህሎችና እሴቶች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ፣ የኢትዮጵያ ሀገር በቀል ባህሎችና እሴቶች የትናንት የጋራ ታሪክ ምስክሮች ብቻ ሳይሆኑ፣ ለዛሬው ዘመናዊ ኪነ ጥበብ ህያው መሰረት፣ የጋራ ማንነት መገንቢያ እርሾዎች ጭምር ናቸው፡፡ እነዚህ ከትውልድ ትውልድ ሲወራረሱ የመጡ የዜማ፣ የሙዚቃ መሳሪያ፣ የስነ-ቃል፣ የቅርጻ ቅርጽ፣ የስዕል፣ የፍልስፍና እና የጥበብ ሀብቶች ኢትዮጵያን በብዝሃነት እንድታሸበርቅ አድርገዋል። እንደ ኢትዮ-ጃዝ ባሉ ድንቅ ሙዚቃዊ የፈጠራ ስልቶች አማካኝነት ዓለም አቀፋዊ እውቅናንም አጎናጽፈዋታል። ስለሆነም እነዚህን ሀገር በቀል የኪነ ጥበብ አሻራዎች በጥናትና ምርምር መደገፍ፣ መንከባከብና ለዘመናዊው የኪነ ጥበብ እድገት እንደ ዋና የፈጠራ ምንጭ መጠቀም ያስፈልጋል። ከምንም በላይ ደግሞ እርስ በእርስ የሚተዋወቅ፣ የሚከባበርና ጠንካራ የጋራ አሰባሳቢ ትርክት ያለው ማህበረሰብ ለመገንባት ወሳኝና ምትክ የሌለው ድርሻ ይጫወታሉ፡፡

## የክረምቱ ... ከገጽ 14 የዞረ

ቢኒያም፤ ትምህርቱ ከሃምሌ ወር መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ነሃሴ 20 ድረስ የሚሰጥ ነው። ይህ የበጎ ፈቃድ ማጠናከሪያ ትምህርት ዋና ዓላማው በጎ ፈቃድን ባህል ለማድረግ፣ ተማሪዎቹ አዲስ ለሚገቡበት የትምህርት ክፍል ለማነቃቃት እና ግንዛቤ ለማስጨበጥ ተብሎ የተዘጋጀ መርሃ ግብር ነው። መርሃ ግብሩ ማንኛውም መማር የሚፈልግ ተማሪ ገብቶ እውቀት የሚያገኝበት፣ ራሱን ከአልባሌ ቦታ የሚታደግበት ጭምር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

የክረምት ማጠናከሪያ ትምህርት በበጎ ፈቃደኞች ከክፍያ ነፃ በሆነ መንገድ ስለሚሰጥ ለወላጆች የገንዘብ ክፍያን ያስቀርላቸዋል፡፡ የመማር ፍልጎት ኖሯቸው መክፈል ባለመቻላቸው ሳይማሩ የሚቀሩ ልጆች እንዳይኖሩ ያደርጋል፡፡

በሌላ በኩል መምህራንና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በበጎ ፈቃደኝነት ሲያገለግሉ ወይም እውቀታቸው ሲያጋሩ ማህበራዊ ኃላፊነታቸውንም እየተወጡ መሆኑን የጠቆሙት ቡድን መሪው፣ ይህን የማጠናከሪያ ትምህርት ከአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ጋር በቅንጅት እቅድ ከማውጣት በየሳምንቱ እስገመገምገም የደረሰ ስራ እየተሰራ መሆኑን አክለዋል፡፡

በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽኑ በጎ ፈቃደኞችን የመመልመል፣ የመመዝገብና የማሰማራት ስራ እንደሚሰራ ገልፀው፤ በ2018 ዓ.ም በክረምት የበጎ ፈቃድ የማጠናከሪያ ትምህርት መርሃ ግብር ከ140 በላይ በሚሆኑ ትምህርት ቤቶች 56 ሺህ 708 ተማሪዎች እየተማሩ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ አበበ ቸርነት በበኩላቸው፤ የክረምት የበጎ ፈቃድ ማጠናከሪያ ትምህርት ተማሪዎች የክረምት ጊዜያቸውን ተጠቅመው ለቀጣይ የትምህርት ዘመን በቂ ዝግጅት ማድረግንና የትምህርት ጥራት ማረጋገጥን ያለመ መሆኑን ይናገራሉ፡፡

ይህ የበጎ ፈቃድ የማጠናከሪያ ትምህርት ተማሪዎች በባለፈው ዓመት ያልገባቸውን ጠይቀው እንዲረዱ፣ ግንዛቤያቸው እንዲጎለብት፣ በጥልቀት የማንበብ አቅማቸውን እንዲያዳብሩ፣ ለቀጣይ ትምህርታቸውም በቂ ዝግጅት እንዲያደርጉና የተሻለ ውጤትም እንዲያስመዘግቡ በማድረጉ ረገድ ሚናው የጎላ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ትምህርት ቢሮ በክረምት ወቅት አቅዶ ከሚሰራቸው ስራዎች ውስጥ የክረምት የበጎ ፈቃድ የማጠናከሪያ ትምህርት አንዱ ነው፡፡ ይህንንም ትምህርቱ በተያዘለት የጊዜ መርሃ ግብር መከናወን አለመከናወኑን፣ ጥራቱን ጠብቆ መሰጠት አለመሰጠቱን እንዲሁም የተሻለ መማር ማስተማር እንዲኖር መደረግ ስላለባቸው ጉዳዮች ከህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ጋር በመሆን የመገምገም ስራዎች ይሰራሉ። ይህም የትምህርት ስራ የተማሪዎችን አዕምሮ መቅረፅ በመሆኑ አንድ ጊዜ ተሰርቶ የሚቆም አለመሆኑን ማሳያ እንደሆነ አቶ አበበ አብራርተዋል፡፡

የክረምት የበጎ ፈቃድ ማጠናከሪያ ትምህርት ተማሪዎች ለመደበኛው ክፍል እንዲዘጋጁ ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳም እንዳለው የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ ወላጆች ልጆቻቸውን እንዲማሩ፣ ተማሪዎችም ትምህርቱን በአግባቡ እንዲከታተሉና ሌሎች ባለድርሻ አካላትም የድርሻቸውን እንዲወጡ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

## የጨረታ ማስታወቂያ

### የጨረታ ቁጥር ስፖርት ም/ቤት 01/2018

በቦሌ ክ/ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት በወረዳ 14 ለሚ ሜዳ የሚገኘውን G+1 ለንግድ ቤት የሚሆኑ የተለያዩ ሱቆች አገልግሎት የሚውል አወዳድሮ ለማከራየት ይፈልጋል። በመሆኑም ቤቶቹ የምድር ቤትና G+1 ያለው ሲሆን፣ 20 የተለያዩ ሱቆች ሲሆኑ የተሟላ ሽንት ቤት፣ ውኃና መብራት እንዲሁም ጥበቃ ያለው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶችን የምታሟሉ በጨረታው እንድትሳተፉ ይጋብዛል፡፡

1. የታደሰ የቀበሌ/ የነዋሪነት/ መታወቂያ እንዲሁም የጨረታ ሰነዱ የተገዛበት ወይም የተከፈለበት ገቢ ደረሰኝ ፎቶ ኮፒ አብሮ ከጨረታ ሰነዱ ጋር መያያዝ /ማስገባት/ ይኖርበታል፡፡
2. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ብር 50,000.00 (ሀምሳ ሺህ ብር) "በቦሌ ክፍለ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት በስፖርት ማዘወተሪያ ስፍራዎች" ስም በተሰራ ሲ.ፒ.ኦ ከጨረታ ሰነዱ ጋር ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
3. ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በስራ ሰዓት በቦሌ ክ/ከተማ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ፑል አስተዳደር እና ፋይናንስ ጽ/ቤት ግዥ ቡድን 3ኛ ፎቅ የቦሌ ክ/ከተማ ህንፃ ላይ በመቅረብ ለእያንዳንዱ ጥቅል የማይመለስ ብር 500.00 (አምስት መቶ ብር) በስፖርት ማዘዉተሪያ ስፍራ አካውንት ቁጥር **ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 1000757608603** በመክፈል ሰነዱን መውሰድ ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን ዋጋ በጨረታ ሰነድ ውስጥ በሚገኘው የዋጋ ማቅረቢያ ላይ በመሙላት በታሸገ ፖስታ የጨረታ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 (አስር) ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ግዥ ቡድን በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡
5. በተጫራቹ የተሞላው ዋጋ በግልጽ ፅሑፍ መቀመጥ እና መፈረም አለበት፡፡
6. አንድ ተጫራች መጫረት የሚችለው ለአንድ (1) ሱቅ ብቻ ነው፡፡ ይህን ተላልፎ የተገኘ ከጨረታ ውጪ ይደረጋል፡፡ የተጫረተውን ሱቅ ካሸነፈ በኋላ ውል ሳይዋዋል ቢቀር ያስያዘው ሲ.ፒ.ኦ ይወረሳል፡፡
7. አሸናፊ አካላት ሱቆቹ ለመጠጥና ከመጠጥ ጋር የተያያዙ ንግዶችን፣ ለብረታ ብረት ብየዳ ስራ፣ ለቁማር (ቤቲንግ)፣ ለአልኮል፣ ለጫትና ሲጋራ እንዲሁም አካባቢን በድምጽ የሚረብሹ ነገሮች መጠቀም ክልክል ነው፡፡
8. የጨረታው አሸናፊ የሚለየው በሚሰጠው ከፍተኛ ዋጋ ይሆናል፡፡ ማናቸውም ተጫራቶች በአንድ ቤት ላይ እኩል ዋጋ ካላቀረቡ እና ከመካከላቸው አንድ ሴት ተጨራች ካለች አሸናፊ እንድትሆን ይደረጋል፤ ሆኖም እኩል ዋጋ ያቀረቡት ተጫራቶች ተመሳሳይ ጾታ ከሆኑ አሸናፊው በጨረታ ኮሚቴ አባላት ፊት ቀርቦ በዕጣ የሚለይ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ሂደት አሸናፊ የሆነው ተጫራች በጊዜ ገደቡ ቀርቦ ካልተዋዋለ ለቦታው ሁለተኛ የወጣው ተጫራች ጽ/ቤቱ በሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርቦ መዋዋል ይችልል፡፡
9. ጨረታው ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለተከታታይ 10 የስራ ቀናት የሚቆይ ሲሆን፣ በመጨረሻው ቀን ከቀኑ 10:00 ሰዓት ታሽጎ በማግስቱ የስራ ቀን ከሆነ ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት ካልሆነ ግን በቀጣይ የስራ ቀን ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
10. ጽ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**አድራሻ፡- ቦሌ ክ/ከተማ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ፑል አስተዳደር እና ፋይናነስ ጽ/ቤት መገናኛ አደባባይ 3ተኛ ፎቅ**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቦሌ ክ/ከተማ የዲዛይን ስራዎች ፑል አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤት**

---

### የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በጥሩወርቅ ተሰማ እርገጤ ስም የተመዘገበ ይዞታ በካርታ ቁጥር የካ/255994/13 የተሰጠበት ቀን 11/09/13 ዓ/ም የሙብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት /ካርታ/ 25/09/2018 ዓ/ም የሚገልፅ መረጃ በማቅረብ አመልክተዋል በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ በመሆኑ ካርታውን አግኝቸዋለሁ ወይም ሙብት አለኝ የሚል አካል ካለ በ30 ቀናት ውስጥ ከላይ በተጠቀሰው መስሪያ ቤት ማለትም በየካ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ሳይሆን ቢቀር በምትኩ ለአመልካች ምትክ ሰርተፊኬት የምንሰጣቸው መሆኑን በማክበር እንጠይቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ**
**የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

### የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ወረዳ 14 አቶ/ ወ/ሮ ጠጅቱ አለሙ ካሳ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ የቤት ቁጥር 002 ባለቤትነት የይዞታ ካርታ ቁጥር የካ12/15971/08 የተሰጠበት ቀን 19/1/2008ዓ/ም ሴሪ ቁጥር 107142 የሆነ የሙብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንደጠፋባቸው በቀን 24/11/2018 ዓ/ም አመልክተው ይህንኑ ይዞታ በጋዜጣ 30 ቀን ውስጥ በይዞታው ሙብት አለኝ የሚል እና ይህ ካርታ የጠፋ ስለሆነ ያገኛ ካለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ የይዞታ ካርታው መጥፋቱን በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣላቸው ሲሆን ካርታ መጥፋቱን የሚያውቅ ካለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ለአመልካቹ ካርታ ወጪ ተደርጎ የሚሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ**
**የየካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ተናኜ ፀሐይ ወ/ፃዲቅ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከለተማ ወረዳ 01 የይዞታ መለያ ቁጥር ቦሌ1/29/1/3/268804/26967/03 የሚገኘው የጋራ መኖሪያ ቤት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት / ካርታ ሴሪ 0251035 የሆነው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ /የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት /ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይገኛዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ**
**የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች አዜብ አብርሃ በቀን 29/11/2018 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በሂሩት ጉልላት ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ቦሌ 16/117/2109 ሴሪ 127240 የቦታው ስፋት በሰነድ 500 ሜ.ካ የቦታው አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነ ይዞታ ኦርጂናል ካርታ የጠፋብኝ በመሆኑ ይሄው ተገልፆ ለሚመለከተው አካል ምትክ እንዳገኝ ደብዳቤ ይፃፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታን ወይም ቤቱን በዕዳ ይገኛዋለሁ አስይገኛዋለሁ የሚል አካ በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁን እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

አቶ ደሳለኝ በዛብህ ፈለቀ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 11 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000061007267670216 የሚገኘው የጋራ መኖሪያ ቤት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት /ካርታ ሴሪ ቁ C 186404 የሆነው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ /የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት / ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይገኛዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች አብዱልከሪም ጌታቸው ሙሳ በቀን 06/11/2018 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በራሳቸው ስም የተመዘገበ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 10 ልዩ ቦታው መሪ ሎቄ የካርታ ቁጥር ለ/ኩ/11/2/6/158547/00 የሴሪ ቁጥር 1681197 የቤት ቁጥር ML/B-02SN/206 የቤቱ ስፋት በሰነድ 42.87 ሜ.ካ የቤቱ አገልግሎት ለንግድ የሆነ ኮንዶሚኒየም ቤት ኦርጂናል ካርታ የጠፋብኝ በመሆኑ ይሄው ተገልፆ ለሚመለከተው አካል ምትክ እንዳገኝ ደብዳቤ ይፃፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይገኛዋለሁ አስይገኛዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁን እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት**
**ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

አቶ ንጉሴ ሀይሌ ገብረማርያም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000061007259134041З ሴሪ ቁጥር C241823 የሆነው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ ይገኛዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ አጀንሲ**
**የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ በቀድሞ ወረዳ 19 ቀበሌ 54 በአዲሱ ወረዳ 08 የቤት ቁጥር 185 በካርታ ቁጥር 11/7616256/00 በሴሪ ቁጥር 027368 ለፋናዬ ፈለቀ እና የኃይለማርያም ዳውድ 6 ወራሾች ተመዝግቦ ተሰጥቶ የነበረ ካርታ ቀደም ሲል የጠፋ መሆኑ በጋዜጣ የታወጀ እና በተቋማችን ታውቆ የመከነ ካርታ አሁን የተገኘ ስለሆነ ይኸው ካርታ ወደ ነበረበት የተመለሰ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ / ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 02 የካርታ ቁጥር ወ2/ውዝ01/587/14454/00 ሴሪ L035154 የሆነው በአቶ ሽምሱ ባህሩ ኑሩ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 21/11/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይገኛዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ**
**ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለፅ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት በ አባተ አበጋዝ ስም የተመዘገበ ይዞታ መለያ ቁጥሩ AA000051102018 የሆነና የተሰጠበት ቀን 19/03/2011 የሆነ የሙብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በቁጥር ለም/ፖጣ/075/18 በ 29/11/2018 ዓ.ም የሚገልፅ ማስረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡ ይህም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለሁ ወይም ሙብት አለኝ የሚል በ 90 ቀናት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅ/ጽ/ቤት ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ምትክ ሰርተፊኬት የምንሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ/ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ የኔነሽ ከማል ዑመር አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ//ክ/ከተማ ወረዳ 08 ካርታ ቁጥር ንፋ/ስ/ሼ - 11/24719/23328/01 ቁጥር ይዞታ የሴሪ ቁጥሩ 115411 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 07 በካርታ ቁጥር 03934 በሴሪ ቁጥር 018544 ወ/ሮ ሀረገወይን ካሳ እውነቱ ስም የተመዘገበ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጁ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ ኢብራሂም ኖህ ሙሳ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ቁጥር AA000080200289 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ ባየች ደምሴ ማሸሌ አበበ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የይዞታ ልዩ መለያ ቀጥር AA0000610073094590220 ሴሪ ቁጥር R 0284792 የሆነው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት /ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 07 ክልል ውስጥ በእነ ሜሮን አባይነህ 3 ሰዎች ስም በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000070702346 ሴሪ ቁጥር L 0124522 በሆነ የተመዘገበው ይዞታ፤ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ/ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጁ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን 27/11/2018 ዓ.ም ጀምሮ 30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

## የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ዘውዲቱ መኮንን አካሉ ስም የተመዘገበ ኮንዶሚኒየም በካርታ ቁጥር የካ09/29028/08 የተሰጠበት ቀን 07/04/08 ዓ.ም የመብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት /ካርታ 22/11/2018 ዓ/ም የሚገልፅ መረጃ በማቅረብ አመልክተዋል በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ በመሆኑ ካርታውን አግኝቸዋለሁ ወይም መብት አለኝ የሚል አካል ካለ በ30 ቀናት ውስጥ ከላይ በተጠቀሰው መስሪያ ቤት ማለትም በየካ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ሳይሆን ቢቀር በምትኩ ለአመልካች ምትክ ሰርተፊኬት የምንሰጣቸው መሆኑን በማክበር እንጠይቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ጌታቸው አብርሃ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ካርታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 02458/1 ሴሪ ቁጥር 0633258 የይዞታ ስፋት 144 ካ.ሜ የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስመዝገባቸውን በቁጥር ወማ/8/1392/18 በቀን 22/11/18 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በተገለፀልን መሰረት ወጪውን ግለሰቡ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅላቸው እየገለፅን በማንኛውም ምክንያት የጠፋውን ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ እስከ 30 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ካላቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ወረዳ 01 ክልል ውስጥ የሚገኝ በብሩክታዊት ሙሉጌታ ስም የተመዘገበ ካርታ ቁጥር 029803 ሴሪ ቁጥር 021701 የቦታው ስፋት 94.64 ካሬ ሜትር የሆነ ይዞታ በእጃቸው ላይ ያለ ኦርጂናል ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ እንዲታወጅ እየገለጽን በማንኛውም ምክንያት የጠፋውን ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከታወጀበት ዕለት ጀምሮ እስከ 30 ተከታታይ የሥራ ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት ከፍያለው ደረሰ ታረቀኝ በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ በቀድሞ ቀበሌ --- በአሁኑ ወረዳ 03 ቤት ቁጥር ------- ነዋሪ ሲሆኑ ከይዞታ አስተዳደር የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር ወ3/ውዝ01/1055/18744/00 በሴሪ ቁጥር 078739 ኦርጂናሉ ካርታ ተፈልጎ ሊገኝ ስላልቻለ በምትኩ ሌላ ካርታ እንዲሰጣቸው ይህንን ካርታ በዕዳ፣ በዋስትና ወይም በሌላ በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ካለ በ30 ቀን ውስጥ ኮ/ቀ/ክ/ከተማ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ካላሳወቀ ግን በምትኩ ሌላ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች ወ/ሮ መሰረት ክፍሌ በአያት ኃ/የተ/የግ/ማህበር ስም የተመዘገበ በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የካርታ ቁጥር ቦሌ 10/61/4/6/47094/00 ሴሪ ቁጥር 129451 የቦታው ስፋት 90 ካ.ሜ የቦታው አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነው ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋብኝ ሌላ ካርታ ምትክ እንዲሰጠኝ በማለት ያቀረቡ በመሆኑ ካርታ የጠፋ መሆኑን በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ኃላፊነት የምንወስድ ይሆናል፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ ኢብራሂም ኖህ ሙሳ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ቁጥር AA000080210288 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ሜሮን ግርማ ጽጌ በቀን 24/11/2018 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 ይዞታ መለያ ቁጥር AA000060500803 ሴሪ ቁጥሩ L 0122828 ይዞታነቱ የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ የመሬት ይዞታ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት /ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች ዶ/ር አክሊሉ ሹመት በቀን 16/11/2018 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 02 ክልል ውስጥ የሚገኝ በአቶ ኑራ ሽፋ በሽር ስም የተመዘገበ እና በሽያጭ ያገኙሁት የካርታ ቁጥር የካ/238385/12 የሆነው ኦርጂናል ካርታ የጠፋብኝ በመሆኑ ይሄው ተገልፆ ለሚመለከተው አካል ምትክ እንዳገኝ ደብዳቤ ይፃፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁን እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 11 የቤት ቁጥር 9999 የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ቁጥር ወ11/ውዝ01/1489/23284/00 ሴሪ ቁጥር 070887 የተሰጠበት ቀን 08/09/2010 የሆነው በአቶ ሳሊም መርሻ ቢርቢሮ ስም የተመዘገበው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 16/11/2018 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ 30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለፅ እንደተሞከረው አየሁ ገነቱ ብዙነህ ስም የተመዘገበ ወረዳ 08 የካርታ ቁጥሩ (ጂ.አይ.ኤስ) 000353 ሴሪ ቁጥሩ 001083 የተሰጠበት ቀን 27/05/1996 የሆነ ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ ታውጆ አገልግሎት እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳዮቹ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጂናል ካርታም ሆነ ኮፒውን /ይዤዋለሁ/ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች ተማም ብዛኒ በቀን 09/11/2018 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በራሳቸው ስም የተመዘገበ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 08 ክልል ውስጥ የካርታ ቁትር ቦሌ8/49/3/9/92/4708/01 ሴሪ ቁጥር 0115402 የቦታው ስፋት በሰነድ 175 ሜ.ካ የቦታው አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነ ይዞታ ኦርጂናል ካርታ የጠፋብኝ በመሆኑ ይሄው ተገልፆ ለሚመለከተው አካል ምትክ እንዳገኝ ደብዳቤ እንዲፃፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁን እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

## የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወረዳ 09 ወንድይፍራው ታረቀኝ ስም የተመዘገበ ይዞታ የይዞታው ልዩ መለያ ቁጥር AA000050900701 የተሰጠበት ቀን 24/10/2009 ዓ.ም የመብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንደጠፋባቸው በቁጥር የካፖ/ለ/ቀ/15/812/18 በቀን 22/11/2018 ዓ.ም የሚገልፅ መረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡

ይህን በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም መብት አለኝ የሚል በ90 ቀናት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ምትክ ሰርተፊኬት የሚሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# የአዳጊዎቹ ተሳትፎ በዓለም ሻምፒዮናው

**በሳህሉ ብርሃኑ**

የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ሻምፒዮና (World Athletics U20 Championships) ወይም የዓለም ጁኒየር የአትሌቲክስ ሻምፒዮና ውድድር ከ20 ዓመት በታች ባሉ አትሌቶች መካከል የሚደረግ ዓለም አቀፍ የአትሌቲክስ ውድድር ነው። በዓለም አቀፉ የአትሌቲክስ ፌዴሽኖች ማህበር አዘጋጅነት በየሁለት ዓመቱ የሚዘጋጅው የመምና የሜዳ ላይ ውድድር እ.አ.አ. ከ1986 ጀምሮ የዓለም ወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና በሚል ስያሜ ሲካሄድ ቆይቷል፡፡ እ.አ.አ 2015 የስያሜ ለውጥ በማድረግ የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ሻምፒዮና በሚል ስያሜ እየተደረገ ይገኛል።

የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ከቀላል የሜዳሊያ ፉክክር ባለፈ፣ የዓለም አትሌቲክስ የታላላቅ አትሌቶችን ቀጣይ ትውልድ የሚያስተዋውቅበት ዋነኛ መድረክ ነው። በዚህ ውድድር ላይ የሚደምቁ ወጣቶች በቀጣይ የኦሎምፒክ እና የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና መድረኮች ላይ የዓለም የበላይነቱን ለመረከብ የሚያስችላቸውን የስነ-ልቦና እና የቴክኒክ ብቃት የሚገነቡበት እንደሆነም ይነገራል።

ከ40 ዓመታት በፊት እ.ኤ.አ በ1986 በአቴንስ ከተማ አንድ ብሎ የጀመረው የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ሻምፒዮና፤ እስከ 20ኛው (የ2024 ሊማ) ሻምፒዮና ድረስ አሜሪካ በአጠቃላይ ሜዳሊያዎች ብዛት ቀዳሚነቷን ይዛለች። አሜሪካ በአጫጭር ርቀት ፣ በውርወራና በዝላይ ውድድሮች የበላይነት ያላት ሲሆን ኬንያ እና ኢትዮጵያ፡- በመካከለኛ እና በረጅም ርቀት ሩጫዎች ባላቸው ከፍተኛ የበላይነት በቅደም ተከተል 2ኛ እና 3ኛ ደረጃን ይይዛሉ።

ኢትዮጵያ የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ሻምፒዮና በታሪኳ ከፍተኛ የተባለውን ውጤት ካስመዘገበችባቸው ውድድሮች መካከል በኮሎምቢያ ካሊ የተደረገው አንዱ ነው፡፡ በ2014 ዓ.ም በኮሎምቢያ ካሊ ከተማ በተካሄደው የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ኢትዮጵያ በ12 ሜዳሊያዎች ከአፍሪካ አንደኛ ከዓለም ሶስተኛ ሆና ያጠናቀቀችበት ነው። ኢትዮጵያ በስድስት ወርቅ፣ በአምስት ብር እና አንድ ነሃስ ሜዳሊያ በአጠቃላይ በ12 ሜዳሊያዎች አሜሪካንና ጃማይካንም ተከትላ ነው በሶስተኛነት ያጠናቀቀችው። ይህም ውጤት እስከ ዛሬ ከተካሄዱት የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ታሪክ የተመዘገበ ውጤት ከፍተኛው እንደሆነ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን መረጃ ያሳያል፡፡

በወቅቱም አሜሪካ በሰባት ወርቅ፣ በአራት ብርና በአራት ነሐስ ሜዳሊያ በ15 ሜዳሊያዎች በአንደኛነት አጠናቃለች። አሜሪካን ተከትላ ጃማይካ በስድስት ወርቅ፣ በሰባት ብርና በሶስት ነሃስ በአጠቃላይ 16 ሜዳሊያዎች በማግኘት ከፍተኛውን የሜዳሊያ ቁጥር ብትይዝም በአሜሪካ በወርቅ ተበልጣ በሁለተኛነት አጠናቃለች። አፍሪካዊቷ አገር ኬንያ ሶስት ወርቅ፣ ሶስት ብርና አራት ነሐስ በማግኘት በአጠቃላይ በአስር ሜዳሊያዎች በአራተኛነት ውድድሩን ማጠናቀቋን ከዓለም አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ያገኘው መረጃ ያሳያል።



ፎቶ- ከገፀ ድር
በ 21ኛው የዓለም ከ20 ዓመት በታች ሻምፒዮና እየተካፈሉ ካሉ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች መካከል ከፊሎቹ

ከአራት ዓመት በፊት በኮሎምቢያ በተከናወነው የአትሌቲክስ ሻምፒዮና ወጣቱ አትሌት ኤርምያስ ግርማ በ800 ሜትር የወርቅ እና በ1 ሺህ 500 ሜትር የብር ሜዳልያዎችን በማግኘት የጥምር ሜዳሊያዎች ባለቤት ነበር። በአንድ ሺህ ሜትር የሴቶች ፍጻሜ ውድድር እንደዚሁ አትሌት ብርቄ ሃየሎም የውድድሩን ክብረ ወሰን በማሻሻል ጭምር አንደኛ ወጥታ የወርቅ ሜዳልያ ባለቤት ነበረች፡፡

ሴት አትሌቶች በደመቁበትና ከዚህ ቀደም የኦሪጎን በኦሪጎን አትሌቲክስ ሻምፒዮና እንደዚሁ ኢትዮጵያ በአስር ሜዳሊያዎች ከፍተኛውን ሜዳሊያ ማስመዝገቧ ይታወሳል። ኢትዮጵያ በ4 ወርቅ፣ በ4 ብርና በ2 ነሃስ ከአዘጋጇ አሜሪካ በመቀጠል ከዓለም 2ኛ ደረጃ ከአፍሪካ አንደኛ ደረጃ በመያዝ ማጠናቀቋ ይታወሳል። በአጠቃላይ 41 አገራት ቢያንስ አንድ ሜዳሊያ ሲያሸንፉ 24 አገራት ደግሞ ቢያንስ አንድ ወርቅ ማግኘታቸውን ከዓለም አቀፉ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ያገኘነው መረጃ ያስረዳል።

በ2024 በፔሩ ሊማ በተካሄደው 20ኛው የዓለም ከ20 ዓመት በታች ሻምፒዮና ኢትዮጵያ 6 የወርቅ፣ 1 የብር እና 2 የነሐስ ሜዳሊያዎችን በአጠቃላይ 9 ሜዳሊያዎች በማሸነፍ በሜዳሊያ ሰንጠረዥ 2ኛ ደረጃን ማስመዝገቧ ይታወሳል።

የሻምፒዮናው መድረክ የዓለም የወደፊት የኦሎምፒክና የዓለም ሻምፒዮኖች የሚፈጠሩበት እንደሆነ ይታወቃል፤ በቀደሙት ውድድሮችም በርካታ ታዋቂ አትሌቶች ከዚህ መድረክ ተነስተው ዓለም አቀፍ ስኬት አስመዝግበዋል። በዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ኢትዮጵያውያኑ አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ 1992 ዓ.ም በ5 ሺህ ሜትር እና 10 ሺህ ሜትር፣ አትሌት አሰፋ መዝገቡ 5 ሺህ ሜትር፣ 10 ሺህ ሜትር እና እንስቷ አትሌት መሰረት ደፋር በ3 ሺህ ሜትርና 5ሺህ ሜትር ሁሉት ሁለት ጊዜ በማሸነፍ ስኬታማ አትሌቶች ናቸው፡፡

የዘንድሮው 21ኛው የዓለም ከ20 ዓመት በታች (World Athletics U20 Championships) አትሌቲክስ ሻምፒዮና በአሜሪካ ኦሪገን ግዛት፣ ዩጂን ከተማ ከሐምሌ 29 እስከ ነሐሴ 3/2018 ዓ.ም. እየተካሄደ ይገኛል፡፡ በዚህ ዓለም አቀፍ ሻምፒዮና ከ190 የሚጠጉ አገራት የሚወክሉ ከ1 ሺህ 700 በላይ ወጣት አትሌቶች በ44 የውድድር ዓይነቶች ላይ ለዓለም ክብር እና ለሜዳልያ ይፎካከራሉ።

በሻምፒዮናው ኢትዮጵያ በ5 ሺህ ሜትር፣ 3 ሺህ ሜትር፣ 1 ሺህ 500 ሜትር፣ 800 ሜትር (በሁለቱም ፆታዎች)፣ 3ሺህ ሜትር መሰናክል (በሴቶች)፣ 400 ሜትር (በሴቶች) እንዲሁም በእርምጃ ውድድር (በሁለቱም ፆታዎች) በመሳተፍ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ በተጠናከረ ዝግጅት ቀርባለች። እንደ አትሌት ሀብታሙ ገበየሁ፣ አትሌት ሀረገወይን ካላዩ፣ አትሌት ኤልሳቤት አማረ፣ ዮርዳኖስ ጽጋቡ፣ አትሌት ደስታው ታዴ፣ እና አትሌት አየለ ሰውነት ለአሸናፊነት ተስፋ ከተጣለባቸው አትሌቶች መካከል ይገኙበታል፡፡

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚደንት ኮማንደር አትሌት ስለሺ ስህን አትሌቶቹ የኢትዮጵያ የአትሌቲክስ ቀጣይ ተስፋ መሆናቸውን በመግለጽ፣ ይህንን እድል በአግባቡ በመጠቀም በዓለም መድረክ አቅማቸውን እንዲያሳዩ አበረታተዋል። አትሌቶቹ የኢትዮጵያን የአትሌቲክስ ታሪክና ክብር በሚመጥን መልኩ በትጋት፣ በዲሲፕሊንና በከፍተኛ የውድድር መንፈስ በመወዳደር የሀገራቸውን ባንዲራ በክብር ከፍ ለማድረግ ወደስፍራው ስለማቅናታቸው ፕሬዝዳንቱ ይገልጻሉ፡፡ ውድድሩ ለወጣት አትሌቶች ዓለም አቀፍ ልምድ የሚያስገኝ እና የወደፊት የኦሎምፒክና የዓለም ሻምፒዮኖች የሚፈጠሩበት አንዱ ትልቅ መድረክ በመሆኑ፣ የኢትዮጵያ ቡድንም የሀገሪቱን የረጅም ርቀት አትሌቲክስ ስኬት ለማስቀጠል ተስፋ ተጥሎበታል።

ሻምፒዮናው በዓለም አቀፍ የአትሌቲክስ ታሪካዊ መድረክ በሆነው በሄይዋርድ ፊልድ ስታዲየም የሚካሄድ ሲሆን፣ ከዓለም ዙሪያ የተውጣጡ ወጣት አትሌቶች ለዓለም ክብር በከፍተኛ ፉክክር ይሳተፋሉ። የዘንድሮው ሻምፒዮና በሚካሄድበት ወቅት በዩጂን ኦሪገን የሚኖረው የአየር ንብረት እና የስታዲየሙ ድባብ ለአትሌቶች ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅ ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቡድን የቴክኒክ አሰልጣኞች የአትሌቶችን ፍጥነት እና ጥንካሬ ከመገንባት ባለፈ፣ በከፍተኛ ፉክክር ወቅት የሚደረጉ ታክቲካዊ ውሳኔዎች ላይ ትኩረት አድርገው ሲሰሩ ቆይተዋል። የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ቡድኑ በሻምፒዮናው ላይ የተሳካ ተሳትፎ እንዲያደርግ አስፈላጊውን የቴክኒክ፣ የህክምና የአስተዳደርና የሎጂስቲክስ ዝግጅቶች በተጠናከረ ሁኔታ ስለማከናወኑም ተነግሯል።

ኢትዮጵያ በወጣቶች አትሌቲክስ መድረክ የበርካታ የዓለም ሻምፒዮኖችን በማፍራት የታወቀች ሲሆን፣ የዘንድሮውም ቡድን ያንን ታሪክ ለመቀጠል በከፍተኛ ዝግጅት ወደ ውድድሩ አቅንቶል በማለት የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌደሬሽን ይገልጻል። የፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንት ኮማንደር አትሌት ስለሺ ስህን አትሌቶችን የመምረጥ ሂደቱ በጥንቃቄ የተከናወነ ስለመሆኑ ያስረዳሉ። ከዚህ ቀደም የእድሜ ተገቢነት ጥፋቶች ስለተፈፀሙ በዓለም አትሌቲክስ ትኩረት ውስጥ ነን ያለፉት ስህተቶች እንዳይደገሙ ተገቢ አትሌቶችን ብቻ ነው ለይተን ያቀረብነው ብለዋል፡፡

ቡድኑ ልምምዱን በአዲስ አበባ ስቴዲየም፣ በጣፎ፣ በእንጦጦ አካባቢ፣ በቀነኒሳ ሆቴል ትራክና ጂም እንዲሁም ከኦሪገን የአየር ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ ምቹ በሆኑ ቦታዎች በተጠናከረ ሁኔታ ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ከዓለም አቀፉ የአትሌት ታማኝነት ዩኒት (Athletics Integrity Unit AIU) ጋር በመተባበር ለአትሌቶች፣ አሰልጣኞችና የልዑክ አባላት የዕድሜ ትክክለኛነት፣ የውድድር ሥነ-ምግባር እና የአትሌት ታማኝነት ጉዳዮች ላይ ማስተማሪያ ስልጠና ተሰጥቷል። የስልጠናው ዓላማም ወጣት አትሌቶች በትክክለኛ መረጃ እና በሙያዊ ሥነ-ምግባር የዓለም አቀፍ ውድድሮችን እንዲሳተፉ ማድረግ ነው።

በሻምፒዮናው እስካሁን በተካሄዱ ውድድሮች ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የብር እና የነሐስ ሜዳሊያዎችን በመውሰድ አበረታች ጅምር አሳይተዋል። በሴቶች 5ሺህ ሜትር አትሌት ሽቶ ጉሚ ሁለተኛ በመውጣት የብር ሜዳሊያ ስታጠልቅ፣ በወንዶች 5ሺህ ሜትር ደግሞ አትሌት ዳምጠው ከበደ የራሱን ፈጣን ሰዓት በማስመዝገብ የነሐስ ሜዳሊያ ለሀገሩ አስገኝቷል።

በሌሎች የማጣሪያ ውድድሮችም ድንቅ ብቃታቸውን ያስመዘገቡ ሲሆን፤ በሴቶች 3ሺህ ሜትር መሰናክል አልማዝ ዮሐንስ እና ወሰኔ አሰፋ፣ እንዲሁም በ1 ሺህ 500 ሜትር ኤልሳቤት አማረ እና ሀረገወይን ካላዩ ውጤታማ በመሆን ለፍጻሜ ውድድር አልፈዋል።

በተጨማሪም በሴቶችና በወንዶች 800 ሜትር ሀብታም ገበየሁ፣ ደራርቱ ሽብሩ፣ ነጋሄ እያሱ እና የሮሳን ግርማ ወደ ግማሽ ፍጻሜ መሸጋገራቸውን አረጋግጠዋል። ዛሬን ጨምሮ በቀጣይ ቀናትም በሚደረጉ ውድድሮች ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ተጨማሪ የሜዳሊያ ድሎችን ያስመዘግባሉ ተብሎ በትልቅ ተስፋ ይጠበቃል።